**በጅማ ዩኒቨርሲቲ**

**የማህበራዊ ሳይንስና ሥነሰብ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረምረቃ መርሐግብር (የሁለተኛ ዲግሪ)**

# ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት የማጎልበት ፋይዳ ትንተና


**በ**

**አበራጌትነት**



**ሐምሌ 2016 ዓ.ም**

**ጅማ ኢትዮጵያ**

# ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን  የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት የማጎልበት ፋይዳ ትንተና


በ

አበራ ጌትነት

ዋና አማካሪ፡-  ማንያለው አባተ(ዶ/ር)

ረዳት አማካሪ ፡-ምህሪት ሳዳሞ(ዶ/ር)

ጅማ ዩኒቨርሲቲ የማህበራዊ ሳይንስና ሥነ-ሰብ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረምረቃ መርሐግብር


ነሐሴ 2016 ዓ.ም

ጅማ ኢትዮጵያ

በጅማ ዩኒቨርሲቲ

ማህበራዊ ሳይንስና ስነ ሰብ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነጽሁፍ-አማርኛ

ትምህርት ክፍል የድህረምረቃ መርሐግብር

የፈተና ቦርድ ማረጋገጫ

ይህ ጥናት “ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ ትንተና በሚል ርዕስ በአበራ ጌትነት ተዘጋጅቶ፣ አማርኛን በማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ሲሆን፣ የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለሚያሟላ በጥናቱ አማካሪና ገምጋሚዎች ተረጋግጧል፡፡

የውጪ ፈታኝ፤ ስም________________________ ፊርማ_____________ ቀን____________

የውስጥ ፈታኝ ፤ ስም______________________ ፊርማ______________ ቀን__________

አማካሪ፤ ስም ________________________ ፊርማ ____________ቀን____________

የትምህርትክፍል ኃላፊ፤ስም________________________ፊርማ ____________ቀን__________

**የምርምር ጥራትና ወጥነት ማረጋገጫ**

ይህ ጥናት "ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ ትንተና በ9ኛ ክፍል በሚል አማርኛን በማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ሲሆን ከዚህ ቀደም በሌላ አካል ያልተሰራ ወጥ የምርምር ስራ መሆኑንና በጥናቱ ጥቅም ላይ የዋሉ ድርሳናት በተገቢው ዋቢ የተደረጉ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- አበራ ጌትነት ገሰሰ

ፊርማ፡-___________

ቀን፡- _____________

## ምስጋና

ከሁሉ በማስቀደም ወደዚህ ስኬት እንድደርስ ምክንያት የሆነኝን ልዑል እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ፡፡

ጥናቱ ይህን ገጽታ እንዲላበስ ከርዕስ መረጣ አንስቶ እስከ ማጠናቀቂያ ድረስ በያንዳንዱ ደረጃ ጥልቅ በሆነ እውቀትና አስተውሎት አንብበው ግርድፉን በማጥራት፣ በማቅናትና በማረም ጠቃሚ አስተያየታቸውንና የተለያዩ ማጣቀሻዎችን በመስጠት አባታዊና ሙያዊ ድጋፋቸው ላልተለየኝ መምህሬና አማካሪዬ ለዶክተር ማንያለው አባተ ምስጋናዬ ከልብ የመነጨ ነው፡፡ለዶክተር ጥበቡ ሽቴ ለዶክተር ምህረት ሳዳሞ እና ዶክተር ለማ ንጋቱ ለጥናቱ መቃናት ለሰጡኝ ሙያዊ አስተያየት ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ለቢፍቱ ሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ለ2015 ዓ.ም 9ኛ ክፍል ተማሪዎች በዋናውና ናሙና ሙከራ ጥናት ወቅት በመሳተፍ ላደረጉልኝ አስተዋጽኦ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡ መ/ር ሙክታር ዱራ የዋናው ጥናት ተሳታፊ የነበሩ ተማሪዎችን በማስተማር የተሰጣቸውን ስልጠና ተግባራዊ ስላደረጉ፣ መ/ር ታደስ ወልዴ፣ መ/ር አለሙ ፍርዱ፣ መ/ርት ስመኝ ጌታቸውና መ/ር ሞገስ አባተ የማስተማሪያ ስነዘዴ ዝግጅትና የመጻፍ ችሎታ ፈተናዎች ላይ አስተያየት በመስጠት፣ ፈተናዎችን በመፈተንና በማረም ስላደረጉልኝ ድጋፍ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር አካላትና ለአማርኛ ትምህርት ክፍል መምህራን ለዋናውና ሙከራ ጥናት ፈቃደኛ ሆነው ስላስተባበሩልኝ፣ ለፈተናና መጠይቅ ማባዣ እንዲሆን የእስተሽኔሪ ድጋፍና የማባዣ ማሽን ስለፈቀዱልኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ መ/ር ናስር ትዛዙ መ/ር ደስታው አሻግሬ መጠይቁንና ፈተናውን ስላባዙልኝ አመሰግናለሁ።

በመጨረሻ ከጥናቱ ጅማሬ እስከ መጨረሻ ድረስ በአይዞህ ባይነት ሲያበረታቱኝ ለነበሩ ቤተሰቦቼ፣ በተለይ ለህቴ ብዙወርቅ ጌትነት፣ ለልጄ ዳዊት አበራ ጌትነት ከልብ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

## አኅጽሮተጥናት

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ መመርመር ነበር፡፡ ጥናቱ የተከተለው ንድፍ ባለሁለት ቡድን ከፊል ፍትነታዊ (Quasi-Experimental) ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በ2015 ዓ.ም. በቢፍቱከተማ አስተዳደር፣ በቢፍቱ ሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይማሩ የነበሩ የ9ኛ ክፍል 88 ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህም ተማሪዎች መረጃዎች የተሰበሰቡት በመጻፍ ችሎታ ፈተናና በመጻፍ ተነሳሽነት መፈተሻ ጽሁፍ መጠይቅ ሲሆን መረጃዎች በባዕድ ናሙና ቲ ቴስት (Independent Samples t-test) እና በንጥል ልይይት (ANCOVA) ተተንትነዋል፡፡ የትንተናው ውጤት እንዳመለከተው የድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት የፍትነት ቡድኑ አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት ጉልህ ($p < 0.05$) ልዩነት ያለ መሆኑን አሳይቷል፡፡ በተጨማሪ የፍትነት ቡድኑ የድህረ ትምህርት በመጻፍ ተነሳሽነት መፈተሻ የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ ተሽሎ ጉልህ ($p < 0.05$) ልዩነት ያለው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህም ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት ከማጎልበት ረገድ አስተዋጽኦ መኖሩ አረጋግጧል፡፡ በዚህም መሰረት ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት ለማጎልበት አዎንታዊ ፋይዳ ያለው በመሆኑ፣ በመማር ማስተማር ሂደት ዘዴውን ክፍል ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ ጠቃሚ መሆኑንም አመልክቷል፡፡

## ማውጫ

ምስጋና ....................................................................................................................................i
አኅጽሮተቃላት ..............................................................................................................................ii
ማውጫ ....................................................................................................................................iii
ምዕራፍ አንድ ............................................................................................................................. 1
መግቢያ ..................................................................................................................................... 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ....................................................................Error! Bookmark not defined.
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ....................................................Error! Bookmark not defined.
1.3. የጥናቱ አላማዎች............................................................................................................. 1
1.4. የጥናቱ ጠቀሜታዎች ........................................................................................................ 6
1.5. የጥናቱ ወሰን.................................................................................................................... 7
1.6. የጥናቱ ውስንነት ............................................................................................................... 7
ምዕራፍ ሁለት..............................................................................Error! Bookmark not defined.
ክለሳ ድርሳናት ............................................................................Error! Bookmark not defined.
2.1. ንድፈ ሃሳዊቅኝት________________________________________________________11
2.11. የመፃፍ ችሎታ ትምህርት.................................................Error! Bookmark not defined.
2.2. የመጻፍ ችሎታና ተነሳሽነት ..............................................Error! Bookmark not defined.
2.3 በትብብራዊ ዘዴ የመማር ንድፈ ሃሳብ ..............................Error! Bookmark not defined.
2.3.1 የትብብራዊ ዘዴ የመማር ማስተማር ሂደት የአተገባበር ብልሃቶች Error! Bookmark not defined.
2.3.1.1 የትብብራዊ ዘዴ የቡድን አመሰራረት ብልሃቶች.........Error! Bookmark not defined.
2.3.1.2 ትብብራዊ ዘዴ የትግበራ ሂደቱ መሰረታዊ መርሆችError! Bookmark not defined.
2.3.2 ትብብራዊ እና ተለምዷዊ የማስተማር ዘዴ ልዩነት እንደ...........Error! Bookmark not defined.
2.3.3 በትብብራዊ ዘዴ የሚዋቀሩ የቡድን አይነቶች ...............Error! Bookmark not defined.
2.3.3.1 መደበኛ ትብብራዊ የመማር ቡድን .......................Error! Bookmark not defined.
2.3.3.2 ኢ. መደበኛ ትብብራዊ የመማር ቡድን..................Error! Bookmark not defined.
2.3.3.3 ትብብራዊ መሰረት ያላቸው ቡድኖች .....................Error! Bookmark not defined.
2.3.4 የትብብራዊ ዘዴ የትግበራ ቴክኒኮች...............................Error! Bookmark not defined.

2.3.4.1 ማሰብ መጎዳኘት እና ማጋራት................................Error! Bookmark not defined.

2.3.4.2 የተለያዩ ተግባራትን ለተለያዩ የቡድን አባላት መስጠት ........Error! Bookmark not defined.

2.3.4.3 ባለ ሶስት ደረጃ ቃለ መጠይቅ ................................Error! Bookmark not defined.

2.3.4.5 ውጤት ተኮር የቡድን አከፋፈል ..............................Error! Bookmark not defined.

2.4 ትብብራዊ ዘዴ እና የመጻፍ ችሎታ ....................................Error! Bookmark not defined.

2.5 ትብብራዊ ዘዴ እና ተነሳሽነት ............................................Error! Bookmark not defined.

2.6 በትብብራዊ ዘዴና በመጻፍ ችሎታ ትምህርት የተደረጉ ቀደምት ........Error! Bookmark not defined.

ምርምሮች ......................................................................Error! Bookmark not defined.

2.7 የጥናቱ ጽንሰ ሃሳባዊ ማእቀፍ...............................................Error! Bookmark not defined.

ምዕራፍ ሶስት.................................................................................................. 9

3.የጥናቱ ዘዴዎች............................................................................................ 32

3.1. የጥናቱ ንድፍ ............................................................................................ 32

3.2. የተጠኚ ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ______________________35

3.2.1.የትምህርት ቤትናሙናአመራረጥ______________________35

3.2.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ______________________35

3.2.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ............................................Error! Bookmark not defined.

3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ......................................................... 33

3.3.1. የመጻፍ ችሎታ ፈተና...........................................Error! Bookmark not defined.

3.3.2. የጽሁፍ መጠይቅ....................................................Error! Bookmark not defined.

3.4. የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ............................................................................. 34

3.5. የጥናቱ ሂደት .......................................................................................... 36

3.6. የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች....................................................................... 39

ምዕራፍ አራት................................................................................................ 40

4. የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ ......................................................... 40

4.1. የመረጃ ትንተና.......................................................................................... 40

4.2. የውጤት ማብራሪያ .................................................................................... 44

ምዕራፍ አምስት............................................................................................... 48

ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት ........ 48
5.1 ማጠቃለያ ........ 48
5.2 መደምደሚያ ........ 50
5.3 አስተያየት ........ 51
ዋቢ ጽሁፎች ........ 53
አባሪዎች ........ 58

# ምዕራፍ አንድ
# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት አላማ ተማሪዎችን በተለያዩ አውዶች በታላሚው ቋንቋ መገልገል ማስቻል ነው፡፡ ይህም በክፍል ውስጥ የሚኖረው የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎችን ባሳተፈ መልኩ የተለያዩ ልምምዶችን እንዲያደርጉና መረጃ እንዲለዋወጡ በማበረታታት ውጤታማ ይሆናል (Brown፣2004)፡፡ ከመረጃ መለዋወጫ መንገዶችም አንዱ መጻፍ ነው፡፡ የጽህፈት ተግባራት አጀማመር በርካታ ክርክሮች ከሚነሱበት ሂደት ይጠቀሳል፡፡ እንደ አብነት (2007 ዓ.ም.) እና ጌታቸው (2011 ዓ.ም.) እንደሚገልጹት፣ ደግሞ የመጀመሪያ ስርአተ ጽህፈት ፈጠራ እስከ አራተኛው ሺህ አመተ አለም ድረስ ይጠቀሳል፡፡ ቢሆንም፣ “ጽህፈት የቅርብ ጊዜ ባህላዊ እድገት ሲሆን የተከሰተው በላፉት አምስት ሺ አመታት ውስጥ” ነው (አብነት፣ 2007 ዓ.ም.)፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የጽህፈትን አጀማመር አስመልክቶ ቁርጥ ያለ ጊዜ መግለጽ የሚያስችል መረጃ አለመኖሩንና ጽሁፎች ተጽፈው በተገኙበት ጊዜ ላይ የሚኖረውን መስማማት ነው፡፡

ረጅም የታሪክ ሂደት አልፎ የመጣው ጽህፈት በ14ኛው ክፍለ ዘመን በእንግሊዝኛ ቋንቋ ፊደላት ተገኝተውለት ትኩረት እያገኘ መጣ፡፡ ይህም ዘመናዊው ተግባቦታዊ የመጻፍ ሂደት ረጅም ታሪክ አልፎ መምጣቱን ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ የመጻፍ ችሎታ አስፈላጊነት ትኩረት ካገኘ 200 መቶ አመታት ያህል ጊዜ ነው (Harmer፣2007)፡፡

በቋንቋ ትምህርት ታሪክ ከ1940ዎች በፊት የመጻፍ ችሎታ ትምህርት የሚመራበት ንድፈ ሐሳባዊ መሰረት ስላልነበረው የሰዋስው ትርጉም ዘዴ ማስተማሪያ አውድ እንጂ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ራሱን ችሎ በይዘትነት አይቀርብም ነበር (Richards, J.C.(1990)& Onozawa( 2010) ፡፡

እንደ Klark (2012) & Harmer (2007) ገለጻ፣ ከረጅም የታሪክ ሂደት በኋላ በ19ኛው ክፍል ዘመን የሰው ልጅ በፖለቲካው እና በቴክኖሎጂው እያደገና እየተራቀቀ ሲመጣ የመጻፍ ችሎታ ትምህርት ራሱን የቻለ የጥናትና የምርምር ዘርፍ እየሆነ መጣ፡፡

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የመጻፍ ችሎታ ትምህርት እንደ አንድ የትምህርት ዘርፍ ትኩረት እንዲያገኝ የስነልሳን፣ የስነ ልቦና ስነልሳን፣ አእምሮአዊ ስነ ልቦናና የማህበራዊ ስነልሳን ባለሙያዎች የምርምር ስራዎችን በመስራት በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ (Uso Juan, Martinez-Flor and Palmer-silveira, J.C (2006)፡፡ በተለይ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪ ያልሆኑ ተማሪዎች በአሜሪካና በሌሎች የትምህርት ተቋማት እየበዙ ስለመጡ ስልጠናዎችን ማዘጋጀት፣ የተለያዩ የምዘና ስርአቶችን መዘርጋት እና በቋንቋ መጻፍን የሚያስገድዱ ሁኔታዎች መፈጠራቸው ለዘርፉ ትኩረት ማግኘት በምክንያትነት ይጠቀሳሉ Clark, (2012).

Harmer, (1998) & Onozawa, (2010) የመጻፍ ችሎታ አስፈላጊና መሰረታዊ ችሎታ ነው፡፡ ይህም ችሎታው ከአፍላቂ ችሎታ ስር የሚመደብ እና ሰዎች ሃሳባቸውንና አመለካከታቸውን በጽሁፍ ለሌሎች የሚያካፍሉበት ነው (Spratt, (2005). ስለሆነም፣ የተግባቦት ማከናወኛ መንገድ የሆነው የመጻፍ ችሎታ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚኖረው የመማር ማስተማር ሂደት በተመረጡ የማስተማር ዘዴዎችና አቀራረቦች ሊተገበር ይገባል፡፡

የመጻፍ ችሎታ ትምህርት በትምህርትነት ይሰጥ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችና አቀራረቦች ቀርቧል (Richards, and Rodgers,(2002 ). Onozawa,(2010). በቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት ከ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በፊት የቋንቋ ትምህርት በልማዳዊ የማስተማር ዘዴ ይቀርብ ነበር (Richards, and Rodgers, (2002). በልማዳዊ ዘዴ (መምህር ተኮር) በክፍል ውስጥ በሚሰጠው ትምህርት የመማር ማዕከል፣ ተቆጣጣሪው፣ መሪው፣ ተሳታፊውና ተናጋሪው (ገለጻ ሰጪው) መምህሩ ሲሆን፣ ተማሪው ፍዝ፣ አድማጭ፣ የታዘዘውን ብቻ አድራጊ የሚሆንበት ዘዴ ነው፡፡

ልማዳዊ ዘዴ (መምህር ተኮር) የክፍል ውስጥ የመጻፍ ችሎታ ትምህርት አቀራረብ በውጤት ተኮር ላይ የተመሰረተ ነበር Kumaravadivelu, (2006). ውጤት ተኮር አቀራረብ በባህሪያዊ ስነልቦና ንድፈ ሃሳብ ላይ ተመስርቶ፤ የመጻፍ ችሎታ ትምህርት የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት በልማዳዊ ዘዴ ይተገበራል Silva, (1994). Hyland, (2003) ገለጻ፣

በዚህ ዘዴና አቀራረብ ለተማሪዎች ሞዴል በማቅረብ በዚያ ጽሁፍ መሰረት ተመሳሳይ የጽሁፍ ይዘት፣ የሃሳብ አደረጃጀት፣ የቃላትን አጠቃቀም፣ የሰዋስውና የአጻጻፍ ስርአት ተከትለው የመጨረሻውን ጽሁፍ እንደዲጽፉ ይጠየቃሉ Nunan, 1998፤ Moore, 2001. Kumaravadivelu, (2006). አመዛዘኑ በተማሪዎች ተጽፎ በቀረበው ጽሁፍ በቋንቋው ቅርጽና ህግ ላይ በማተኮር ትክክለኛውን የአጻጻፍ ስርአት እና የቋንቋ አጠቃቀም ብቃታቸውን መነሻ በማድረግ ችሎታቸውን ይፈትሻል ( Hyland, (2003).

እንደ ሚላዊት (2015) ልማዳዊ ዘዴ ተማሪዎችን የማያሳትፍ፣ ነጻነት የማይሰጥ፣ በቡድን ተግባራትን ለመፈጸም እድል የማይሰጥ፣ የተራክቦና የትግበራ ጉድለት ያለበት፣ ለመነጋገርና ለመወሰን እድል መስጠት የማይችልና ለመማርም ተነሳሽ የማያደርግ ዘዴ በመሆኑ በዘርፉ ምሁራን በማስተማር ዘዴዎች ላይ ተጨማሪ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡

ከ19ኛው ዘመን አጋማሽ ጀምሮ በቋንቋ ትምህርት ዘርፍ በማስተማሪያ ዘዴዎች ላይ በርካታ ጥናቶች በመደረጋቸው በስነ ትምህርቱ ዘርፍ የማስተማር ዘዴ ለውጥ መጥቷል፡፡ በተለይ ከ1950ዎቹ እስከ 1980ዎቹ ባለው ጊዜ ተጠንተው ከቀረቡ ዘዴዎች የአማራጭና ተግባቦታዊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥናቶች በስነ ትምህርታዊ ሂደት የማስተማር ዘዴን ከልማዳዊ (ከመምህር ተኮር) ወደ ተማሪ ተኮር (ተግባቦታዊ ዘዴ) እንዲሸጋገር አድርገዋል (Richards,and Rodgers, (2002).

በአማራጭና ተግባቦታዊ ዘዴዎች የመጻፍ ችሎታ የክፍል ወስጥ የመማር ማስተማር ሂደት በሂደት ተኮር አቀራረብ ላይ ይመሰረታል፡፡ ሂደት ተኮር አቀራረብ በግንባታዊያን ንድፈ ሃሳብ ላይ ተመስርቶ፣ የመጻፍ ችሎታ ትምህርት የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት በተግባቦታዊ ዘዴ ይተገበራል፡፡ መርሆው መጻፍ ሃሳብ ላይ የሚመሰረት ራስን ማግኛ ሂደት ሲሆን፣ ተማሪዎች (ጸሃፊዎች) ውስጣቸው ያለን ሃሳብና ስሜት የሚገልጹበት ነው (Onozawa, (2010)፡፡ በዚህ አቀራረብ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት በተማሪዎች ፍላጎትና በቡድን መማር ላይ ተመስርቶ፤ ከመጨረሻው የጽሁፍ ውጤት ይልቅ ወደ ውጤት በሚያንደረድረው የመጻፍ ሂደታዊ ተግባራት ላይ ያተኩራል፡፡

Kroll, (1990). ጠቅሰው እንደገለጹት፣ ሂደታዊ አቀራረብ አንድን ጽሁፍ እንደማሳኪያ መንገድ የሚታይ ሲሆን፣ በውስጡ ማቀድን፣ መከለስን፣ ማረምን፣ ወዘተ ያካትታል፡፡ ስለዚህ፣ በሂደት ተኮር አቀራረብ መምህራን ተማሪዎቻቸው የመጻፍ ሂደት ደረጃዎችን በቡድን እንዲተገብሩ ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል (በድሉ፣2007 ዓ.ም፤ ማረው፣2007 ዓ.ም.፤ Silva,(1994) .Hyland, (2003).

ተግባቦታዊ ዘዴዎች በባህርያቸው በክፍል ውስጥ በሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች መማራቸውን በኃላፊነት እንዲመሩ፣ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣ ከውድድር ይልቅ በመተባበር እንዲማማሩ፣ ተግባቦታዊና ማህበራዊ ክሂል እንዲያዳብሩ፣ በመካከላቸው በሚኖረው ተራክቦ ጤናማ የመማር ሁኔታ እንዲፈጥሩና በመማር ሂደት ተነሳሽ እንዲሆኑ ያስችሏቸዋል Richardes,andRodgers,(2010& Kumaravadivelu,(22006)፡፡ ስለሆነም፣ መምህራን የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና ተነሳሽነታቸውን ለማሳደግና የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ አቀራረቦችን አዋህዶ መጠቀምና በተማሪዎች ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ተግባቦታዊና ትብብራዊ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ሊተገበሩ ይገባል፡፡

በመጻፍ ችሎታ ትምህርት የክፍል ውስጥ ትግበራና በመጻፍ ተነሳሽነታቸው ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍና ለውጤታማነቱ በማስተማሪያ ዘዴዎች፣ ስልቶችና አቀራረቦች ላይ በተለያዩ ተመራማሪዎች በተደረጉ ጥናቶች ንድፈ ሃሳባዊ ለውጦች ታይተዋል፡፡ ከእነዚህም አንዱ ትብብራዊ ዘዴ ነው (Richardes, and Rodgers,(2002). Cohen, (1994). እንደሚገልጹት፣ ትብብራዊ ዘዴ ልማዳዊ (መምህር ተኮር) ዘዴን በመተካት የሚታይ ለውጥ ያመጣ ጽንሰ ሃሳብ ሲሆን፣ በመጻፍ ችሎታ ትምህርትና በመጻፍ ተነሳሽነት ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ ለልማዳዊ ዘዴ በአማራጭነትም ቀርቧል፡፡ ትብብራዊ ዘዴ በመጻፍ ችሎታ ትምህርት በክፍል ውስጥ በሚኖረው የመማር ማስተማር ሂደት የትምህርቱን ይዘት በተለያዩ የማስተማሪያ አቀራረቦች፣ ብልሃቶችና ስልቶችን አዋህዶ ማቅረብም ያስችላል፡፡

ትብብራዊ ዘዴ በተማሪዎች መካከል ማህበራዊ ተራክቦን በመፍጠር፣ በቡድን ላይ የተመሰረተ ተግባራዊ ልምምድ በመስራት በመማር ሂደት የሚገጥማቸውን ችግር በጋራ የመፍታት ችሎታ የሚያዳብሩበትና ተጨባጭ የሆነ የጋራ ግብ የሚያሳኩበት ዘዴ ነው Li, M. P.& Lam,B.H.(2013).

Shran, (2010). እንደሚገልጹት፣ በትብብራዊ ዘዴ የመማርን ሃሳብ በማመንጨት ረገድ ቀዳሚው ሰው አሜሪካዊው ጆን ዲወይ ናቸው፡፡ ዘዴው በ1930ዎቹና በ1940ዎቹ በአሜሪካ ሀገር በከፍተኛ ሁኔታ ሊዳብር ችሏል፡፡ የበለጠ ትኩረት ያገኘውና ከፍተኛ የምርምር መስክ እየሆነ የመጣው በ1970ዎቹ እንደሆነ ይገልጻሉ Silva,Hurley,and Chamberlain, (2003). እንደ Silva, (2003). and Gillies, (2016). ገለጻ፣ የምርምር ውጤቶች እንደሚያሳዩት ይህ የማስተማር ዘዴ በተለያዩ ሀገራት በስፋት ተቀባይነትን ያገኘ፣

በተማሪዎች መካከል ማህበራዊነትን ያጎለበተ፣ ተማሪዎችን በመማር ሂደት ተነሳሽ ያደረገ፣ በሁሉም የትምህርት እርከኖች እና አይነቶች ውጤታማ የሆነ ነው፡፡
ስለሆነም ይህ ጥናት የተግባቦታዊ አቀራረብ መሰረት ካላቸው የቋንቋ ማስተማር ዘዴዎች መካከል አንዱ የሆነው ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና ተነሳሽነታቸውን ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ በመመርመር አንዳች ውጤት (ድምዳሜ) ላይ ደርሷል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በሀገራችን ስርአተ ትምህርት ውስጥ ከተካተቱ የትምህርት አይነቶች መካከል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንዱ ነው፡፡ ዋና አላማውም ክሂሎችን ከማጎልበት አኳያ ተማሪዎች ጥሩ አድማጭ፣ ጥሩ ተናጋሪ፣ ጥሩ አንባቢና ጥሩ ጸሀፊ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡ እንዲሁም የስነ ጽሁፍ እና የስነ ልሳን እውቀቶችን ማዳበር ሌላው ዋና የቋንቋ ትምህርት አላማ ነው፡፡
የመጀመሪያው ትብብራዊ ዘዴ የመጻፍን ችሎታ ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ የተመለከቱ ጥናቶች (ዘነበች፣ 2011 ዓ.ም.፤ Astaina, (2011) and Milawati, (2015) .ናቸው ፡፡ ከነዚህ ምዘነበች(2011) ዓ.ም.እና Milawati, (2015). የትብብራዊ መማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለውን ሚና የፈተሹ ናቸው፡፡ በጥናታቸው ተማሪዎች በመጻፍ ችሎታ ትምህርት የክፍል ውስጥ ትግበራ ላይ ያላቸው ተነሳሽነት ማነስ፣ በመጻፍ ሂደት ሃሳብ ማመንጨትና የሃሳብ እጥረት እንዲሁም፣ በሰዋስው አወቃቀር ላይ ያተኮረ ጥናት አድረገው ያገኙት ውጤት ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ለማሻሻል፣ ሃሳብ የማመንጨትና የሰዋስውን እውቀት ለማሳደግ ተመራጭና አዎንታዊ ፋይዳ ያለው መሆኑን አረጋግጧል፡፡
ሁለተኛው ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ ከልማዳዊ (መምህር ተኮር) ዘዴ ጋር በንጽጽር የፈተሹ ጥናቶች (ሙሀሙድ፣2016፤ Bawn,(2017).ናቸው፡፡ ሙሀመድ (2016) የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል በትብብራዊ ዘዴ ማስተማር በሚል ርዕስ ዝቅተኛ የመጻፍ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማብቃት ታስቦ ባካሄዱት ጥናታቸው ትብብራዊ ዘዴ ከልማዳዊ ወይም ከመምህር ተኮር ዘዴ በተሻለ ሁኔታ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ከማሻሻል ረገድ ውጤታማ ዘዴ እንደሆነ አረጋግጠዋል፡፡ Brown, (2007). ደግሞ ትብብራዊ ዘዴ ለመማር ማስተማርና በክፍል ውስጥ ለሚኖረው የትግበራ ሂደት ያለውን ሚና መርምረዋል፡፡ ጥናቱም በልማዳዊ እና በትብብራዊ ዘዴ ማስተማር መካከል ባለው ውጤታማነት ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ ውጤቱም

ትብብራዊ ዘዴ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ የሚያስችል ተግባቦታዊ ዘዴ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ በሁለቱ ዘዴዎች መካከልም ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ አመልክቷል፡፡ ሶስተኛው ትብብራዊ ዘዴ ተነሳሽነትን ለማሳደግ ካለው ፋይዳ አኳያ ከተደረጉ ጥናቶች Quirey,(2015). ተጠቃሽ ነው፡፡ በትብብራዊ ዘዴ ብልሃቶች ላይ የተመሰረተ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት የቋንቋ ተማሪዎችን የመማር ተሳትፎ ከማሳደግ አኳያ ያለውን ሚና የፈተሸ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ውጤትም የተማሪዎችን ተጋግዞ በመማር ላይ ያላቸውን ተሳትፎና ተነሳሽነት በማሳደግ በኩል ትብብራዊ ዘዴ የተሻለ እንደሆነ አረጋግጠዋል፡፡

ይህን ሃሳብ በማጠናከር Silba (1994) እንደገለጹትም፣ በመጻፍ ችሎታ ትምህርት ውስጥ እንደ ችግር ከሚነሱ አንዱ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ የማስተማር ዘዴ በመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎችን መጻፍ ተነሳሽ የማድረግ ያለማድረግና እንዲሁም የመጻፍ ችሎታን የማሻሻል ያለማሻሻል ተጽዕኖ አለው፡፡ ስለዚህ ዘዴውና የትግበራ ብልሃቱ ማህበራዊ ተራክቦ ላይ የሚያተኩር፣ ተግባቦታዊ መሰረት ያለው፣ ማህበራዊ ክሂልን የሚያሳድግ እና አዎንታዊ ግንኙነትንም የሚያጎለብት ሊሆን ይገባል፡፡

እነዚህ የቀደምት ጥናቶች ሲታዩ ይህ ጥናት ይዞት ከተነሳው ርዕስ አኳያ የሚከተሉ ክፍተቶች አሏቸው፡፡

1. ትብብራዊ ዘዴ የመጻፍ ችሎታ ከማጎልበት አኳያ ያለው ሚና በተናጥል የተጠና ቢሆንም፣ ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን ለማጎልበት ያለውን ሚና በተመለከተ የጥናት ርዕስ ተሰጥቶት በተቀናጀ መልኩ አልተጠናም፡፡

2. ከተዳሰሱት ጥናቶች በአጠቃላይ በሀገር ውስጥና በውጭ ቋንቋ የተጠኑ ቢሆንም በሀገር ውስጥ ከመጻፍ ተነሳሽነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ጥናቶች ያለመገኘት እንደ ክፍተት ታይቷል፡፡

3. በቀደምት ጥናቶች ላይ ተመራማሪዎች በተመሳሳይ ርዕስ ምርምር ቢደረግ ተማሪዎች ላይ የተሻለ ግንዛቤ በመፍጠር የመጻፍ ችሎታቸውንና የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን የበለጠ ማሳደግ እንደሚቻል የተሰጡ አስተያየቶችም ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡፡

በተጨማሪ በትምህርት ቤቶች የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ያለበት ነባራዊ ሁኔታ ተተኩሮበታል፡፡ አጥኚው ከመምህራን ጋር በሚደረጉ ኢ-መደበኛ ውይይቶች፣ በትምህርት ክፍሉ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ በክፍል ውስጥ የሚኖረውን የመማር ማስተማር ሂደት

አተገባበር ለመፈተሽ በሚደረጉ የውስጥ ሱፐርቪዥን (ምልከታዎች) እና በምልከታው ላይ በተደረጉ የጋራ ውይይቶች ወቅት ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ የብዙ መምህራን ሃሳብ መሆኑን አስተውሏል፡፡

በመሆኑም፣ ከመምህራን፣ ከክፍል ውስጥ ምልከታ ከተገኘው ውጤትና ከላይ በተዳሰሱት ጥናቶች ካሉት ክፍተቶች በመነሳት የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታ እና የመጻፍ ተነሳሽነት ለማጎልበትና የሚስተዋሉ ችግሮችን ከመቅረፍ አንፃር ትብብራዊ ዘዴ ፋይዳ ይኖረው ይሆንን? የሚለው መሰረታዊ ጥያቄ የዚህ ጥናት ዋና አነሳሽ ምክንያት ሆኗል፡፡ ይህም ጥናት የቀረቡ ክፍተቶችን መነሻ በማድረግ ተግባቦታዊ መሰረት ካላቸው የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች አንዱ የሆነው ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነትን ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ መርምሯል፡፡ በዋናነት ይህ ጥናት የሚመልሳቸው ጥያቄዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታ ለማጎልበት ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው?

2. ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ለማሳደግ ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው?

## 1.3. የጥናቱ አላማዎች

የዚህ ጥናት አቢይ አላማ በትብብራዊ ዘዴ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ ከዚህ አቢይ አላማ በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ይኖሩታል፤

1. የትብብራዊ ማስተማርያ ዘዴው የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታ ዝምድና መመርመር

2. የትብብራዊ ማስተማርያ ዘዴው የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ማሳደግ መቻሉን መፈተሽ ፤

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታዎች

በትብብራዊ ዘዴ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ የመረመረው ጥናት ሲጠናቀቅ የሚገኘው ውጤት የሚከተሉት ፋይዳዎች ይኖሩታል፡፡

የመጀመሪያው የጥናቱ ውጤት በአማርኛ የመጻፍ ችሎታ ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብና ተነሳሽነት ከማጎልበት አኳያ ባለው ፋይዳ ላይ የትብብራዊ ዘዴን የትግበራ ብልሃቶችንና ቴክኒኮችን በማስተዋወቅ ለመምህራንና ተማሪዎች የተሻለ ግንዛቤ ይፈጥርላቸዋል፡፡

ሁለተኛው ለመርሃ ትምህርትና ለማስተማሪያ መሳሪያ አዘጋጆች ትብብራዊ ዘዴ በመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት መጎልበት ያለውን ፋይዳ በመረዳት በመርሃ ትምህርቱ አነዳደፍና በማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት ሂደት በትብብር ለሚከናወኑ ተግባራት ትኩረት እንዲሰጡ ያስችላቸዋል፡፡

በተጨማሪ በመጻፍ ችሎታ ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ፣ በማስተማር ዘዴውና ተነሳሽነት ዙሪያ ባሉ ክፍተቶች ላይ በቀጣይ ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ አጥኚዎች መነሻ ይሆናል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ የተካሄደው በ2015 ዓ. ም. በደቡብ ምዕራብ ክልል በቤንች ሸኮ ዞን ካሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በቢፍቱ ከተማ አስተዳደር በአመቺ ንሞና በተመረጠው በቢፍቱ ሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቤትና በትምህርት ቤቱ ካሉ የክፍል ደረጃዎች በዘጠነኛ ክፍል ላይ ነው፡፡ በዘጠነኛ ክፍል ካሉ አስር መማሪያ ክፍሎች በአንድ መምህር የሚማሩ አራቱ ክፍሎች በአመቺ ንሞናና ከአራቱ ክፍሎች ሁለቱ በቀላል ዕጣ ንሞና ተመርጠዋል፡፡ ቀሪ የዘጠነኛ ክፍል ምድቦችንና ሌሎች የክፍል ደረጃዎችን አልተመለከተም፡፡

የመጻፍ ችሎታ በባህሪው ባለ ብዙ ክሂል ነው፡፡ በውስጡም በርካታ ንዑሳን ችሎታዎችን (የቃላት አጠቃቀም፣ የአጻጻፍ ስርአት፣ የሃሳብ አደረጃጀትና ሰዋስው) ያካተተና ውስብስብ በመሆኑ በጥልቀት አልፈተሸም፡፡ ነገር ግን የክፍል ውስጥ የትግባራ ሂደቱና አመዛዘኑ በእነዚህ ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ውስንነት

የትብብራዊ ዘዴ መፃፍን ማስተማር የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለውን ሚና በቢፍቱ ሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት የመረመረው ይህ ጥናት በጥናቱ ሂደት ሊፈጠሩ ይችላሉ፤ ተብለው የታሰቡ የወጭ ተጽዕኖዎችን ለመቆጣጠር በጥናቱ ወቅት የመማር ማስተማር

ሂደቱ በመደበኛው ክፍለ ጊዜና በተጨማሪ በተቃራኒ ፈረቃ የተያዘውም ክፍለ ጊዜ ለሁለቱም ቡድኖች እኩል እንዲተገበርና ለፍትነት

ቡድኑ የሚቀርበው የማስተማሪያ ብልሃት ዕቅድ በክፍለ ጊዜ መጨረሻ በአዋኙው እንዲሰበሰብ ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1. የ መጻ ፍ ችሎታ ትምህርት

የመጻፍ ችሎታ በቋንቋ ትምህርት እንዲዳብር ከሚጠበቀው መሰረታዊ ጉዳይ አንዱና ዋነኛው ሲሆን፣ በንግግር የሚተላለፍን መልዕክት እይታዊ በሆኑ ምልክቶች በመጠቀም ተማሪዎች በተሳካ መንገድ ሃሳባቸውን በጽሁፍ አማካይነት ማስተላለፍ እንዲችሉና እንዲግባቡ ማብቃት ነው፡፡ የአምላክስራ (2008 ዓ.ም.፤ Bayren,(1988). ጠቅሰው) እንደገለጹት፣ የመጻፍ ችሎታ ለሀሳብ ልውውጥ፤ አዳዲስ እውቀትንና ልምድ ለማግኘት፣ የሚሰማቸውን ሃሳብ በትክክል ለመግለጽ ወይም በቋሚነት ተመዝግቦ እንዲቆይ ለማድረግ፣ ንቁ ተሳታፊ ለመሆንና ትምህርት ቀመስ በሆነ ማህበረሰብ ውስጥ በተለያዩ ተግባራት ለመሳተፍ ወዘተ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ የትምህርት ትግበራውም ተማሪዎች ይህን ተረድተው በመጻፍ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ይጠይቃል፡፡

የመጻፍ ችሎታ ትምህርት ትኩረት እንዲያገኝ በተለያዩ ምሁራን ንድፈ ሃሳባዊ ጠቀሜታ ያላቸው ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ እነዚህ የመምህራንን የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲደግፉ የተጠኑ ሲሆኑ፣ የመጻፍ ችሎታ ትምህርት ንድፈ ሃሳቦች ትኩረትም ጽሁፍ ተኮር፣ ጸሃፊ ተኮርና አንባቢ ተኮር ናቸው Hylad,2007፣2008). Albesher,(2012).Raimes,(1993). ጠቅሰው እንደገለጹት፣ ደግሞ ንድፈ ሃሳቦቹን ከመጻፍ ችሎታ ትምህርት አቀራረቦች ጋር በማዋሄድ ውጤት ተኮር (ቅርጽ ተኮር)፣ ሂደት ተኮር (ጸሀፊ ተኮር) እና ዘወግ ተኮር (አንባቢ ተኮር) በማለት ይከፍሏቸዋል፡፡ Johnson, (1994)and Hyland, (2011). ዋቢ አድርገው እንደገለጹት ትኩረት የሚደረግባቸው ንድፈ ሃሳቦች መረጃ አድራሽ ጸሀፊው፣ መረጃ ተቀባዩ አንባቢው፣ መረጃው የሚመሰረትበት ነባራዊው እውነታ እና መልእክቱ የተመሰረተበት የቋንቋ ምንጭ ናቸው፡፡ በዚህ ጽሁፍ ከጥናቱ አላማ አኳያ ትኩረት የሚደረግባቸው ጸሃፊና አንባቢ ናቸው፡፡

የመጀመሪያው የመጻፍ ችሎታ ትምህርት ንድፈ ሃሳብ ጸሃፊን የሚመለከት (መጻፍ ሂደት ተኮር) ነው፡፡ የንድፈ ሃሳቡ ትኩረት ጸሃፊው ሃሳብ አመንጭ፣ አዋቃሪና መልእክት

አስተላላፊ ስለሆነ ከጽሁፉ ቅርጽ (መዋቅር) ይልቅ ጸሃፊው ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ይህንን ሃሳብ በማጠናከር ጆንስ (1994) እና ሃይላይ (2011 ዓ.ም.) እንደገለጹት፣ ጸሃፊው
ጽሁፍ በሚያዘጋጅበት ጊዜ ሃሳብ ለማመንጨት እና ለመጻፍ ሂደታዊ የመጻፍ ደረጃዎችን ይጠቀማል፡፡ ትግበራውም ሂደታዊ አደረጃጀቱ ላይ ያተኩራል፡፡

Johnson, (1994)and Hyland, (2007.2008). እንደገለጹት፣ ጸሃፊዎች ከሚኖራቸው ንድፈ ሃሳባዊ አተያይ በሁለት ክፍሎች ይከፈላሉ፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ራስን መግለጽ ሲሆን ሁለተኛው ሂደታዊ (አእምሯዊ) ነው፡፡

በዚህ ንድፈ ሃሳብ የመጀመሪያው ክፍል ጸሃፊንና ፈጠራዊ ገለጻን ይመለከታል፡፡ የዚህ አተያይ ተከታዮች እንደ Elbow, (1998). በብዙ የመጻፍ ችሎታ ትምህርት አቀራረብ በክፍል ውስጥ በሚኖረው የመማር ማስተማር ሂደት የመምህራን ግብ ተማሪዎች ውስጣቸው ያለውን ችሎታ ተጠቅመው የራሳቸውን ሃሳብ እንዲያመነጩ እና ተከታታይነት ባለው ሁኔታ እንዲጽፉ ነው፡፡ በአተያዩም የክፍል ውስጥ ትግበራ የሚደራጀው በተማሪዎች ልምድና አስተያየት ሲሆን፣ መጻፍ ፈጠራዊ ራስን ማግኛ ስራ ተደርጎ ይወሰዳል Hidi,s,&Boscolo,j(2007). Hyland,( 2011). ይህም የሚደረገው ተማሪዎች በሚጽፉበት ጊዜ የራሳቸውን መረዳት እንዲገልጹ ማበረታታት፣ የማሰብ ጊዜ ማመቻቸት፣ ውጤታማ የሆነ በሃሳብ ትስስር ላይ የተመሰረተ ጽሁፍ እንዲጽፉና በራሳቸው ገለጻ እንዲረኩ ለመርዳት ነው፡፡ ምክንያቱም መጻፍ ሂደታዊ እድገት ነው፡፡

ሁለተኛው አተያይ ጸሃፊዎችንና የመጻፍን ሂደት (አእምሯዊያንን) የሚመለከት ነው፡፡ ይህም በመጻፍ ሂደት አንድ ጸሃፊ (ተማሪ) ምን አይነት የአጻጻፍ ዘዴን መከተል እንዳለበት የሚጠቁም በጣም ተፈላጊ አተያይ ነው፡፡ ብዙ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ከሂደታዊ የመጻፍ ብልሃቶች ጋር ቅርበት በመፍጠር የመጻፍ ብልሃቶችን ለመጠቀም አእምሮን ማዘጋጀትን፣ ተግባራትን ማከናወን፣ የአቻ እና መምህራን ምጋቤ ምላሽ መስጠትንና በርካታ ረቂቆችን እንዲጠቀሙ የሚያደርጉበት ነው Hyland,( 2008). ይህ ጸሃፊዎችንና የመጻፍን ሂደት (አእምሯዊያንን) አተያይ ላይ የተመሰረተው ቡድን እንደ Johnson, (1994). አእምሯዊያን ወይም መጻፍን እንደ ችግር መፍታት የሚመለከቱ ናቸው፡፡ እንዲሁም፣ በፍላወር "ለመጻፍ ችግር ፈቺ ብልሃቶች" በሚለው መጽሃፋቸው አእምሯዊያን ንድፈ ሀሳባዊ አተያያቸው ማሰብና ሂደት በሚሉ ቃላት ላይ ይመሰረታል፡፡ አላማውም የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ በማዳበር እንዲጽፉ ማስቻል ነው Johnson,( 1994).

የአእምሯዊያንን ንድፈ ሃሳብ ያስተዋወቁት ሃይስና ፍላወር ሲሆኑ፣ መጻፍ በአእምሮ ውስጥ መረጃ ማስቀመጥን (ማቀድንና ሃሳብ ማፍለቅን)፣ ማደራጀትን (የማሰብ ክሂሎችን መጠቀምን) እና ማስተላለፍ የሚሉ ተግባራትን የያዘ የማሰብ ውጤት ነው Johnson,(1994),Clark, (2012). ስለዚህ ተማሪዎች መጻፍ የሚማሩት፣ ሃሳብ የሚገልጹበት እና ችሎታ የሚያዳብሩበት ሂደት እንደሆነ ሊገነዘቡ ይገባል፡፡

መጻፍ የፈጠራ ሂደት ነው፡፡ ተማሪው የቋንቋውን የሰዋስውና አጻጻፍ ስርአት ጠብቆ፣ ይዘቱንና ተገቢ በሆነ የሃሳብ አደረጃጀት ተጠቅሞ በውስጡ ያለውን ሃሳብ የሚገልጽበት፣ ራሱን የሚያገኝበት፣ መረጃ የሚያስተላልፍበትና አንባቢን የሚያሳምንብት ሂደት ነው Troyka,(2010).

ሁለተኛው የመጻፍ ችሎታ ትምህርት ንድፈ ሃሳብ አንባቢ ተኮር ነው፡፡ ጸሃፊ ተኮር ንድፈ ሃሳብ ይዘትን እንደ ጽሁፍ አውድ የሚመለከት እና ጸሃፊው ምን ማሰብ እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ነገር ግን አንባቢ ላይ ያተኮረው ንድፈ ሃሳብ ከተለመደው የአጻጻፍ ሁኔታ ላቅ ወዳለው ጸሃፊው አንባቢን እያሰበ የጽሁፉን ይዘት እያስፋ እንዲሄድ ያስገነዝባል Hyland,( 2008).

Johnson,(1994). Clark,(1978). and Flower(1979) እንደገለጹት፣ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ባደረጉት ጥናታቸው የመጻፍን ተግባር ግለሰባዊ ብቻ ከማድረግ አእምሯዊ ሂደት በመጠቀም ከጸሃፊ ተኮር ወደ አንባቢ ተኮር ንድፈ ሃሳብ እንዲሸጋገር አድርገዋል፡፡ በመሆኑም አንድ ጸሃፊ (ተማሪ) ጽሁፉን መጻፍ በሚያስብበት ጊዜ የአንባቢን ስሜትና ፍላጎት በመረዳት መጻፍ አለበት፡፡ ስለዚህ እንደ Johnson, (1994). and Hyland, (2011). ገለጻ በመጻፍ ችሎታ ትምህርት በተጽእኖ ፈጣሪነቱ የሚነሳው አእምሯዊያን ንድፈ ሃሳብ መጻፍ የተወሳሰበ አእምሯዊ ሂደትን የሚጠይቅ ቢሆንም ተማሪዎች ሂደቱን ብቻ ከመከተል መልዕክቱ የሚተላለፍለትን አንባቢ ሊረዱ ወይም ትኩረት ሊያደርጉለት ይገባሉ ፡፡

በአጠቃላይ አንድ የመጻፍ ሂደት በጸሃፊው፣ በሚተላለፈው መልዕክትና አንባቢ ላይ ያተኩራል Brereton,(1995). ስለዚህ ተማሪዎች የራሳቸውን ሃሳብ የማመንጨትንና የመግለጽ ችሎታን እውቀት ተጠቅመው፣ አአምሯዊ የመጻፍ ሂደታዊ አወቃቀሮችን ተከትለው፣ አንባቢ ሊረዳው በሚችለው መልኩ እንዲጽፉ ሊበረታቱ ይገባል፡፡

## 2.2. የመጻፍ ችሎታና ተነሳሽነት

የመጻፍ ችሎታ ወስብስብ እና በጣም ጠቃሚ ችሎታ ነው፡፡ ምክንያቱም መረጃን፣ ገለጻን፣ አስተያየትን፣ እምነትን፣ ስሜትን፣ ክርክርንና ንድፈ ሃሳቦችን በቋሚነት መዝግቦ ማቆያ ነው፡፡ ይህ ችሎታ አንድ ጸሃፊ ሃሳቡን በቃላት አማካይነት ትርጉም ባለው ቅርጽ ተገቢውን መልእክት ለማስተላለፍ የሚረዳ ልዩ ችሎታ ነው፡፡ በውስጡ የተማሪዎችን በራስ መተማመን፣ የመረዳት ችሎታን፣ የመጻፍ ቅልጥፍናንና ፈጥረው የመጻፍ ችሎታን ማዳበር ያካትታል Saban,(2011).

እንደ Banget,and Drawuns, እና ሌሎች (2004) ገለጻ፣ መጻፍ አንዱ የመግባቢያ መንገድ ስለሆነ እያንዳንዱ ተማሪ ለተሳካ ተግባቦት የማሰብ ብቃትና የሰዋስው ችሎታ ሊኖረው ይገባል፡፡ ምክንያቱም ተማሪው ጥሩ የመጻፍ ችሎታ ከሌለው የማሰብ ችሎታን በማሳደግ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖን ይፈጥራል Hillocks,(2006). ስለዚህ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚኖረው የመማር ሂደት ትኩረት ሰጥተውና ተነሳሽ ሆነው ሊማሩ ይገባል፡፡

ተነሳሽነት በተማሪዎች ወጤት ላይ የራሱ ተጽዕኖ አለው፡፡ ተማሪዎች ለመጻፍ ችሎታ ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነት ከፍተኛ ከሆነ በክፍል ውስጥ ለሚኖረው የተግባር አፈጻጸም ዝግጁ ይሆናሉ፤ የመማር አላማቸውም ይሳካል፡፡ ነገር ግን ተነሳሽነታቸው ዝቅተኛ ከሆነ በክፍል ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመፈጸም አይዘጋጁም፤ፈቃደኛም አይሆኑም፡፡ እንዲሁም እነዚህ ዝቅተኛ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች መጻፍን መማር ሲያስቡ ያልተገባ ጭንቀት፣ ዝቅተኛ ግላዊ ብቃት፣ የራስን መማር የመምራት አቅም እና በራስ የመወሰን ችሎታ ማነስ ይታይባቸዋል Pajares,(1996).

ተነሳሽነት ግብ ተኮር ነው፡፡ ተነሳሽነት አንድን ግብ ለማሳካት የሚያነቃቃ፣ አቅጣጫ የሚያመለክት፣ ቀጣይነት ላለው የተግባር አፈጻጸም የሚያዘጋጅና ግፊት የሚያደርግ ውስጣዊ ስሜት (ባህሪ) ነው Harmer,(1991)&Pajares,(1996). ይህም የሚያመለክተው ተነሳሽነት ከመማር ማስተማር ሂደትም ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው መሆኑን ነው፡፡

ተነሳሽነት ካለው ባህሪ የተነሳ ውስጣዊ እና ውጫዊ ተብሎ ይከፈላል፡፡ ውስጣዊ ተነሳሽነት በአእምሯዊያን ንደፈ ሃሳብ ላይ የሚመሰረት አንድ ግለሰብ (ተማሪው) አንድን ተግባር ለመፈጸም ካለው ውስጣዊ ፍላጎት፣ እምነት፣ ዋጋ እና ከተግባር ጠቋሚነት የሚመነጭ ተፈጥሯዊ ፍላጎት (ውስጣዊ እርካታ) ነው፡፡ ውጫዊ ተነሳሽነት በባህሪያዊያን ንድፈ ሃሳብ ላይ የሚመሰረት የአንድ ግለሰብ (ተማሪ) የተግባር አፈጻጸም በማትጊያ ወይም በማነቃቂያ

ተጽዕኖ ስር የሆነ ተነሳሽነት ነው፡፡ ይህም ውጫዊ ተጽዕኖ ከመምህራን፣ ከቤተሰብ እና ከቀጣሪ ተቋም ይደርሳል Hancock,(2004) Raimes(2009). እንደ Bandura, (1997). ገለጻ፣ ተነሳሽነት በውስጡ ግላዊ ብቃትን (ውጤታማነትን)፣ አመለካከትን፣ እምነትንና ግብ ያካትታል፡፡ ስለዚህ ተማሪው ጥሩ ጸሃፊ ለመሆን ተነሳሽነቱ ሊያድግና በወስጡ ጠንካራ እምነት ሊፈጠርለት ይገባል፡፡ ይህም ከተማሪዎች ስነልቦናዊ ሁኔታ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡

ከላይ የተነሱ ሃሳቦችን በመሰብሰብ Hidi,s.&Boscolo, (2007). ተነሳሽነት ግላዊ ብቃት፣ ግላዊ መረዳት እና ግለ መር የሚባሉ ስነ ልቦናዊ ገጽታዎች እንዳሉት ይገልጻሉ፡፡ ግለ ብቃት ከባንዱራ ማህበራዊ ግንዛቤ ንድፈ ሃሳብ አኳያ ለሰው ባህሪ ጥሩ ተንባይ የሆነ የተነሳሽነት ገጽታ ነው Bandura,(1997). ተማሪዎች ግለ ብቃታቸው እየጨመረ የሚመጣ ከሆነ በመማር ሂደታቸው ውጤታማ ይሆናሉ፡፡ በአንጻሩ ግለ ብቃታቸው ዝቅተኛ ከሆነ የመማር ውጤታቸውም እየቀነሰ ይመጣል፡፡ ዝቅተኛ ግለ ብቃት ፍርሃትን ይፈጥራል፤ አልችልምን ያመጣል፤ በመጨረሻ የመማርን አላማ ያበላሻል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ይህን ገጽታ ማሳደግ እንዲችሉ የመጻፍ ችሎታ ትምህርት የመማር ማስተማሩን ሂደት በትብብራዊ ዘዴና በትግበራ ብልሃቶቹ ማስደገፍ ያስፈልጋል፡፡

ግላዊ ብቃት አንድን ተግባር ለመፈጸም ባለ እምነትና አቋም ላይ ስለሚመሰረት በግላዊ መረዳት እና የራስን መማር ተቆጣጥሮና አየገመገሙ በመምራት ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥር የስነ ልቦናዊ ተነሳሽነት ገጽታ ነው Hidi,s.&Boscolo,(2007). ስለሆነም፣ እነዚህ ገጽታዎች ከተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ትምህርት ጋር ቀጥተኛ ትስስር ስላላቸው ትኩረት በመስጠት የተማሪዎችን ተነሳሽነት ማሳደግ አስፈላጊ ነው፡፡

## 2.3 በትብብራዊ ዘዴ ማስተር

ከ1970ዎቹ ጀምሮ የመማር ማሰተማር አቀራረብ ከልማዳዊ (መምህር ተኮር) ወደ ዘመናዊው ወይም ተማሪ ተኮር ዘዴ የተሸጋገረበት እና በትብብራዊ ዘዴ ማስተማር አውቅና እያገኘና እያደገ የመጣበት ጊዜ ነው Sharn,& (2010). Gils,( 2016). ትብብራዊ ዘዴ ሂደታዊ ትምህርት (መማር) ላይ በማተኮር በተማሪዎች መካከል ማህበራዊ ግንኙነትን ለማጎልበት በሁሉም የክፍል ደረጃዎችና የትምህርት አይነቶች የሚተገበር ከተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች አንዱ ነው Silva,&Chamberlain, (2003).

በትብብራዊ ዘዴ ማስተማር አመንጭነቱ የሚታወቀው በስነ ትምህርቱ ዘርፍ ሊቅ የሆኑ ጆን ዲወይ ሲሆኑ፣ ፍልስፍናው የተመሰረተው ትምህርት ቡድናዊነት ላይ የተመሰረተና የተማሪዎችን ተሳትፎ ማእከል ያደረገ እንዲሆን በማሰብ ነው፡፡ እንደ ጆን ዲወይ ገለጻ፣ ትምህርት አሳታፊነትን የሚያበረታታ፣ ሃላፊነት የሚሸከምና ነጻነት የሚሰማውን ዜጋ ወይም ማህበረሰብ መፍጠር በመሆኑ ከእለት ተእለት ህይወታዊ እንቅስቃሴ ተለይቶ አይታይም Sharan,( 2010).

ትብብራዊ ዘዴ አዲስ ጽንስ ሃሳብ ባይሆንም በ19ኛው ክፍል ዘመን መጀመሪያዎቹ የታወቀና እንደ አንድ የመማር ማስተማር ዘዴ የበርካታ ምርምር ሰዎችን ቀልብ መሳብ ጀመረ፡፡ ጥናታቸውም ከስነ ትምህርት ውጤታማነት፣ ማህበራዊ ተራክቦን ከመፍጠር፣ አእምሯአዊ እድገትን ከማምጣት፣ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተነሳሽነትን ከመፍጠርና ለትምህርት ቤቶች አደረጃጀት ካለው ሚና አኳያ ሲፈተሽ ትብብራዊ ዘዴ የተሻለ ማስተማሪያ ዘዴ ነው Sharan,( 2010) Samadiyn,(2014).

ትብብራዊ ዘዴ አላማውን (ትምህርታዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ ግብ ለማሳካት) በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከሚኖረው ቡድናዊ ተራክቦ የሚገኘውን እውቀት ለማህበራዊ እና ትምህርታዊ ልምድ ማግኛ ያደረገ ሲሆን፣ በተማሪዎች መካከል ተራክቦን በማሳደግ የሚገኘውን ግብአት (እውቀት) መጠቀም የሚያስችል አውድ የሚፈጥር ዘዴ ነው Li,M.P.&Lam,B.H.(1997).

ትብብራዊ ዘዴ አደረጃጀቱ ስብጥራዊነት ላይ የሚመሰረት በመሆኑ በተማሪዎች መካከል ባህሪያዊ፣ ግንዛቤያዊ እና ማህበራዊ ትስስርን ይፈጥራል፡፡ ባህሪያዊ ትስስሩ በአንድ ቡድን አባላት መካከል መነጋገርን፣ መተራረምን፣ ድጋፍ መሰጣጣት፣ የሃሳብ ትግልና የተሻለ የመረጃ ልውውጥ በመካከላቸው ስለሚኖር ጠንካራ ግንኙነትንና ጤናማ አንድነትን መፍጠር ያስችላል፡፡ ግንዛቤያዊ /አእምሯዊያን/ ትስስሩ በመማር ሂደት በሚኖረው ተራክቦ መረጃዎችን ከተለያየ አቅጣጫ በመረዳት ማደራጀትን፣ ማብራራትን፣ መተንተንንና መግለጽን ስለሚያካትት ጠንካራ ህብረት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ማህበራዊ ትስስሩ ደግሞ በተማሪዎች መካከል በሚኖረው ተራክቦ አዎንታዊ ግንኙነትን፣ ተግባርን በሀላፊነት መከወንን፣ ተራክቦን ማሳደግን፣ ተገቢ የሆነ ማህበራዊ ክሂልን ለመጠቀም የሚያስችል ቡድናዊ የመማርን ሂደትን ይፈጥራል Samadiyn,( 2014).

የትብብራዊ ዘዴ ንድፈ ሃሳብ የተመሰረተው በቫይጎቲስኪ ማህበራዊ ግንባታ ላይ ነው Gilsna,&Ashame,(2003). Harmer, (2007) እንደሚገልጹት፣ ማህበራዊ ግንባታ ትኩረቱ በማህበራዊ ተራክቦ እና በትብብራዊ መማር አእምሯዊና ስሜታዊ እውነታዎች ግንባታ ባለው ጠቀሜታ ላይ ነው፡፡ ቫይጎቲስኪ በጥናታቸው መማር ማህበራዊ እንደሆነ፣ እውቀት የሚገነባውም በተማሪዎች መካከል በሚኖረው የነቃ ተሳትፎና በማህበራዊ ተራክቦ መሆኑን ይገልጻሉ Jonson,(2014).

በማህበራዊ ግንባታዊያን ንድፈ ሃሳብ በማህበራዊ ተራክቦ ውስጥ መማርና እውቀትን በቀላሉ ማጎልበት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ከቤተሰብ ጋር፣ ከሞግዚቶቻቸውና ከሌሎች አዋቂዎች ጋር በሚኖራቸው ተራክቦ መማር የሚችሉ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ በትምህርት ቤት ውስጥ በክፍል ውስጥ በሚኖረው የመማር ሂደት ከመምህራንና ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በሚኖረው ተራክቦና በሚለዋወጡት ምጋቤ ምላሽ ይማማራሉ፤እውቀት ያገኛሉ Yusnani,(2018).

የግለሰቦች ችሎታ የሚያድገው በማህበራዊ ተራክቦ ውስጥ ነው፡፡ በትብብራዊ ዘዴ በተማሪዎች መካከል የሚፈጠረው ተራክቦ መወያየትን፣ መከራከርን፣ መተማመንንና በግልጽ አስተያትን የመስጠት እድል ስለሚሰጥ፤ እውቀትንና መረጃን በመለዋወጥ የተሻለ መረዳትንና ችሎታን እንዲጎለብቱ ያስችላቸዋል Cesler,(1992).& Lantolf,J.P.(2000).

በማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ የሚነሳው ጠቃሚ ጉዳይ የቀረበ የእድገት ክልል ነው፡፡ ይህ እድገት ተማሪዎች መማራቸው ከግላዊነት ወደ ማህበራዊነት (ተማሪ ከተማሪ አቻ ተራክቦ እና ከመምህር ተማሪ ጤናማ ግንኙነት) በማሸጋገር በጋራ መስራት ሲችሉ የተሻለ መረዳትና የተቀራረበ ግንዛቤ በመፍጠር አጠቃላይ እውቀታቸውን በማሳደግ የቀረበ የእድገት ክልል ማጎልበት ያስችላቸዋል፡፡ ነገር ግን የቀረበ የእድገት ክልልን በትምህርት ቤት መማሪያ ክፍል ውስጥ ከመምህራንና ከአቻ ተማሪዎች ጋር ከሚኖረው ማህበራዊ ተራክቦ ውጭ በመገደብ ፈጽሞ ውጤታማ ማድረግ አይቻልም (ላም ቢ ኤች፣2013)፡፡

ከቫይጎቲስኪ ማህበራዊ ግንባታ ጽንሰ ሃሳብ የምንረዳው በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች ፍዝና አድማጭ ብቻ አይሆኑም፡፡ በመጻፍ ችሎታ ትምህርት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰጡ ተግባራትን በትብብራዊ ቡድን ሆነው በሚያደርጉት ተራክቦ ውስጥ በምክንያታዊ ውይይቶች መተማመንን፣ አስተያየቶችንና ምጋቤ ምላሾችን ስለሚለዋወጡ ንቁ ተሳታፊ በመሆን ጠንካራ ማህበራዊ አንድነትና ጤናማ ግንኙነት በመፍጠር፣ ማህበራዊ ክሂላቸውንና አእምሯዊ ግንዛቤያቸውን ከፍ ያደርጋል ፡፡

### 2.3.1 የትብብራዊ ዘዴ የመማር ማስተማር ሂደት የአተገባበር ብልሃቶች

#### 2.3.1.1 የትብብራዊ ዘዴ የቡድን አመሰራረት ብልሃቶች

እንደ Richards and Rodgers, (2002). ገለጻ የቡድን ምስረታ በተማሪዎች መካከል አዎንታዊ ተደጋጋፊነት እንዲኖር የሚያደርግ ስለሆነ በቡድን ምስረታ ወቅት የሚከተሉትን ነገሮች ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

1.የመጀመሪያው የቡድን ስፋት መወሰን፡- የተማሪዎችን ዕድሜ፣ ለትምህርቱ የተሰጠው ሰዓትና የሚከናወኑ ተግባራትን ከግምት ውስጥ በማስገባት አንድ ቡድን ውስጥ ምን ያህል ተማሪ መካተት እንዳለበት መወሰን ነው፡፡ የቡድን አደረጃጀቱን ከ 2-4 የሚደርሱ ተማሪዎችን በአንድ ቡድን መመደብ ተመራጭነት አለው፡፡

2.ተማሪዎችን በየቡድኑ መመደብ፡- ይህ ደግሞ በመምህሩ ወይም በተማሪዎች ምርጫ አለበለዚያ ደግሞ በእጣ ሊከናወን ይችላል፡፡ በመምህሩ ምርጫ የሚከናወነው ምደባ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ ምክንያቱም የተማሪዎችን ያለፈ ጊዜ ስኬት፣ ፆታ፣ የመጡበትን አካባቢ ባህላዊና ማህበራዊ ዳራ እና የመሳሰሉትን ጉዳዩች በሚገባ ሊያውቅ ስለሚችል ነው፡፡

3.ለሁሉም የቡድን አባል ተማሪዎች የየራሳቸው የሆነ ድርሻን መስጠት፡- ለምሳሌ፡-

አስተዋዋቂ፡-ራሱ የቡድኑ ተሳታፊ በመሆን የቡድኑን ስራ በሃላፊነት ይመራል፡፡ለቡድን አባላት ተግባራትን እንዲከፋፈሉ ያደርጋሉ፡፡

ጸሀፊ፡-በትብብራዊ ዘዴ የሚማሩ ቡድኖች በውይይት ሂደት የሚነሱ ሃሳቦችን በመመዝገብ የተጠቃለለውን የመጨረሻውን ሪፖርት ለአቅራቢው ያቀርባል፡፡

የሰዓት ተቆጣጣሪ፡-የቡድን አባላት መጠቀም ያለባቸውን ጊዜ ያሳውቃል፤ይቆጣጠራል፤ ለቡድኑ የተሰጠው ጊዜና ተግባራት መጣጣማቸውን ያረጋግጣል፡፡ተጨማሪ
ጊዜ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ከመምህሩ ጋር በመነጋገር እንዲጨመር
ያደርጋል፡፡ አቅራቢ፡- የቡድን አባላትን የውይይት ማጠቃለያ ለክፍሉ ያቀርባል ወይም ያንጸባርቃል፡፡ አረጋጋጭ፡-እያንዳንዱ የቡድን አባል የተጣለበትን ሃላፊነት መወጣት አለመወጣቱን
በመከታተል ያረጋግጣል፡፡ አበረታች፡- እያንዳንዱ የቡድን አባል የተሰጠውን ተግባር በሚያከናውንበት ወቅት
የበለጠ እንደተጋ የሚያበረታቱ ቃላትን በመጠቀም እንዲበረታቱ ያደርጋል፡፡ ወ.ዘ.ተ እያሉ እያንዳንዱን ተማሪ መሰየምና ድርሻ መስጠ ያስፈልጋል፡፡

4.እያንዳንዱ ተማሪ ለስራው ተጠያቂ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስ፡- ይህ በቡድን ስራው ወቅት እያንዳንዱ ተማሪ ካበረከተው አስተዋፆ በመነሳት ውጤት በመስጠት ወይም ከቡድን አባላት ውስጥ ዕድል ሰጭ በሆነ መንገድ በዘፈቀደ ሁኔታ አንዱን በማስነሳት ስራቸውን ለክፍሉ ተማሪ እንዲያንጸባርቁ በማድረግ እና በመሳሰሉት ዘዴዎች ሊከናወን ይችላል፡፡

5.የተማሪዎችን የቡድን ስራ መዋቅር ማስያዝ፡- ይህ ተማሪዎች በቡድን ሆነው አንድን ተግባር በሚያከናወኑበት ወቅት የተለያዩ ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ በማድረግ ይከናወናል፡፡

6.በስብጥራዊነት ማቧደን (Hetrogeneous grouping):- ስብጥራዊ መርህ በአንድ ትብብራዊ የመማር ቡድን ውስጥ የሚዋቀሩ ተማሪዎች ቅይጥ ወይም ውህድነት የሚታይበት ነው፡፡ ይህም የተማሪዎች የተለያዩ ተላውጦችን (ጾታን፣ ብሄርን፣ ማህበራዊ መደብን፣ ሃይማኖትንስብእናን፣ እድሜ፣ ቋንቋ፣ ችሎታና ትጋትን) የሚያካትት ነው፡፡ እንዲሁም የቡድን አባላትን የሃሳብ ተሳትፎ ጥምረትም ይጠይቃል፡፡ አላማውም በተማሪዎች መከካል መተጋገዝን፣ ልምድ መለዋወጥን፣ እውቀት መጋራትን፣ ልዩነትን መቀበልንና ማድነቅን ያጎለብታል (ጃኮብስ፣2004) ፡፡

### 2.3.1.2 ትብብራዊ ዘዴ የትግበራ ሂደቱ መሰረታዊ መርሆች

ተማሪዎችን በቡድን ማስቀመጥና ተባብረው እንዲሰሩ ብቻ መጠበቅ የተማሪዎችን ትብብራዊነት ማሳደግ አይችልም፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በተመደቡበት ትብብራዊ ቡድን በትግበራ ሂደቱ ነቅተው የማይሳተፉ፣ በነጻነት ሃሳባቸውን ለሌሎች የማያካፍሉና ከሌሎችም የማይቀበሉ፣ የማይከራከሩ፣ የማይተማመኑና የመማር ሂደታቸውን የማይገመግሙ ከሆነ የሚጠበቀው ውጤት ዝቅተኛ ይሆናል Jonson,(1990). በክፍል ውስጥ ትብብራዊ ዘዴን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመተግበር የሚረዱ አምስት ቁልፍ የሆኑ መርሆች አሉ RobertJonson,(1992)Jonson,andJonson,Smiz,(1998)&Jonson&Jonson,(2000)Jonson,& Jonson,(2017፤).

የመጀመሪያው ቁልፍ መርህ በክፍል ውስጥ በሚኖረው የመማር ሂደት አዎንታዊ ተደጋጋፊነት መፍጠርን የሚመለከት ነው፡፡ ተማሪዎች አንድን የመማር ግብ ለማሳካት ሚናቸውን በለየ መደጋገፍ አንዱ ሌላውንና ራሱን ለማብቃት ድርሻውን መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ ምክንያቱም የአንዱ መጠቀም የቡድን አጋሩ መጠቀም እንዲሁም የአንዱ መጎዳት የቡድኑ መጎዳት ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ መርህ ተማሪዎች የሚያስቡትና የሚነጋገሩት ከመማር የሚጠበቀውን ውጤት የጋራ ስኬት ማድረግ ነው፡፡ በሂደቱም

በሚኖረው ተራክቦ የተማሪዎች የመማር ተነሳሽነት ይጨምራል፤ ውጤት ላይ ከፍ እንዲል ያደረጋል፤ የባህሪይና አመለካከት ለውጥ ይመዘገባል Li,M.P.&Lam,B.H.( 2013).

ሁለተኛው ቁልፍ መርህ ትብብራዊነትን ለማሳካት በተማሪዎች መካከል ተራክቦንና ፈቃደኝነትን ማሳደግና ማበረታታት ይመለከታል፡፡ ትብብራዊነትን ማሳደግ እንደ Gills,(2016). ገለጻ በተማሪዎች መካከል መተማመን በመገንባት፣ የማስተባበር፣ ምክንያታዊነትን፣ ውሳኔ የመስጠትና ችግሮችን የመፍታት ክሂል ያዳብራሉ፡፡ ትብብራዊነት ሲያድግ የቡድን አባላት ስነ ትምህርታዊ እና ስብእናዊ አቅም በማሳደግ ችሎታቸውን በተግባር ማሳየት ይጀምራሉ፡፡ እንዲሁም፣ በቡድን አባላት መካከል በሚኖረው ተራክቦ ብቃትንናውጤታማነትን ያሳድጋሉ Zwan,( 2015).

ሶስተኛው መርህ የተማሪዎችን ግለሰባዊና ማህበራዊ ተጠያቂነትን ወይም ተግባራትን ለማከናወን የሚኖራቸውን ኃላፊነት የሚመለከት ነው፡፡ ትብብራዊ ቡድንን ስንጠቀም የተቀናጀ ቡድንና ግለሰባዊ ተጠያቂነት ይሻል፡፡ አላማውም እያንዳንዱ የትብብራዊ ቡድን አባል በራሱ ፈቃድ ጠንካራ ስብእና የሚገነባበት ነው፡፡ ግለሰባዊ ተጠያቂነት እያንዳንዱ የቡድን አባል ጥንካሬ የሚፈተሽበትና የሚረጋገጥበት ቁልፍ ነው፡፡ የመማሪያ ክፍሉም ገጽታ አንደኛ ተማሪዎች እውቀትን፣ ክሂልን፣ ብልሃትንና የትግበራ ቡድኑን የትግበራ ቅደም ተከተል የሚማሩበት ሲሆን ሁለተኛው በትብብራዊ የመማር ሂደት ያገኙትን እውቀት ውይም ብቃታቸውን፣ የመማር ብልሃታቸውንና ያገኙትን ግላዊ ችሎታ በተግባር የሚያሳዩበት ነው Jonson,(2014).

አራተኛው መርህ ከተቀመጠው ቡድናዊ ግብ አኳያ እያንዳንዱ የቡድን አባል ሚናውን በመለየት፣ ሃላፊነቱን በማወቅ፣ የሚጠበቅበትን ተግባር በማከናወን ውጤታማነቱ የሚፈተሸበት ቡድናዊ ሂደት ነው፡፡ ከተገኘው ውጤት በመነሳት ከተሳካ ውጤቱ ቀጣይነቱን ለማስጠበቅ፣ ካልተሳካ የማረም ስራ የሚሰራበት ነው፡፡ አላማውም የጋራ ግብ በማሳወቅ፣ የተግባር ሂደቱን በግልጽ ለማብራራት፣ ውጤታማነቱን ለማሳደግና ግብ ማሳካት ነው Tran,V.D(2013).

የመጨረሻው መርህ በተማሪዎች መካከል ማህበራዊ ክሂል የሚያሳድገውን የፊት ለፊት ተራክቦን የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ መርህ ቁልፍ ጉዳይ እንደ Li,M.P.&Lam,B.H.(2013).and Zwan,(2015). ገለጻ ግለሰቦች ለጋራ ስኬት መረዳዳትን፣ መበረታታትንና መመሰጋገንን ሊያሳድጉ ይገባል የሚል ነው፡፡ ምንም እንኳን አንዳንድ ቡድኖች ተናጠላዊነትንና የሌላው የመገልበጥ ችግር ቢታይባቸውም ሌሎች የጋራ አላማን ለማሳካት

በትብብራዊ ተራክቦ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡ በእነዚህ አእምሯዊ ሂደቶችና በውስጤ ቡድናዊ ተግባራት አፈጻጸም ከሌሎች ጋር የሚኖረውን ተራክቦ በማሳደግ ችግሮችን እንዴት መፍታት እንደሚቻል፣ በጽንሰ ሃሳቦች ላይ መወያየትንና መግለጽን፣ እውቀትን መማማርንና ከቀደመ እውቀት ጋር በማስተሳሰር ክሂልን ማጎልበት ይቻላል፡፡ የፊት ለፊት ተራክቦ መርህ በቡድን አባላት መካከል የቡድን ተጠያቂነትን፣ ምክንያታዊ ክርክርንና ማጠቃለያ መስጠትን፣ ማህበራዊ አርአያነትንና የመደጋገፍ ችሎታን እንዲያሳድጉ በማድረግ በኩል አዎንታዊ ተጽእኖ ያደርጋል ፡፡

### 2.3.2 ትብብራዊ እና ተለምዷዊ የማስተማር ዘዴ ልዩነት እንደ

**onson,**(1999). and Yusnani, (2018) .በተለምዷዊ ና ትብብራዊ ዘዴ መካከል ያለውን ልዩነት በሚከተለው መልኩ ያስቀምጣሉ፡፡

| ተለምዷዊ ዘዴ | ትብብራዊ ዘዴ |
|---|---|
| መምህር ተኮር ነው፤ | ተማሪ ተኮር ነው፤ |
| አዎንታዊ ተደጋጋፊነት አይታይበትም፤ | አዎንተዊ ተደጋጋፊነት ይታይበታል፤ |
| አንድ ወጥነት ያለውን ወይም ተመሳሳይ (homogeneity) የማስተማር ስልትን ይከተላል፤ | የተማሪዎችን የተለያዩ ተላውጦችን መሰረት ያደረገ ውህድ (ስብጥራዊነት) ይታይበታል፤ |
| የቡድን ስራን የሚያከነውኑ ቢኖሩም ጥቂት ናቸው፤ተማሪዎችም ያለ ማንማ ጣልቃ ገብነት ይማራሉ፤ | |
| ግለሰባዊ ተጠያቂነት አይታይበትም፤ | በየቡድናቸው በሚኖረው የተግባር አፈጻጸምግለሰባዊ ተጠያቂነት ይኖራል፤ |
| ቡድን አባላት መካከል አንዳቸው ስለአንዳቸው ሃላፊነት አይኖራቸውም፤ | ሁኔታ ይሰራሉ፤የአባላቱም ሃላፊነት አለባቸው፤ |
| ከተሪዎች የሚጠበቀው የተጠናቀቀ ስራ ነው፤ | በቡድን ስራው ግብና አላማ ተቀምጦ የሚሰራ ስለሆነ ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ያበረታታል፤ |

| | |
|---|---|
| በትብብራዊነት ላይ የተመሰረተ መልካም ግንኙነት የሌለው ነው፤ | ምቹ የሆነ የክፍል ውስጥ መማርና መልካም የስራ ግንኙነት ይፈጥራል፤ |
| በተማሪዎች የመማር ሂደት ላይ የሚደረገው ክትትል አናሳ ነው፤ | መምህሩ ያመቻቻል፤ ያነቃቃቸዋል፤ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣል፤ ተገቢ የሆነ ክትትል ይደረጋል፤ |
| ተማሪዎች አስቀድመው የሚያውቁት ክሂል አለ ተብሎ ስሚታሰብ ትብብራዊ ክሂሎት ላይ አያተኩርም፤ | ትብብራዊ ክሂሎት እንዲያድግ ይጠበቃል፤ |
| እውቀትን ያስተላልፋል፤ | አውቀትን ያሸጋግራል፤ |
| ግላዊ እና ውድድራዊ ነው፤ | ትብብራዊነት ላይ ያተኩራል፤ |

### 2.3.3 በትብብራዊ ዘዴ የሚዋቀሩ የቡድን አይነቶች

እንደ Jonson, (1998). and David.Jonsnand, (1998). ንድፈ ሃሳብ ጥናት የትብብራዊ ዘዴ የቡድን ዓይነቶች በሶስት ይከፈላሉ፡፡ ዘዴው ሁለገብ የሆነ የማስተማሪያ ቅደም ተከተላዊ ሂደቶች ያሉት ሲሆን፣ ለተለያየ አላማ ማለትም ለዝርዝር የትምህርት ይዘት ማስተማሪያ (መደበኛ የሆነ ትብብራዊ መማር ቡድን)፣ በእይታና በገለጻ መልክ ለሚቀርቡ የማስተማሪያ መሳሪያ መረጃዎችን ለማረጋገጥ (ኢ. መደበኛ የሆነ ትብብራዊ መማር ቡድን) እና ረጅም ጊዜ የሚወስድ ድጋፍና እገዛ የሚሹ አካዳሚያዊ ትምህርቶችን (ትብብራዊ መሰረት ያላቸው ቡድኖችን) እንጠቀማቸዋለን፡፡ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

#### 2.3.3.1 መደበኛ ትብብራዊ የመማር ቡድን

መደበኛ በትብብራዊ ዘዴ የመማር ቡድን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተሰጣቸውን አንድን የትምህርት ይዘት በመሸፈን የጋራ ግብ ለማሳካት ከአንድ ክፍለ ጊዜ እስከ ለበርካታ ሳምንታት የሚቆይ የቡድን አይነት ነው፡፡ የዚህ ቡድን የትግበራ ሂደት ተማሪዎች በመማር ሂደት የሚገጥማቸውን ችግር በጋራ በመፍታት በመማሪያ መጽሀፋቸው በየምዕራፉ መጨረሻ የሚሰጡ ጥያቄዎችን በመስራት ሪፖርት እንዲያቀርቡ ይጠይቃል፡፡

#### 2.3.3.2 ኢ. መደበኛ ትብብራዊ የመማር ቡድን

ይህ ቡድን በጊዜያዊነት የሚደራጅ ሆኖ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተሰጣቸውን ስራ እስኪጨርሱ ድረስ ከጥቂት ደቂቃዎች እስከ አንድ ክፍለ ጊዜ ብቻ ይቆያል፡፡ አላማው

ለተማሪዎች የሚቀርበውን የትምህርት ይዘት ማስተዋወቅ፣ ተማሪዎችን ዝግጁ ማድረግና ማጠቃለያ መስጠት ነው፡፡ በኢ- መደበኛ ትብብራዊ ቡድን ከመምህሩ ገለጻ በፊትና በኋላ ለቡድኑ የመወያያ ጊዜ ከ3-5 ደቂቃ እና ለእያንዳዱ ተናጋሪ ከ2-3 ደቂቃ ይፈቅዳል ፡፡

### 2.3.3.3 ትብብራዊ መሰረት ያላቸው ቡድኖች

ይህ ቡድን ረዥም ጊዜ የሚቆይ፣ ስብጥራዊ የሆነ ትብብራዊ ቡድን ያለውና ቋሚ አባላት የሚይዝ ነው፡፡ አላማው እያንዳንዱ የቡድን አባል ተማሪ በመማር ሂደት ውጤታማ እንዲሆን መደገፍ፣ ማበረታታትና ማገዝ (የክፍል ቁጥጥር፣ ተግባራትን መጨረስ፣ መማር) እና ጤናማ የሆነ ማህበራዊና ግንዛቤያዊ ክሂላቸውን ማሳደግ ነው፡፡

### 2.3.4 የትብብራዊ ዘዴ የትግበራ ቴክኒኮች

በትብብራዊ ዘዴ በርካታ የትግበራ ቴክኒኮችና አደረጃጀቶች ያሉ ቢሆንም የክፍል ውስጡን የመማር ማስተማር ሂደት የሚያግዙና ተማሪዎችን ውጤታማ የሚያደርጉትን መርጦ መጠቀም የተለያዩ ችሎታዎችን ማዳበር ያስችላል፡፡ በመማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራንና ተማሪዎች በቀላሉ ተግባራዊ ሊያደርጓቸው የሚሏቸው ቴክኒኮች እንደማንዳል (2009) የሚከተሉ ናቸው፡፡

#### 2.3.4.1 ማሰብ መጎዳኘት እና ማጋራት

ይህ የትግበራ ቴክኒክ (አደረጃጀት) በላይማን (1981) የተነደፈ ነው፡፡ በትግበራ ሂደቱ ቴክኒኩ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ተግባር (ጥያቄ) በዝምታ እንዲሰሩና የተረዱትን በማስታወሻቸው እንዲጽፉ ይፈቅዳል፡፡ ተማሪዎች በተሰጣቸው ጥያቄ በግላቸው የተረዱትን ከቡድን አጋሮቻቸው ጋር ጥንድ ጥንድ ሆነው ይወያያሉ፤ በውይይት ሂደቱ የሚነሱ ሃሳቦችን በአንክሮ ይከታተላሉ፤ ማስታወሻ ይይዛሉ፡፡ በጥንድ የተደረገው ውይይት በቡድን ከተጠቃለለ በኋላ ለክፍል ይቀርባል፤ ውይይት ተደርጎ፤ አስተያቶች ተሰጥተው፤ የመጨረሻው ስራ ለመምህሩ ይሰጣል፡፡

የዚህ ማስተማሪያ ዘዴ ጠቀሜታው እንደ Zwan, (2015). የሚከተሉ ናቸው፡፡

- ለተማሪዎች በቂ የማሰቢያ ጊዜ ስለሚሰጣቸው የጠራ ምላሽ እንዲኖራቸው ያደርጋል፤
- ከማሰቢያ ጊዜ በኋላ በጥንድ ስለሚወያዩ አመለካከታቸውን ለሌሎች የማጋራት እድል ይሰጣቸዋል፤
- በተማሪዎቹ መካከል (ራሳቸውን ማግለል ለሚፈልጉ) ተራክቧዊ ተግባቦት ከፍ እንዲል ያደርጋል፡፡

### 2.3.4.2 የተለያዩ ተግባራትን ለተለያዩ የቡድን አባላት መስጠት

ይህ የትብብራዊ ዘዴ የትግበራ ቴክኒክ አንዱና በብዙ የሚታወቅ ሲሆን በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሁለት ቡድኖች መካከል ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ሁለቱ ቡድኖች መደበኛው (home group)ና ጊዜያዊ (expert group) ቡደኖች ናቸው፡፡ የትግበራ ሂደቱም በመደበኛው ቡድን ላሉ የቡድን አባላት የተለያዩ የመጻፊያ ርዕሶች ይሰጣቸዋል፡፡ ቀጥሎ አንድ ጊዜያዊ ቡድን ይደራጅና የመደበኛው ቡድን አባላት የተሰጣቸውን ርዕስ ይዘው ወደ አዲሱ ቡድን ይመጣሉ፡፡ በተሰጣቸው ርዕስ በጊዜያዊ ቡድኑ ይወያያሉ፣ ማስታወሻ ይጽፋሉ፡፡ በአዲሱ ቡድን የነበረውን ውይይት ከጨረሱ በኋላ ወደ መደበኛ ቡድናቸው ተመልሰው በተነሱ ጥያቄዎች ላይ የተደረሰውን ምላሽ ለቡድን አባሎቻቸው ያብራራሉ፣ ይደማመጣሉ፣ የጋራ ድምዳሜ ላይ ይደርሳሉ፡፡ በመጨረሻም መምህሩ የየቡድኑን ማጠቃለያ ለክፍሉ እንዲቀርብ ካደረጉ በኋላ ምጋቤ ምላሽ ይሰጥና ይጠቃለላል፡፡ እንደ Galican,(2019). ይህ ቴክኒክ ተሳትፏቸውን በማሳደግ ማህበራዊነትንና ትብብራዊነትን ይፈጥራል፡፡

### 2..3.4.3 ባለ ሶስት ደረጃ ቃለ መጠይቅ

በዚህ የትብበራዊ ዘዴ ትግበራ ቴክኒክ የክፍል ውስጥ የመማር ሂደት የሚተገበረው የአንደኛው ቡድን አባላት ከሌላኛው የቡድን አባላት አንድ አንድ ተማሪ ይመርጣሉ፡፡ የመጀመሪያው ደረጃ ከሁለቱ አንዱ ጠያቂ ሌላኛው ተጠያቂ በመሆን ጠያቂው ማብራሪያ የሚሻ ጥያቄ ይጠይቃል፡፡ ተጠያቂው ስለቀረበው ጥያቄ የተረዳውን ይገልጻል፡፡ ሌሎች የቡድን አባላት ይከታተላሉ፡፡ ሁለተኛው ደረጃ ሚና በመለዋወጥ ተጠያቂው ጥያቄ ይጠይቃል፡የተረዳውን ምላሽ ይሰጣል፡፡ በሁለቱም ዙር የሚሰጡ ምላሾች በጠያቂዎቹ ይመዘገባል፡፡ በመጨረሻም ሁለቱም ጠያቂና ተጠያቂ ተማሪዎች ወደየቡድናቸው ይመለሱና በተነሳው ጥያቄ ላይ የተረዱትን ምላሽ ለቡድን አባላት ይገልጻሉ፡፡ አላማውም ተማሪዎች በቡድን መማር ውስጥ የሚገጥማቸውን ችግር የመፍታት፣ ተግባራትን የመጨረስ፣ ውጤታማ መሆን የሚያስችልና ክሂል የሚያዳብሩበት ነው (ተስፉ፣2010፤ Galican,(2019).

ከላይ ከተነሱ ውጭ Slavin,R.E. (1995) and Jonson,(1998). የነተደፉና Li,M.P.&Lam,B.H. (2013). የተብራሩትን የትብብራዊ ዘዴ የትግበራ ቴክኒኮች እንመለከታለን፡፡

### 2.3.4.4 በጋራ መማር

የዚህ ትብብራዊ ዘዴ ሞዴል ጀማሪ David.Jonson and Rodgers,&Jonson ናቸው Jonson,(1998). and Li,M.P.&Lam,B.H.(2013). ሞዴሉ በባህሪው በአዎንታዊ ተደጋጋፊነት፣

ግለሰባዊ እና ቡድናዊ ተጠያቂነት፣ የፊት ለፊት ተራክቦ በማሳደግ፣ በትብብራዊ ክሂል እና በቡድን ሂደት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ዘዴው ስብጥራዊ የሆነ ቡድን በማደራጀት፣ በአንድ የትምህርት ይዘት የጋራ ውጤት የሚመዘገብበት ሲሆን፣ ትኩረቱ በትብብራዊ መማር ክፍል ውስጥ ተማሪዎች ወደ ትግበራው ከመግባታቸው በፊት ቡድን ይደራጁና የትግበራ ሂደቱ እንዴት እንደሚፈጽም ይወያያሉ ፡፡

### 2.3.4.5 ውጤት ተኮር የቡድን አከፋፈል

ይህ ዘዴ በተለያዩ የትምህርት አይነቶች (ቋንቋ፣ ሂሳብ፣ ማህበራዊ ሳይንስ ወዘተ) ጥቅም ላይ የዋለ ነው እንደ Silva, (1995). ገለጻ ውጤት ተኮር የቡድን አከፋፈል አምስት የትግበራ ደረጃዎች አሉት፡፡

- የተመረጠው የትምህርት ይዘት ለተማሪዎች በጥያቄ መልክ ይገለጽላቸዋል፡፡
- ከቀረበው ገለጻ በመነሳት የቡድን ውይይት ይደረጋል፡፡ እዚህ ላይ ጥንቃቄ ሊደረግ የሚገባው የመማር ሂደቱ ውድድር ሊነጸባረቅበት ስለሚችል የቡድን አደረጃጀቱ ስብጥራዊ እንዲሆን ይመከራል፡፡
- ምንም እንኳን ውይይቱ በቡድን የተደረገ ቢሆንም አቅም መፈተሻ ምዘና በግል እንዲፈተኑ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን የቡድን ውጤቱ ለእውቅና አሰጣጥ ስለሚጠቅም ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡
- እውቅና ይሰጣል፡፡ ውጤታማነታቸው የሚረጋገጠውና እውቅናው የሚሰጠው በተማሪዎች በቡድን ስራ በመጡት ውጤት አማካይ ላይ ተመስርቶ ቀድሞ ካለ ውጤት ጋር በማመዛዘን ይከናወናል፡፡

## 2.4 ትብብራዊ ዘዴ እና የመጻፍ ችሎታ

የቋንቋ ትምህርት አንዱ አላማ ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታቸው ዳብሮ ሃሳባቸውን፣ አመለካከታቸውንና ስሜታቸውን በጽሁፍ እንዲገልጹ ማስቻል ነው፡፡ ሆኖም ችሎታውን ለማስተማር ወስብስብና ከባድ የሚያደርጉ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህም ልንተዋቸው የማንችላው ንኡሳን ችሎታዎች ናቸው፡፡

Moore, (1999) እንደገለጹት፣ የመጻፍ ችሎታ ሰዋስውን ማወቅ ብቻ ሳይሆን ጽንሰ ሃሳባዊ ውሳኔን የሚጠይቅ ችሎታ ነው፡፡ መጻፍ የተለያዩ ገጽታዎች ያሉት ስለሆነ እንደ ንግግር

በቀላሉ የምንተግብረው አይደለም፡፡ መማርን የሚሻ፣ ጥሩ ሃሳብ ማፍለቅን፣ ከአላማው ጋር ማያያዝንና ማስፋፋትን የሚጠይቅ፣ ተገቢ ቃላትን መርጦ በመጠቀም ጥራት ያለውን ሃሳብ ለአንባቢ ማድረስ ላይ ያተኩራል፡፡

Spratt,M. (2005). እንደገለጹት፣ የመጻፍ ችሎታ በውስጡ ንኡሳን ችሎታዎችን የያዘ ነው፡፡ እነዚህም የአጻጻፍ ስርአት፣ የቃላት ምርጫ፣ የቋንቋ አጠቃቀም፣ ይዘት፣ ሰዋስውና የሃሳብ አደረጃጀት ናቸው፡፡ እነዚህ ንኡሳን ችሎታዎች ትክክለኛነት ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ሳይሆኑ ለአንባቢ የሚደርሰውን ጭብጥ እና ተግባቦታዊ ስኬትም ይመለከታሉ፡፡ ከቋንቋ ተግባር አንዱ ማግባባት ስለሆነ በመጻፍ ሂደት ተግባቦትን ለማሳካት በቂ ሃሳብ፣ ያን ሃሳብ በተገቢው መንገድ ማቀናጀት እና መግለጽ ያስፈልጋል Nunan,(1999).

Milawati, (2015). ገለጻ በተማሪዎች መካከል የመጻፍ ችሎታ ልዩነት አለ፡፡ ስለዚህ ይህን ልዩነት የሚያቀራርብ ዘዴ ያስፈልጋል፡፡ በተለያዩ ጥናቶች ሊረጋገጥ እንደተቻለው ውጤታማ ከሆኑ ዘዴዎቸ አንዱ ትብብራዊ ዘዴ ነው፡፡ ተማሪዎችን በትብብር ማሰራት አእምሮአዊ ለውጥን፣ በጥልቀት ማሰብን፣ መፍጠር መቻልንና ችግር ፈቺ ዘዴን መከተል ነው፡፡

በትብብራዊ ዘዴ ተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ የማስተማር ሂደት አእምሮአዊ ፍላጎትንና ዝግጅትን፣ ፈጠራንና ከፍተኛ የሆነ ቅደም ተከተላዊ የማሰብን ሂደት ተግባራት ያካትታል እንደ Sarget, (2004). ገለጻ የመጻፍ ችሎታን በትብብራዊ ዘዴ ማስተማር በትብብራዊ ተግባራት ሂደት የሚሰሙ አዳዲስ ቃላትን ለመተዋወቅ እድል ይሰጣል፤ እነዚያን ተግባራት በመማር ማሰተማሩ ሂደት መተግበር ትብብራዊ መማርንና የመጻፍ ችሎታ ሂደታዊ ተግባራትን ለማዋሃድ ይጠቅማል፡፡

በትብብራዊ ዘዴ የመጻፍ ችሎታን ለማስተማር የምንጠቀማቸው ተግባራት ሁለት አላማዎች ይኖሩታል፡፡ የመጀመሪያው በሚተላለፈው መልእክትና ተግባቦታዊ ተግባራት ላይ የሚያተኮር ሲሆን የመጻፍ ቅልጥፍናን ይመለከታል፡፡ ሁለተኛው ከቅርጽና መዋቅር ጋር የሚያያዘው ትክክለኛነት ላይ የሚያተኩረው ነው፡፡ መምህሩ በተግባር ሂደት የመጀመሪያውን መጠቀም ከፈለገ አእምሮአዊ ሁኔታን፣ በፍጥነት መጻፍንና ታራካዊ ቅደም ተከተሎችን መጠቀም ይችላል፡፡ ሁለተኛውን የሚመርጥ ከሆነ በቡድን ደብዳቤዎች እና ፕሮጀክቶች ላይ ሊያተኩር ይችላል Milawati,2015). ስለሆነም በመማሪያ ክፍል ውስጥ የዘዴው ትግበራ ሂደት ተገቢውን ትኩረት ሊያገኝ ይገባል፡፡

## 2.5 ትብብራዊ ዘዴ እና ተነሳሽነት

በመማር ማስተማር ሂደት ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገባቸው ነገሮች አንዱ ተነሳሽነት ነው፡፡ ተነሳሽነት እንደ Harmer, (1991). ሰዎች አንድን ተግባር እንዲፈጽሙ የሚገፋፋ ውስጣዊ ስሜት ነው፡፡Hancock, (2004). እንደገለጹት፣ ደግሞ ተነሳሽነት አንድ ሰው አንድን ግብ ማሳካት እንዲችል የሚያነቃቃ፣ የሚመራና ባህሪን የሚያስቀጥል ኃይል ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፡፡

የተለያዩ ጥናቶችም እንዳረጋገጡት ተነሳሽነት ከተማሪዎች መማርና ውጤታማነት ጋር ጥብቅ ትስስር አለው (ዋንጋ፣ ሂርተልና ዋልበርግ፣1993)፡፡ ቢሆንም፣ እንደ Goldberg,K.Foster,K.Maki,B. Emde,J.&O' Kelly,M. (2001). ገለጻ በትምህርት ቤት ውስጥ በሚኖረው የመማር ማስተማር ሂደት ብዙ ተማሪዎች ስኬታማ ለመሆን ያላቸው ተነሳሽነት ዝቅተኛ ነው፡፡ ዋነኛውም መለያ ግዴለሽነት፣ በክፍል ውስጥ የሚሰጡ ተግባራትን አለመስራት፣ ከክፍል መቅረትና ሌሎች የስነምግባር ችግሮች ናቸው ፡፡

ተማሪዎች ተነሳሽነታቸው ዝቅተኛ እንዲሆን ምክንያት ከሚሆኑ የመጀመሪያው ግለ ብቃት የለኝም ከሚል ስሜት የሚመጣ አሉታዊ አመለካከት ነው፡፡ ግላዊ ብቃት በመማር ሂደት ተግባራትን በብቃት ከመወጣት ጋር ይያያዛል Maki,(1980). ሁለተኛው የመምህር ተማሪ ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት ነው፡፡ አንድ መምህር ወደ መማሪያ ክፍል ሲገባ ይዞት የሚመጣው የትምህርት ይዘት አቀራረብ፣ የማስተማር ብልሃትና ለተማሪዎች የሚያሳየው ፍቅር በተማሪዎች የመማር ተነሳሽነት ላይ የራሱ ተጽዕኖ አለው Goldberg,K.እና ሌሎች(2001).

የተማሪዎችን ተነሳሽነት ለማሳደግ እንደ Lepper,M.R. (1988). ገለጻ አራቱን Cs ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህም የመጀመሪያው ቁጥጥር ሲሆን ተማሪዎች ውስጣዊ ተነሳሽ ሆነው መማራቸውን በበላይነት ተቆጣጥረው እንዲማሩ ማድረግ ተነሳሽነታቸውን ያሳድጋል፡፡ ሁለተኛው ፍላጎት መቀስቀስ ነው፡፡ ይህም ሰዎች የሚያከናውኗቸው ተግባራት ተግዳሮትን መፍታት ላይ ያተኮሩ ከሆነ ተነሳሽታቸው ይጨምራል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ችግሮችን መፍታት ላይ ያተኮሩ ተግባራትን እንዲፈጽሙ ሲደረጉ ተነሳሽ ይሆናሉ፡፡ ሶስተኛው አንድ መምህር የራሱ ተማሪዎች የሚፈልጉትን ተግባር መምረጥና ፍላጎታቸውን

ማወቅ ተነሳሽነታቸው እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ የመጨረሻው መማርን አውዳዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

እንደ Patrichia, (2006). ገለጻ ሌላው የተማሪዎችን ተነሳሽነት ሊያሳድግ የሚችለው የማስተማር ዘዴ ምርጫችን ነው፡፡ ከማስተማሪያ ዘዴዎቹም የተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት ከማደግ አኳያ ትብብራዊ ዘዴ ተማራጭ ነው፡፡ ዛሬ በሚታየው አለም የሳይንሱ ሊቃውንት የሚገጥሟቸውን ውስብስብ ችግሮች ለመፍታትና ውጤታማ ለመሆን የቡድን ስራን ተግብረዋል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎችም ለተሻለ ውጤት በትብብር መማር አለባቸው፡፡

Patricia, (2006) Silva,(1989). ጠቅሰው) እንደገለጹት፣ ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን ተነሳሽነት ከማሳደግ አኳያ ሁለት አስፈላጊ ገጽታዎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ተማሪዎች ቡድናዊ ግብ እንዲያሳኩና በመካከላቸው አዎንታዊ መደጋገፍ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ ሁለተኛው ተማሪዎች በመማር ሂደታቸው ግለሰባዊ ሃላፊነት ተሰምቷቸው እንዲማሩ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህም የሚያመለክተው አንድ ቡድን የሚመሰረተው በቡድን አባላቱ ግላዊ መማርና በቡድናዊ ውጤት ላይ ነው፡፡

በአጠቃላይ በትብብራዊ ዘዴ ተማሪዎች እንዲማሩ ማድረግ በተማሪዎች መካከል በራስ መተማመንን፣ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣ መደጋገፍ እንዲዳብር፣ መማራቸውን ተቆጣጥረው እንዲመሩና በተማሪዎች መካከል አዎንታዊ ተደጋጋፊነት እንዲፈጠር አዎንታዊ ተጽዕኖ ያደርጋል፡፡

## 2.6 በትብብራዊ ዘዴና በመጻፍ ችሎታ ትምህርት የተደረጉ ቀደምት

## ምርምሮች

ይህ ክፍል ከዚህ ጥናት ጋር በርዕስ፣ በአላማና እና ከተደረሰበት ድምዳሜ አንጻር በመፈተሽ ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ምርምሮች የተከለሱበት ክፍል ነው፡፡ እነዚህም ምርምሮች ይዘታቸው በመጀመሪያ ትብብራዊ ዘዴ ከንድፈ ሃሳባዊ አተያይ፣ የትግበራ ሂደቱንና ውጤቱንና የመማርን ብቃት ለማሳደግ ያለውን ሚና የተመለከተ፣ ሁለተኛው የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና የመማር ፍላጎታቸውን ከማጎልበት አኳያ ባለው ሚና፣ ሶስተኛው የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ የተመለከቱ እና አራተኛው ትብብራዊ ዘዴ እና ልማዳዊ

(መምህር ተኮር) ዘዴ የመጻፍ ችሎታን ለማጎልበት ካላቸው ፋይዳ አኳያ በንንጽር የፈተሹ ጥናቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡

በመጀመሪያ ትብብራዊ ዘዴ ከንድፈ ሃሳብ አኳያ የመማርን ብቃት ለማሳደግ ያለውን ሚና የተመለከቱ ጥናቶች Tran,V.D(2013). በሲሳይ፣ ኦላኒና አኑዋር(2015)እና Yusnani,(2019).ናቸው፡፡ ከጥናቶቹ ሁለቱ የውጭ ሲሆኑ አንዱ የሀገር ውስጥ ነው፡፡ Yusnani, (2018). በትብብራዊ ዘዴ ንድፈ ሃሳባዊ አተያይ ላይ ያተኮረ ጥናት አድርገዋል፡፡ ጥናቱ ትብብራዊ ዘዴ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በአእምሮታዊ፣ ባህሪያዊ እና ማህበራዊ ትስስራዊ እድገት ላይ ያለውን ሚና የተመለከተ ነው፡፡ የሰነድ ፍተሻ በማድረግ በቅይጥ ምርምር አይነት የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመተንተን ውጤቱን ገልጸዋል፡፡ ውጤቱም ተማሪዎች በትብብራዊ ዘዴ ሲማሩ ትምህርታዊ ክሂላቸውን በማሳደግና ማህበራዊ ተራክቦ በመፍጠር የመማር ብቃታቸውን የማጎልበት ፋይዳ ያለው መሆኑን አመልክቷል፡፡ ይህም በተማሪዎች መካከል የመወያየት፣ የመከራከር፣ የመተማመን፣ ሃሳባቸውን በነጻነት መግለጽ፣ ሌሎችን የማዳመጥና የትግበራ መርሆ ተማሪዎች በመማር ውጤታቸው ስኬታማ እንዲሆኑ አስተዋጽኦ ማድረጉን አረጋግጠዋል፡፡

ሌላው TranV.D (2013). በክፍል ውስጥ በሚኖረው የትብብራዊ ዘዴ ትግበራ ንድፈ ሃሳባዊ አተያይን መረዳት በሚል የተደረገ ጥናት ነው፡፡ ንድፈ ሃሳባዊ አተያዩ ልማዳዊ እና ትብብራዊ ዘዴ በተማሪዎች የመማር ውጤት ላይ የሚኖራቸውን አዎንታዊ ተጽዕኖ በማነጻጸር ተመልክቷል፡፡ በተለይ የትብብራዊ ዘዴን ፋይዳ በተሳሳተ መንገድ የተረዱና ተጨባጭ ለውጥ የሚያመጣ መሆኑን የማይቀበሉትን የማቃናትም አላማ ያለው ጥናት ነው፡፡ ውጤቱ ትብብራዊ ዘዴ ሚዛናዊ፣ ምክንያታዊና በተግባር የተፈተነ ዘዴ ስለሆነ፣ በተማሪዎች የመማር ሂደት ትምህርታዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊና ስነልቦናው ውጤት የማምጣት ፋይዳ ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡ በተጨማሪ በትብብራዊ ዘዴ በተማሩና በልማዳዊ ዘዴ በተማሩ መካከል ጉልህ የውጤት ልዩነትም መኖሩን አመልክተዋል፡፡

የትብብራዊ ዘዴ የትግበራ ሂደቱንና ውጤታማነቱን የተመለከተው የሀገር ውስጥ ጥናት በሲሳይ፣ ኦላኒና አኑዋር (2015) በሀረማያ ዩኒቨርሲቲ የተደረገው ተግባራዊ ምርምር ነው፡፡ አላማውም የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን ችሎታ ከማሻሻል አኳያ ያለው ሚናና የዘዴው አተገባበር መመርመር ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ጥናቱም ዘዴውን በመተግበር ሂደት እንቅፋት የሚሆኑ ጉዳዮችን በመለየት ለአተገባበር አመቺ የሆኑ ብልሃቶችን ይጠቁማል፡፡ ይህ ጥናት ንጥል ገላጭ ንድፍ ላይ ተመስርቶ የመረጃ አሰባሰብኑና አተናተኑን በቅይጥ (አይነታዊና

መጠናዊ) ምርምር አይነት የተገበረ ሲሆን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ የጽሁፍ መጠይቅ፣ ምልከታና የቡድን ውይይት ናቸው፡፡ የተሰበሰቡ መረጃ በገላጭና ድምዳሚያዊ ስታቲስቲክስ ተተንትኖ የተገኘው ውጤት ትብብራዊ ዘዴ የቡድን አደረጃጀቱ በጥንቃቄ ከተከናወነና ብልሃቶቹ በተገቢው የሚተገበሩ ከሆነ የተማሪዎችን የመማር ውጤትና ችሎታቸውን ከማሻሻል አኳያ ያለው ሚና አዎንታዊ ነው፡፡

ሁለተኛው የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማጎልበት ካላቸው ሚና አኳያ የተደረጉ ምርምሮች (ዘነበች፣2011 ዓ.ምAstarina,(2011) sumarshe, and Sanny,(2013) Milawati,(2015)& ዩሱፍ፣ጆሲ እና ዩሱፍ ፣2019፣)ናቸው፡፡ እነዚህ ጥናቶች የሀገር ውስጥና የውጭ ጥናቶች የተከለሱበት ነው፡፡ የዩሱፍ፣ ጆሹዋ እና ዩሱፍ (2019) የትብብራዊ ዘዴ የማስተማርና መማር ብልሃቶችን ተጠቅሞ ማስተማር የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ የማጎልበት ሚናን በተመለከተ በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ያተኮረ ምርምር አድርገዋል፡፡ የጥናቱ ንድፍ ከፊል ፍትነታዊ ሲሆን፣ የጥናቱ ውጤት ፈተናን በመረጃ መሳሪያነት በመጠቀም በገላጭና ድምዳሚያዊ ስታቲስቲክስ ተተንትኖ ተቀምጧል፡፡ በዚህ ጥናት ከመጻፍ ችሎታ ንኡሳን ችሎታዎች (ቃላት፣ አደረጃጀት፣ ሰዋስው እና አጻጻፍ ስርዓት) አራቱ ተተኩሮባቸዋል፡፡ የጥናቱም ውጤት በትብብራዊ ዘዴ ትምህርቱ ከመቅረቡ በፊት የተሰጣቸው የፈተና ውጤት ትምህርቱን ከተማሩ በኋላ ተፈትነው ካመጡት ውጤት አንጻር ሲታይ በእነዚህ ተላውጦች ላይ ይታይ የነበረውን የመጻፍ ችሎታ ችግር ለመቅረፍ እና ችሎታቸውን ለማሳደግ በትብብራዊ ዘዴ ማስተማር ውጤታማ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ Albesher, (2012). የተደረገው ጥናት የትብብራዊ ዘዴ ብልሃቶች ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ የማሳደግ ውጤታማነት እንግሊዝኛን በሁለተኛ ቋንቋ ከሚማሩ ተማሪዎች አንጻር የመረመረ ነው፡፡ ትኩረት የተደረገባቸው የመጻፍ ችሎታ ንዑሳን ችሎታዎች የሃሳብ አደረጃጀትና ማስፋፋት፣ ይዘት፣ የሰዋስው ትክክለኛነት፣ የቃላት አጠቃቀምና በአጻጻፍ ስርዓት ላይ ነው፡፡ ጥናቱ በሁለት ቡድን በተከፈሉ 48 ተማሪዎች ላይ የተደረገ ሲሆን ከትምህርት በፊትና በኋላ የሙከራ ቡድኑ በትብብራዊ ዘዴ ተምረው እንዲፈተኑና የቁጥጥር ቡድኑን በግል እንዲማሩና እንዲጽፉ በማድረግ ተከናውኗል፡፡ ከፈተናው፣ ከጽሁፍ መጠይቁና ከአራት ተማሪዎች ከተገኘው መረጃ ትንተና የተገኘው ውጤቱ እንዳረጋገጠው ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና የተማሪዎችን አመለካከት ከማሳደግ አኳያ አዎንታዊ ተጽዕኖ መፍጠሩን አረጋግጧል፡፡

Astarina, (2011). በትብብራዊ ዘዴ መጻፍን መማር የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለውን ሚና በኮሎምቢያ ዮጋያከተር በስምንተኛ ክፍል ሰላሳ ተማሪዎች፣ አንድ የእንግሊዝኛ መምህርና ራሷዋ አጥኚዋ ተሳታፊ የሆኑበትን ጥናት አድርገዋል፡፡ በጥናታቸው ለይተው ያዩቷቸው ችግሮች ተማሪዎች በመጻፍ ችሎታ ትምህርት የክፍል ውስጥ ትግበራ ላይ ያላቸው ተነሳሽነት (የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ውጤታማነትን የሚወስንና አንድን የመማር ግብ ማሳኪያ) ማነስ፣ በመጻፍ ሂደት ሃሳብ ማመንጨትና የሃሳብ እጥረት (በመጻፍ ሂደት ሃሳብ እንደ ጽሁፍ ይዘት በሚታየው) እና በሰዋስው አወቃቀር (ከጽሁፍ ተለይቶ በማይታየው) ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ የጥናቱ መረጃ የተሰበሰበው በምልከታና በቃለ መጠይቅ ሲሆን የጥናቱ ውጤት ተተንትኖ ሲታይ ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን ተነሳሽነት ለማጎልበት፣ ሃሳብ በማመንጨትና ማጎልበትን ለማሳደግ እና የሰዋስውን እውቀት ለማሻሻል ፋይዳ እንደነበረው አረጋግጧል፡፡

Milawati, (2015). በጆጎናላን ክላንተ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችን በትብብራዊ ዘዴ መጻፍን ማስተማር የመጻፍ ችሎታ ከማሻሻል ረገድ ያለውን ሚና የመረመረ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱም 42 ተማሪዎች የተሳተፉበትና መረጃዎች የተሰበሰቡት በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ፣ በጽሁፍ መጠይቅና በፈተና ነው፡፡ የተሰበሰቡ መጠናዊና አይነታዊ መረጃዎች ተተንትነው ሲገለጹ የጥናቱም ውጤት ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ከማሻሻል ረገድ የተሻለ እና ተመራጭ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

የሱማርሽ እና ሳኒያ (2013) የትብብራዊ ዘዴ የማሰብ፣ ማጎዳኘት እና የማጋራት ብልሃት ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማጎልበት ያለው ሚና የመረመረ ጥናት ነው፡፡ ጥናታቸው ተማሪዎች በትብብራዊ ቡድናቸው ሆነው የመጻፍ ችሎታን ትምህርት እንዲማሩ ተደርገው ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት እንደተቻለ አረጋግጠዋል፡፡

ቀጥሎ የቀረበው የሀገር ውስጥ ጥናት ሲሆን ዘነበች (2011 ዓ.ም.) የትብራራዊ መማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለውን ሚና በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት የፈተሸ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ የተከተለው ንድፍ ሙከራዊ፣ ለመረጃ አሰባሰቡና አተናተኑ መጠናዊ ምርምር ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት የመጻፍ ችሎታ ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ እነዚህ የተሰበሰቡ መጠናዊ መረጃዎች በድምዳሜያዊ ገላጭ ስታቲስቲክስ ቲ- ቴስት ተተንትነዋል፡፡ ከድህረ ትምህርት ፈተናና ከጽሁፍ መጠይቅ መረጃ የተገኘው የጥናቱ ውጤት እንዳረጋገጠው በትብብራዊ የመማር ዘዴ በሙከራ ቡድን የተማሩ ተማሪዎች

በተለመደው ዘዴ በቁጥጥር ቡድን ከተማሩ ተማሪዎች የተሻለ ውጤት ማምጣታቸውን ነው፡፡ ይህም ትብብራዊ መማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን አመልክቷል፡፡

ሶስተኛው የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ለማጎልበት ካላቸው ሚና አኳያ የተደረጉ ምርምሮች Patricia,(2006) Hidi,SBoscolo(2007) Quirey,(2015) ናቸው፡፡ Patricia, (2006) ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎች ተነሳሽነት ለማሳደግ ያለውን ፋይዳ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሙያ ባደረጉት ጥናት ፈትሸዋል፡፡ የጥናታቸው ትኩረት በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች ተግባራትን ለማከናውን ባላቸው ተነሳሽነት፣ የመማር ውጤት ስኬታማነት እና ሳይቀሩ ክፍል መገኘታቸው ላይ ነው፡፡ በቅድመና ድህረ ሙከራ ጥናት በጽሁፍ መጠይቅ ተነሳሽነታቸውን፣ በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና የመማር ውጤታማነታቸውንና ከትብብራዊ ዘዴ የክፍል ትግበራ በፊትና በኋላ ሳይቀሩ ክፍል መገኘታቸው መረጃ በመሰብሰብ ተንትነው ውጤቱን ገልጸዋል፡፡ ውጤቱም ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን ተነሳሽነትና የመማርን ውጤት ስኬታማ ከማድረግ አኳያ ፋይዳው አዎንታዊ መሆኑን አረጋግጧል፡፡

Quirey, (2015) በትብብራዊ ዘዴ የመማር ማስተማር ብልሃቶች (ጅግሶው እና ማሰብ፣ ማጎዳኘት እና ማጋራት) ላይ የተመሰረተ የቋንቋ ተማሪዎችን የመማር ተሳትፎን ከማሳደግ አኳያ ያለውን ሚና የፈተሸ ጥናት ነው፡፡ የተማሪዎችን በግል ማሰብን፣ ጊዜ መጠበቅን ማሳደግ እና ተጋግዞ በመማር ላይ ያላቸውን ተሳትፎ በመፈተሸ ትብብራዊ ዘዴ ይህን በማሳካት በኩል ውጤታማ እንደሆነ አረጋግጠዋል፡፡ እንዲሁም Hidi,S&Boscolo, (2007) የመጻፍ ተነሳሽነት የተለያዩ ትርጉሞች በሚለው ጽሁፋቸው ከመጻፍ ችሎታ ጋር ተያያዥ ችግሮችን በተመለከተ ባደረጉት ጥናት እንደመሰረታዊ ችግር የሚታዩ ስነ ልቦናዊ አቀራረብ (ለተማሪው ተነሳሽነት ትኩረት አለማድረግ) እና ልማዳዊ የማስተማር ዘዴ እና ልማዳዊ ስርአተ ትምህርት (የመጻፍን ክሂል ለሌሎች ክሂሎች መሸጋገሪያ አድርጎ ማየት ወይም እንደ መጨረሻ ውጤት ብቻ አድርጎ መመልከት) ያነሳሉ፡፡ በጥናታቸውም ውጤት ላይ በሰጡት አስተያየት ለተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ እና የመጻፍ ተነሻስነት መሻሻል ምክንያት የሚሆኑትን ተግባቦታዊ የማስተማሪያ ዘዴዎችና ተነሳሽነትን የሚፈጥሩ አሳታፊ የማሰተማሪያ ተግባራት መጠቀም እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል፡፡

አራተኛው ትብብራዊ ዘዴ እና ልማዳዊ (መምህር ተኮር) ዘዴ የመጻፍ ችሎታን ለማጎልበት ካላቸውን ፋይዳ አኳያ በንንጽር የፈተሹ ጥናቶችን የሚመለከት ነው፡፡

ሙሀመድ (2016) የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል በትብብራዊ ዘዴ ማስተማር በሚል ርዕስ ዝቅተኛ የመጻፍ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ለማብቃት ታስቦ ባካሄዱት ጥናታቸው ትብብራዊ ዘዴ ከልማዳዊ ወይም ከመምህር ተኮር ዘዴ በተሻለ ሁኔታ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ከማሻሻል ረገድ ውጤታማ ዘዴ እንደሆነ አረጋግጠዋል፡፡ Bawun, (2007) ደግሞ ትብብራዊ ዘዴ ለመማር ማስተማርና በክፍል ውስጥ ለሚኖረው የትግበራ ሂደት ያለውን ሚና ከማስተማር ዘዴው አኳያ መርምረዋል፡፡ በአሜሪካ የህዝብ ትምህርት ቤት የአፍሪካ አሜሪካ እና ላታይ ተማሪዎች ላይ

የተደረገው ጥናት በልማዳዊ እና በትብብራዊ ዘዴ ማስተማር መካከል ባለው ውጤታማነት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ውጤቱም ትብብራዊ ዘዴ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ የሚያስችል ተግባቦታዊ ዘዴ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ በሁለቱ ዘዴዎች መካከልም ጉልህ ልዩነት መኖሩን ውጤቱ አመልክቷል፡፡

ቀጥሎ የቀረበው የሀገር ውስጥ ጥናት ሲሆን የማረው በግልና በቡድን መማር ላይ የተመሰረተ ጥናት ነው፡፡ ይህም ጥናት በማረው (1987 ዓ.ም.) በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል በሁለተኛ አመት ተማሪዎች ተተኳሪነት በግልና በቡድን በሚጻፉ በሳል ድርሰቶች ላይ በንጽጽር የተካሄደ ግምገማ ነው፡፡ ትኩረቱም በግልና በቡድን ሆነው ድርሰት በሚጽፉበት ወቅት ከሁለቱ ቡድኖች መካከል የተሻለ በሳል ድርሰት የጻፈ የቱ ነው? የሚለውን መለየት ላይ ነበር፡፡ የትግበራ ሂደቱ የተለያዩ ርዕሶችን በመስጠት ድርሰት እንዲጽፉ በማድረግ የተከናወነ ሲሆን ለመረጃ አሰባሰቡም ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የተጻፉ ድርሰቶች ተፈትሸው የተገኘው የጥናቱ ውጤት እንዳመለከተው በግል ድርሰት ከጻፉት ይልቅ በቡድን የጻፉት ውጤታማ መሆናቸውን አረጋግጧል፡፡

## 2.7 የጥናቱ ጽንሰ ሃሳባዊ ማእቀፍ

ይህ ጽንሰ ሃሳባዊ ማእቀፍ በዚህ የምርምር ሂደት ሊኖሩ የሚችሉ የትግበራ ሂደቶችን የሚጠቁም ነው፡፡ የአተገባበር ሂደቱ በትብብራዊ ዘዴ በአማርኛ የመጻፍን ችሎታ

ለማስተማር እና ለመማር ያለን ፍላጎት ለማጎልበት እነዚህን የትግበራ ሂደቶች መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ ጽንሰ ሃሳባዊ ማእቀፉ እንደሚከተለው ይብራራል፡፡

ϖ ትብብራዊ ዘዴ አላማው የግለሰብንና የቡድንን መማር ከግብ ማድረስ ነው፡፡ ይህንን አላማ ለማሳካት የአተገባበር ሂደቱ በአዎንታዊ መደጋገፍ ላይ ተመስርቶ፤ ግለሰባዊ ተጠያቂነት ኖሮት፣ ፊት ለፊት በመነጋገር እና በቡድናዊ መረካከብ ትብብራዊነትን ማሳደግ ይሻል፡፡ ማእቀፉ ይህን ሂደት ያመለክታል፡፡

ϖ የመጻፍ ችሎታ መነሳሳትንና አእምሯዊ ሂደትን የሚጠይቅ በመሆኑ ተማሪዎች ሊነሳሱ፣ ተደጋግፈው በመነጋገር፣ ምጋቤ ምላሽ በመሰጣጣት እና በመተማመን መስራት አለባቸው፤ ማእቀፉ ይጠቁማል፡፡

ϖ በትብብራዊ ዘዴ የመጻፍ ችሎታን ለማስተማር ሂደታዊ የጽህፈት ተግባራትን ማከናወን ችሎታውን ለማጎልበት የሚረዳ መሆኑን ማቀድን፣ ማርቀቅን፣ መከለስን፣ ማረም እና ማሳተም ትኩረት ይደረግባቸዋል፡፡ ንድፉ ይህን ያብራራል፡፡

ϖ በትብብራዊ ዘዴ የሚቀርበው የማስተማር የትግበራ ሂደት የተማሪዎችን ችሎታ ማጎልበት ስለሆነ መሳካት አለመሳካቱ በምዘና ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ስለሆነም ለመፈተሽ እንዲመች የመጻፍ ችሎታ ትምህርት አላባውያን እንደ መመዘኛ ቀርበዋል፡፡ ማእቀፉ ይህንን ያሳያል፡፡

ϖ ተነሳሽነት በመጻፍ ክሂል ትምህርት ውስጥ አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያደርስ ስለሚችል በትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመማር ውጤት ለማሳደግ በትብብር የመማር ሂደት ትኩረት ሊደረግበት እንደሚገባ ይጠቁማል፡፡

ϖ በአጠቃላይ ጽንሰ ሃሳባዊ ማእቀፉ በትብብራዊ ዘዴ ማስተማር በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ እና የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ ለውጥ እንዲመጣ የትኛውን ተግባር መቼና እንዴት መከናወን እንዳለበት የሚያብራራ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት
# የጥናቱ ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታ እና የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ የምርምሩንም

አላማ ከግብ ለማድረስ የሚሰበሰበው መረጃ የአተናተን ሂደቱ መጠናዊ ምርምር ላይ በመመስረት ከፊል ፍትነታዊ (Quasi-Experimental) ንድፍ ተተግብሯል፡፡

## 3.2 የተጠኝ ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄደው ት/ቤት ውስጥ የሚማሩ ጠቅላላ የ9 ኛ ክፍል ተማሪዎች 520 ሲሆኑ ለጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎችን ለመምረጥ ከተደለደለብት ክፍሎች ከሚማሩ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በቀላል ዕጣ ናሙና ዘዴን በመጠቀም 88(ሰማንያስምንት)ተማሪዎች የተመረጡ ናቸው ::

### 3.2.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጠው ትምህርት ቤት በደቡብ ምዕራብ ክልል በቤንች ሸኮ ዞን በቢፍቱ ከተማ አስተዳደር በቢፍ ሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ የንምና ዘዴ (Convenience sampling) የተመረጠ ሲሆን ይህም ትምህርት ቤት የተመረጠበት ምክንያት አጥኘው በመምህረነት እየሰራበት ያለ በመሆኑ መረጃዎችን ሊያገኝ ስለሚችል ነው ፡፡

### 3.2.2 የክፍል ደረጃ የናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጠው የክፍል ደረጃ 9ኛ ክፍል ሲሆን የጥናቱ ተተኳሪዎችም የ 9 ኛ ክፍል የአማረኛ ቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች ናቸው ፡፡ ይህም የክፍል ደረጃ ሊመረጥ የቻለው በሀገር ደረጃ የመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት እርከን የሚያበቃው ስምንተኛ ክፍል ላይ ሲሆን፣ የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት እርከን የሚጀምረው በዘጠነኛ ክፍል ነው፡፡ ስለሆነም፣ ተማሪዎች አንደኛ ደረጃን ሲጨርሱ ይዘውት የመጡት የመጻፍ ችሎታ ያለበትን ደረጃ እና ትምህርቱ የቀረበላቸውን ዘዴ በማረጋገጥ በሁለተኛ ደረጃ ሊማሩ የሚገባቸውን የይዘት ጥልቀት፣ መከተል የሚገባን የመማር ብልሃት እና የማስተማር ዘዴ ለመጠቆም ታስቦ ነው፡፡

### 3.2.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ 9 ኛ ክፍልን በማስተማር ላይ የሚገኙት መምህራን አራት በመሆናቸው አንዱ በቀላል እጣ ንሞና ዘዴ በጥናቱ እንዲካተት ተደረጓል ፡፡

### 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

በጥናቱ የሚተኮርባቸውን መሪ ጥያቄዎች በመመለስ፣አላማዎችን ለማሳካት መረጃዎች ያስፈልጋሉ፡፡ እነዚህም መረጃዎች የተገኙት ከተሳታፊ ተማሪዎች ነው፡፡ ከተሳታፊ ተማሪዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለመለካት ከተሰጠ የመጻፍ ችሎታ ፈተናና ተነሳሽነታቸውን ለመፈተሽ ከተሰራጨው የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በፍትነትና በቁጥጥር ቡድኖች በቅድመና በድህረ ትምህርት ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ የትግበራ ሂደቱ የፍትነት ቡድኑ በትብብራዊ ዘዴና የቁጥጥር ቡድኑ በተለመደው ዘዴ ትምህርቱን ሳይማሩና ከተማሩ በኋላ በተገኘው የፈተና ውጤትና ተነሳሽነታቸውን ለመፈተሽ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘውን ውጤት በማነጻጸር ልዩነቱ ተፈትሾዋል፡፡

#### 3.3.1. የመጻፍ ችሎታ ፈተና

በዚህ ጥናት ተግባራዊ ከተደረጉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አንዱ ፈተና ነው፡፡ በጥናቱ የሚሳተፉ ሁለቱ ቡድኖች (ፍትነታዊ እና የቁጥጥር) በክፊል ሙከራዊ ንድፍ መሰረት የመጻፍ ችሎታቸውን ለመፈተሽ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍና መርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱ የመጻፍ ችሎታ ትምህርት ይዘቶችን መነሻ በማድረግ ለሁለቱም ቡድኖች ሳይለዩ የመጻፍ ችሎታ አላባውያን (ንኡሳን ችሎታዎች) መመዘኛነት ላይ የተመሰረተ አራት ክፍሎች ያሉት የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና ጥያቄዎች ተግባራዊ ሆኗል፡፡

የቅድመ ትምህርት ፈተና የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት የመፈተሽ አላማ ያለው ሲሆን ከልምምዱ በፊት በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የሆነ የችሎታ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ድህረ ትምህርት ፈተናው ተማሪዎች ከልምምዱ በኋላ ያመጡትን ውጤት መነሻ በማድረግ በቅድመ ትምህርት የታየውን የመጻፍ ችሎታ ለውጥ ለመለካት ነው፡፡ ይሄውም በቅድመ ትምህርት በተወሰደው መረጃ የሁለቱም ቡድኖች ደረጃ ከተለየ በኋላ፣ የድህረ ትምህርት ውጤትም ተወስዶ፣ በቅድመ ትምህርት ከታየው ውጤት ጋር ምን ያህል እንደተዛመደ ወይም ልዩነት እንዳሳየ ለማረጋገጥ ነው፡፡

የፈተናውን ተገቢነትና አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ለተማሪዎች ከመቅረቡ በፊት በአማካሪ፣ በደረጃውና በሌሎች ሁለት የሁለተኛ ዲግሪ ባላቸው መምህራን ተገምግሞ ከቀረቡ በኋላ፣ አንዳንድ ጥያቄዎች የመጻፊያ ርዕሶች የተማሪው የመማር አከባቢ ያገናዘቡ እንዲሆኑ

ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪ የቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና በዋናው ጥናት ተተኳሪ ባልሆኑ 30 በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሙከራ (pilot test) ተደርጎ በክሮንባክ አልፋ አስተማማኝነት መገመቻ ተረጋግጧል፡፡ የአስተማማኝ ደረጃ ውጤቱም የመጻፍ ችሎታ የፈተና .950 ሆኗል፡፡ ይህም ከፍተኛ በመሆኑ አስተማማኝ ሆኗል(አባሪ 10ን ይመልከቱ)፡፡ የሙከራ ፍተሻ፣ ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች እርማት በሶስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተከናውኗል፡፡ የተገኘው ወጤት በክሮንባንክ አ ል ፋ አስተማማኝነ ት መገመቻ ተቀምጧል፡፡

### 3.3.2. የጽሁፍ መጠይቅ

በዚህ ጥናት ትኩረት ከተደረግባቸው ተላውጦች አንዱ ተማሪዎቸ ለመጻፍ ያላቸውን ተነሳሽነት የሚፈትሽ ሲሆኑ ሶስቱን የስነ ልቦና ተነሳሽነት ገጽታዎች ላይ ያተኩራል፡፡ የጽሁፍ መጠይቁም ትብብራዊ ዘዴ በተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ላይ የራሱ ተጽእኖ እንዳለው ለማረጋገጥና ተነሳሽነታቸውን ለመመርመር በትብብራዊ ዘዴ ከመማራቸው በፊትና ከተማሩ በኋላ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የተዘጋጀው ከአሸልይ (2012) አካዳሚያዊ የተነሳሽነት ጥያቄዎች ተሻሽሎ በመውሰድ ነው (ከአባሪ 1 ይመልከቱ)፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል የተማሪውን ዳራ እና ሁለተኛው ክፍል በጥናቱ አላማ ላይ የተመሰረቱ አማራጭ ምላሽ ያለው (በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ መወሰን እቸገራለሁ፣ አልስማም፣ በጭራሽ አልስማማም) ሃያ አምስት ዝግ ጥያቄዎችን የያዘ ክፍል ነው፡፡ መጠይቁ በአጥኚው ተዘጋጅቶ ለተማሪዎች ከመቅረቡ በፊት በአማካሪ፣ በሁለት የሁለተኛ ዲግሪ ባላቸውና በደረጃው መምህራን ከተገመገመ በኋላ በተማሪዎች እንዲሞላ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪ የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቁ የጥናቱ ተተኳሪ ባልሆኑ ሰላሳ የ9ኛF ክፍል ተማሪዎች እንዲሞሉ በማድረግ ቅድመና ድህረ ሙከራ ፍተሻ (Pilot Study) ተደርጎ በክሮንባንክ አስተማማኝነት መገመቻ ተረጋግጧል፡፡ በተካሄደውም በናሙና ሙከራ ጥናት የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት .823 ሆኗል፡፡ ይህም የጽሁፍ መጠይቅ አስተማማኝ መሆኑን አመልክቷል፡፡ ከሙከራ ፍተሻ ጥናቱ በተገኘው ውጤት መሰረት ውስጣዊ ተዛምዷቸው የመለካት አቅማቸው ዝቅተኛ ሊሆኑ ይችላሉ፤ የተባሉ ጥያቄ 7፣ 8 እና 13 ላይ የተወሰነ ማሻሻያ (አባሪ 3 ን ይመልከቱ) ተደርጎባቸዋል፡፡

### 3.4. የማስተማሪያ ብልሃቶች

በዚህ የጥናት ሂደት ከቅድመ ፈተና በኋላ ለድህረ ፈተና የሚያዘጋጃቸው አጫጭር ማስታወሻዎች ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም የማስተማሪያ ውሁዳሀድ ዝግጅት የደረጃውን መማሪያ ማስተማሪያ መጽሃፍ እና መርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶችን፣ በትብብራዊ ዘዴ የማስተማሪያ ብልሃቶች፣ የመጻፍ ችሎታ ንኡሳን ችሎታዎችንና የመጻፍ ችሎታ ሂደቶችን ባገናዘበ መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡ ውሁዳሀዱ የመጻፍ ችሎታ ትምህርት ይዘቶችን አካቶ ከድርሰት የአጻጻፍ ስልቶች በተራኪ፣ በገላጭ እና ምክንያታዊ ትስስር ላይ በተመሰረቱ ጽሁፎች ነው፡፡ ውሁዳሀዱ ለቁጥጥርና ለፍትነታዊ ቡድኑ በተመሳሳይ መልኩ የቀረብ ሲሆን የመማር ማስተማር አቀራረብና የትግበራ ብልሃቶች ሂደት የተለያየ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ የፍትነት ቡድኑ ተማሪዎች የትግበራ ሂደቱ በትብብር ቡድን ላይ ይመሰረታል፡፡ የመጻፍ ክሂል ሂደታዊ ደረጃዎችን ከቡድን አጋሮች ጋር በመሆን ርዕስ መምረጥ፣ በውይይት ሃሳብ ማመንጨትና ቢጋር ማዘጋጀት በጋራ አከናውነዋል፡፡ የማርቀቅ ሂደቱን በግል ከጻፉ በኋላ የመከለስና ምጋቤ ምላሽ የመለዋወጥ ትግበራ በቡድን በማከናወን የመጨረሻውን ጽሁፍ እንዲጽፉ ተደርጓል፡፡ የቁጥጥር በቡድኑ የመማር ማስተማሩ ሂደት በተለመደው መንገድ የተተበገረ ሲሆን አጠቃላይ ሂደቱ በተቀመጠለት የትምህርት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ተከናውኗል (አባሪ16 ን ይመልከቱ)፡፡

### 3.5. የጥናቱ ሂደት

ከጥናቱ ትግበራ አስቀድሞ የጥናቱ አካላይ ለሆነው ትምህርት ቤት ከጅማ ዩኒቨርሲቲ የጥናቱን አላማ አስመልክቶ ደብዳቤ ተጽፏል፡፡ ትምህርት ቤቱ ደብዳቤው ደርሶት ፈቃደኛ በመሆኑ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር አካላት፣ ከትምህርት ክፍሉ መምህራን፣ ከአሰልጣኝ መምህሩና ከጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ጋር በጥናቱ አላማ ላይ ውይይት ተደርጎ ፈቃደኛ መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡፡

ፈቃደኛ ከሆኑ በኋላ እዚያው ትምህርት ቤት በጥናቱ ተሳታፊ ካልሆኑ ክፍሎች በዕጣ አንዱ ተመርጦ ለዋናው ጥናት መረጃ ማግኛና መንደረደሪያ እንዲሆን በቅድሚያ የናሙና ሙከራ ጥናት ተደርጓል፡፡ በናሙና ሙከራ ጥናቱ አተገባበር፣ የዋናው ጥናት ንድፍ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችንና የአተገባበር ሂደቱ በተመለከተ ከአማካሪ ጋር ውይይት ተደርጎና እርማቶች ከተደረጉ በኋላ የመጨረሻው ዝግጅት ተይዞ ወደ ዋናው ትግበራ ተገብቷል፡፡

የስልጠና ሂደቱን በተመለከተ አሰልጣኝ መምህሩ ወደ ክፍል ከመግባታቸው በፊት የፍትነት ቡድኑን የክፍል ውስጥ ትግበራንና በትብብራዊ ዘዴ ምንነት፣ ከልማዳዊ ዘዴ ጋር ያለውን ልዩነት፣ በዘዴው መሰረታዊ መርሆች፣ በአተገባበር ብልሃቶች፣ የዘዴውን ጠቀሜታ ፣በዘዴው የመምህርንና የተማሪዎች ሚና እና የመተግበሪያ ብልሃቶችን እንዲሁም በክፍል ውስጥ የትግበራ ዕቅዱን በተመለከተ በአጥኚው ተዘጋጅቶ በአማካሪ ተገምግሞ በቀረበው የማስተማሪያ ሂደት ትግበራ ማኑዋል ላይ ለስድስት ሰዓታት ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡ ለአተገባበር ሂደት እንዲመቻቸው የስልጠናው ማኑዋል ኮፒ ለመምህሩ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ የፍትነት ቡድኑ ተማሪዎችም በዘዴው የአተገባበር ሂደት እንግዳ እንዳይሆኑና ግራ እንዳይጋቡ ሚናቸውንና አመዛዘኑን በተመለከተ ሁለት ሰዓት የፈጀ ውይይት ነክ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከዚያ በኋላ ለመረጃው አሰባሰብና ለመማር ማስተማር ሂደት አመቺነት ትምህርቱ በመደበኛው ክፍል በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜና ከተማሪዎችና አሰልጣኝ መምህር ጋር በተደረገ ውይይት በተቃራኒ ፈረቃ አንድ ተጨማሪ ክፍል ጊዜ ተመድቦ እንዲከናወን ተደርጓል፡፡

የቡድን አመሰራረት፡ አስቀድሞ በቡድን አመሰራረቱ ስብጥራዊነት ላይ ተገቢ ግንዛቤ የተፈጠረ መሆኑን በማረጋገጥ በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ተግባራትን በትብብር ማከናወን እንዲችሉ አቦዳደኑ በአሰልጣኝ መምህሩ በተማሪዎች ዳራና የትብብራዊ ዘዴ መርህ በሚፈቅደው መሰረት ስብጥራዊነት ለመጠበቅ በተማሪዎች ውጤት (ባላቸው ችሎታ)፣ እድሜ፣ ጾታ፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖትና ብሄር ላይ ተተኩሯል፡፡

በመረጃ አሰባሰብ ሂደት በሚፈጠሩ አንዳንድ ክፍተቶች አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳይፈጠር፣ የጥናቱም ውጤት ተዓማኒነትና ተገቢነት የጎደለው እንዳይሆን ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ ስለሆነም ከጥናቱ ተሳታፊዎች በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካይነት መረጃ የመሰብሰብ ሂደቱ አጥኚው በተገኘበት ቦታና ጊዜ ተከናውኗል፡፡

ዋናው ጥናትም በ6/6/2015 ዓ.ም ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት ፈተና ተፈትነውና የመጻፍ ተነሳሽነት መፈተሻ የጽሁፍ መጠይቅ ሞልተው ተጀምሯል፡፡ የተሰበሰበው የፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ መረጃ በትክክል መከናወኑንና የአሞላል ስህተት እንዳይፈጠር የማጣራት ስራ ተሰርቷል፡፡ ሁለቱ ተተኳሪ ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ፈተና ከተፈተኑና የመጻፍ ተነሳሽነት መፈተሻ የጽሁፍ መጠይቅ ከሞሉ በኋላ በቀላል የዕጣ ናሙና የፍትነትና የቁጥጥር ቡድን ተብለው ተለይተው ተመድበዋል፡፡

የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር አተገባበሩ የደረጃውን መርሃ ትምህርት መሰረት ያደረገ የክፍለ ጊዜ አከፋፈል ተክትሎ የመደበኛውን ሁለት ክፍለ ጊዜና በተጨማሪ በአሰልጣኝ መምህሩና በጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች መስማማት አንድ ተጨማሪ ክፍለ ጊዜ በተቃራኒ ፈረቃ ተመቻቾ አጠቃላይ መርሃ ግብሩ ለአራት ሳምንታትና አንድ ተጨማሪ ቀን ወይም አስራ ሶስት ክፍለ ጊዜ የሽፈነ ትምህርት ተሰጥቷቸዋል፡፡ በክፍል ውስጥ በነበረው የትግበራው ሂደት ትኩረት የተደረገባቸው የትምህርት ይዘቶች አረፍተ ነገር፣ ስርአተ ነጥብ፣ሰዋስውና አንቀጽ ሲሆኑ የመጻፍ ችሎታ ንኡሳን ችሎታዎችን (የሃሳብ አደረጃጀት፣ የአጻጻፍ ስርአት፣ ሰዋስው፣ የቃላት አጠቃቀምና ይዘት) እና የመጻፍ ሂደትን (ማቀድ፣ ሃሳብ ማመንጨት፣ አስተዋጽኦ መንድፍ (ቢጋር)፣ መከለስና እንደገና መጻፍ) ያገናዘበ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር የአመዛዘን ሂደቱ የጽሁፍ ችሎታ መተግበሪያ ጽሁፎችና በትብብራዊ ዘዴ ብልሃቶች ላይ የተመሰረተ የተማሪዎች በግል በራሳቸው ቡድን የሚደረግ አቻ ምጋቤ ምላሽ፣ የቡድን ስራ አቻና የመምህር ምጋቤ ምላሽ፣ የቡድን ስራ (በቡድን የተዘጋጀ የተማሪዎች የአንቀጽና የድርሰት ጽሁፎች) የክፍል ውስጥ አቅርቦትና የድህረ ትምህርት ፈተና ናቸው፡፡

አጠቃላይ የክፍል ውስጥ ልምምድ ከየካቲት 9/2015 ዓ.ም፣ እስከ መጋቢት 7/2015 ዓ.ም ባለው ጊዜ ተከናውኖ የድህረ ትምህርት ፈተናው መጋቢት 8/2015 ዓ.ም. ተሰጥቷል፡፡ በጥናቱ ሂደት ከተሳታፊዎቹ ጋር ጤናማ ግኑኝነት እንዲኖር፣ የሚሰበሰበው መረጃ እንዳይዛባ፣ ለተገቢነቱንና ለአስተማማኝነቱ ጥናቱን በተቀመጠለት ጊዜ ለማስኬድ ጥንቃቄ ተደርጓል፡፡

## 3.6. የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች

በጥናቱ ተሳታፊ ከሆኑ ተማሪዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተናና የመጻፍ ተነሳሽነት መፈተሻ ጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መጠናዊ መረጃዎች ትክክለኛነታቸው ለማረጋገጥ መረጃዎችን የመለየት፣ የማጣራት፣ የማደራጀትና ኮድ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡

የተተኳሪ ቡድን ተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለመለካት በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና እንዲሁም የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን ለመፈተሽ ከተሰራጨው የጽሁፍ መጠይቅ ከተሰበሰበው መረጃ የተገኘው አማካይ ውጤት እሙኖች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ የስርጭት ወጥነታቸው በገላጭ ስታትስቲክስ በተያያዥ አምድ ግራፍ ተሰልቷል፡፡ በፍትነትና በቁጥጥር ቡድኖቹ መካከል የመጻፍ ችሎታ የፈተና ውጤትና የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን ለመፈተሽ ከተሰራጨው የጽሁፍ መጠይቅ መረጃ በተገኘው አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩ በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ( በባዕድ ናሙና ቲ ቴስትና በንጥል ልይይት ትንተና) በማስላት ውጤቱ ተቀምጧል፡፡

# ምዕራፍ አራት
# የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

## 4.1. የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እና የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማጎልበት ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው? እና የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ለማሳደግ ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው? የሚሉ ሲሆኑ ጥያቄዎቹን ለመመለስ በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስትና በባለብዙ ተላውጦ ልይይት ትንተና ስልቶች ተተንትነዋል፡፡ ለጥናቱ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በተደረጉ ትንታኔዎች ላይ ለስታትስቲካዊ ስሌቶቹ ፍተሻ የጉልህነት ደረጃ $p < 0.05$ ነው፡፡

በዚህ መሰረት የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እና የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ ለመፈተሽ የመጀመሪያው ጥያቄ የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታን ለማጎልበት ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው? የሚለው ሲሆን፣ ይህን ለማረጋገጥ የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑ የቁጥጥርና የፍትነት ቡድን ተማሪዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ያላቸው የመጻፍ ችሎታና ያስመዘገቡት ውጤት በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 4.1፡ - የቁጥጥርና የፍትነት ቡድን የቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ትንተና በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት

| ቡድን | ናሙና n | አማካይ m | መደበኛ ልይይት | የቲ ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የፍትነት | 44 | 61.496 | 10.069 | 3.060 | 86 | .003 |
| የቁጥጥር | 44 | 53.019 | 15.372 | | | |

በሰንጠረዥ 4.1 የቀረበው የውጤት ትንትና እንደሚያመለክተው የፍትነት ቡድን ተሳታፊ ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤታቸው (m = 61.496) 49 እና የቁጥጥር ቡድን ተሳታፊ ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤታቸው (m = 53.019) ሆኗል፡፡ እንዲሁም የመደበኛ ልይይት (standard devation) የፍትነት ቡድኑ አማካይ ውጤት (10.069) ሲሆን የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት (15.372) ሆኗል፡፡ ይህም አማካይ ውጤቶቹ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ልዩነት ያለው መሆኑን ያሳያሉ፡፡ በቡድኖቹ መካከል ያለውን የአማካይ ውጤት ልዩነት .003 መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥም ድምዳሜያዊ ስታቲስትክስ (inferential statistics) መጠቀም የግድ ይላል፡፡

ስለሆነም በቡድኖቹ ተሳታፊዎች መካከል የመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤት .003 ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ በባዕድ ናሙና ቲቴስት ተፈትሾ በ 86 የነጻነት ደረጃ የቲ ዋጋ = 3.060,የፒ ዋጋ = .003 ሆኗል፡፡ ይህም የሚያመለክተው በፍትነትና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል ያለው የመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት ያለው መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም የፒ ዋጋ =.003 ከመቁረጫ ነጥቡ $p < 0.05$ አንሶ ተገኝቷል፡፡

የጥናቱ ሁለተኛው ጥያቄ የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ለማሳደግ ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው? የሚለው ነው፡፡ ይህን ለማረጋገጥ የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑ የቁጥጥርና የፍትነት ቡድን ተማሪዎች በቅድመ ትምህርት ያላቸው የመጻፍ ተነሳሽነት ለመፈተሽ የጽሁፍ መጠይቅ ተሰራጭቷል፡፡ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት በቅደም ተከተል ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 4.2፡- የቁጥጥርና የፍትነት ቡድን የቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት ትንትና በባዕድ ቲ-ቴስት

| ቡድን | ናሙናአማካይመደበኛ | የቲ ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ | |
|---|---|---|---|---|---|
| (n) | (m) | ልይይት | | | |
| የፍትነት 44<br>የቁጥጥር 44 | 4.246 4.022 | .270.424 | 2.953 | 86 | .004 |

በሰንጠረዥ 4.2 ከቀረበው መረጃ የሚገነዳው የሁለቱ ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት የፍትነት ቡድን (4.246) ሲሆን፣ የቁጥጥር ቡድኑ (4.022) ነው፡፡

የመደበኛ ልይይት ውጤት የፍትነት ቡድኑ (.270) ሲሆን የቁጥጥር ቡድኑ (.424) ነው፡፡ ውጤቱም በሁለቱ ቡድኖች መካከል ልዩነት ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡ ቢሆንም በሁለቱ ተሳታፊ ቡድኖች መካከል ውጤቱን መነሻ በማድረግ ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተስልቶ የመጣው ውጤት በ86 የነጻነት ደረጃ የቲ ዋጋ = 2.953, የፒ ዋጋ = .004 ሆኗል፡፡ የፒ ዋጋ ከመቁረጫው ውጤት አንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም በሁለቱ ቡድኖች መካከል .004 ልዩነት ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡

በቅድመ ትምህርት ፈተናና የጽሑፍ መጠይቅ ውጤቶች ትንተና ወቅት በባዕድ በቲ-ቴስት ተስልተው ውጤቶች የፒ ዋጋ = .003 እና = .004 ሆነዋል፡፡ ይህ ደግሞ ከመቁረጫ ነጥቡ $p$ < 0.05 ያነሰ በመሆኑ ጉልህ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ስለሆነ ከመነሻው ጀምሮ ጉልህ ልዩነት የነበራቸው ውጤቶች በመመዝገባቸው በልዩነቶቹ ምክንያት ሊኖር የሚችለውን ተጽዕኖ ለመቆጣጠር የሁለቱም ቡድኖች የድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተናና የመጻፍ ተነሳሽነት መፈተሻ የጽሑፍ መጠይቅ ውጤቶች በንጥል ልይይት (ANCOVA) ተተንትኖ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 4.3፡- የቁጥጥርና የፍትነት ቡድን የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት በባለ አንድ ልይይት ትንተና (ANCOVA)

| ቡድን | ናሙና n | አማካይ m | መደበኛ ልይይት | የF ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህት ደረጃ | የጥንካሬ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የፍትነት | 44 | 71.076 | 14.559 | 18.574 | 1.86 | .001 | .179 |
| የቁጥጥር | 44 | 56.864 | 14.240 | | | | |

18.574 1,86 .001 .179

የቁጥጥር 44 56.864 14.240

በሰንጠረዥ 4.3 የቀረበው የንጥል ልይይት ትንተና ውጤት እንደሚያመለክተው የድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤት የፍትነት ቡድን (71.076) እና የቁጥጥር ቡድን (56.864) ሆኗል፡፡ የመደበኛ ልይይት የፍትነት ቡድኑ አማካይ ውጤት (14.559) ሲሆን የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት (14.240) ሆኗል፡፡ ይህም በሁለቱም አማካይ ውጤቶች መካከል ልዩነት ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡ ቢሆንም ይህን ገላጭ መረጃ በማየት ልዩነት አለ፤

ብሎ ከመደምደም ይልቅ የልዩነቱን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ድምዳሜያዊ ስታቲስትክስ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡

ስለሆነም በተስተካካይ የመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ በባለ ሁለት ጫፍ (sig (2-tailed)) ተሰልቶ ውጤቱ F(1,86) = 290.320፣ የፒ ዋጋ = .001፣ የጥንካሬ ደረጃው .179 ሆኗል፡፡ ይህም የሚያመለክተው በፍትነትና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል ያለው የመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤት .001 ያለው መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም የፒ ዋጋ= .001 ከመቁረጫ ነጥቡ $p < 0.05$ አንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህ የአማካይ ውጤቱ ጉልህ ልዩነት የሚያረጋግጠው የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል 17.9 በመቶ አዎንታዊ ሚና ያለው መሆኑን ነው፡፡

በቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ወቅት በቲ-ቴስት ተሰልቶ ውጤቱ የፒ ዋጋ= .004 ከመቁረጫ ነጥቡ $p < 0.05$ ያነሰ በመሆን ጉልህ ልዩነት ያለ መሆኑን በማሳየቱ ከትምህርት ትግበራ በኋላ እንደወረደ ቢሰላ የቀደመው ጉልህ ልዩነት ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ በዚህም ሊኖር የሚችለውን ተጽዕኖ ለመቆጣጠር የሁለቱም ቡድኖች የድህረ ትምህርት የጽሑፍ መጠይቅ ውጤቶች በንጥል ልይይት (ANCOVA) ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 4.4፡- የቁጥጥርና የፍትነት ቡድን የድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት በንጥል ልይይት ትንተና

| ቡድን | ናሙና (n) | አማካ (m) | መደበኛ ልይይት | የF ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ | የጥንካሬ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የፍትነት | 44 | 4.576 | 0187 | 37.838 | 1,86 | .001 | .308 |
| የቁጥጥር | 44 | 4.134 | .4174 | | | | |

በሰንጠረዥ 4.4 የቀረበው የንጥል ልይይት ትንተና ውጤት እንደሚያመለክተው የድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት የፍትነት ቡድን (4.576) እና የቁጥጥር ቡድን (4.134) ሆኗል፡፡ የመደበኛ ልይይት የፍትነት ቡድኑ አማካይ ውጤት (.187) ሲሆን የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት (.4174) ሆኗል፡፡ ይህም በአማካይ ውጤቶች መካከል ልዩነት ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡ ቢሆንም ይህን ገላጭ መረጃ በማየት ልዩነት አለ፤ ብሎ

ከመደምደም ይልቅ የልዩነቱን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ድምዳሜያዊ ስታቲስትክስ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡

ስለሆነም በተስተካካይ የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ በባለ ሁለት ጫፍ (sig (2-tailed)) ተሰልቶ ውጤቱ F(1,86)= 37.838፣ የፒ ዋጋ= .001፣ የጥንካሬ ደረጃውም .308 ሆኗል፡፡ ይህም የሚያመለክተው በፍትነትና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል ያለው የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት ያለው መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም የፒ ዋጋ= .001 ከመቁረጫ ነጥቡ $p < 0.05$ አንሶ ተገኝቷል፡፡ በአማካይ ውጤቶች የታየው ጉልህ ልዩነት የሚያረጋግጠው የትብብራዊ ዘዴ 30.8 በመቶ ያህል የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን ለማሻሻል ያለውን አዎንታዊ ሚና ነው ፡፡

በአጠቃላይ በጥናቱ ሂደት በድህረ ትምህርት ከመጻፍ ችሎታ ፈተናና ከመጻፍ ተነሳሽነት መፈተሻ ጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መጠናዊ መረጃዎች የትንተና ውጤት የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነትን ከማጎልበት አኳያ ሚናው አዎንታዊ መሆኑን አሳይተዋል፡፡

## 4.2. የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታ እና የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ አላማውን ለመፈተሽ የቀረቡ የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታን ለማጎልበት ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው? እና የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ለማሳደግ ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው? የሚሉት ሲሆኑ ተሳታፊዎችን በሁለት ቡድን በመክፈል ከፊል ፍትነታዊ ንድፍ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ጥያቄዎቹን ለመመለስ በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መጠናዊ መረጃዎች በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታቲክስ ተተንትነዋል፡፡

የትንተናው ውጤት እንዳመለከተው በድህረ ትምህርት ወቅት በትብብራዊ ዘዴ ታግዘው የመጻፍ ችሎታ ትምህርት የክፍል ውስጥ ልምምዳቸውን ያደረጉ የፍትነት ቡድን ተማሪዎችና በተለመደው ዘዴ የተማሩ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት F(1,86) = 18.574፣ የፒ ዋጋ = .001፣ የጥንካሬ ደረጃ .179 ወይም 17.9% ሆኗል፡፡ ይህም የሚያመለክተው በፍትነትና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል ያለው

የመጻፍ ችሎታ አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት ያለው መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም በድህረ ትምህርት ወቅት በትብብራዊ ዘዴ ታግዘው የመጻፍ ችሎታ ትምህርት የክፍል ውስጥ ልምምዳቸውን ያደረጉ የፍትነት ቡድን ተማሪዎችና በተለመደው ዘዴ የተማሩ የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የተነሳሽነት መፈተሻ የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት አማካይ F(1,86) = 37.838፣ የፒ ዋጋ = .001፣ የጥንካሬ ደረጃ .308 ወይም 30.8% ሆኗል፡፡ ይህም በቡድኖች መካከል የተነሳሽነት ልዩነት ጉልህ መሆኑን አሳይቷል፡፡

ከድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተናና የመጻፍ ተነሳሽነት መፈተሻ የጽሁፍ መጠይቅ አማካይ ውጤት ማጠቃለያ በመነሳት በትብብራዊ ዘዴ ታግዞ የክፍል ውስጥ ልምምድ ያደረገውን ቡድን (የፍትነት ቡድንን) ዘዴው የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ አስችሎታል፡፡ ይህም ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነትን ከማሳደግ አኳያ ፋይዳ ይኖረው ይሁንን? የሚለውን ጥያቄ ጥናቱ ዘዴው አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን በማረጋገጥ መልሷል፡፡

የዚህ ጥናት ውጤት ትብብራዊ ዘዴ የመማር ብቃት ለማሳደግ ካለው ፋይዳ አኳያ ከተጠኑ ከዩስናን (2018) እና ከትራን (2013) ከንድፈ ሃሳባዊ አተያይ የጥናት ውጤት ጋር ይደጋገፋል፡፡ ዩስናን (2018) በትብብራዊ ዘዴ ንድፈ ሃሳባዊ አተያይ ላይ ባተኮረ ጥናታቸው ትብብራዊ ዘዴ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በአእምሮታዊ፣ ባህሪያዊ እና ማህበራዊ ትስስራዊ እድገት ላይ ያለውን ሚና ተመልክተዋል፡፡ የሰነድ ፍተሻ በማድረግ ይፋ ባደረጉት ውጤት ተማሪዎች በትብብራዊ ዘዴ ሲማሩ ትምህርታዊ ክሂላቸውን በማሳደግና ማህበራዊ ተራክቦ በመፍጠር የመማር ብቃታቸውን የማጎልበት ፋይዳ ያለው መሆኑን አመልክቷል፡፡ ይህም በተማሪዎች መካከል የመወያየት፣ የመከራከር፣ የመተማመን፣ ሃሳባቸውን በነጻነት መግለጽ፣ ሌሎችን የማዳመጥና የትግበራ መርሆ ተማሪዎች በመማር ውጤታቸው ስኬታማ እንዲሆኑ አስተዋጽኦ ማድረጉን አረጋግጠዋል፡፡ በዚህም ጥናት በዘዴው የተማሩ የፍትነት ቡድን ተሳታፊ ተማሪዎች በመጻፍ ችሎታ ትምህርት ወቅት መማራቸውን በትብብር በማድረጋቸው ውጤታማ ሆነዋል፡፡

ትራን (2013) ንድፈ ሃሳባዊ አተያይ ጥናታቸው ልማዳዊ እና ትብብራዊ ዘዴ በተማሪዎች የመማር ውጤት ላይ የሚኖራቸውን አዎንታዊ ተጽዕኖ በማነጻጸር ይፋ ባደረጉት ውጤት ትብብራዊ ዘዴ ሚዛናዊ፣ ምክንያታዊና በተግባር የተፈተነ ዘዴ ስለሆነ በተማሪዎች የመማር ሂደት ትምህርታዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊና ስነልቦናው ውጤት የማምጣት ፋይዳ ያለው መሆኑን አሳይተዋል፡፡ በተጨማሪ በትብብራዊ ዘዴ በተማሩና በልማዳዊ ዘዴ

በተማሩ መካከል ጉልህ የውጤት ልዩነትም መኖሩን አመልክተዋል፡፡ ይህም ጥናት ትብብራዊ ዘዴ ከተለመደው ዘዴ ይልቅ የተማሪዎችን መማር በማሻሻል የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን የማሳደግ ፋይዳ ያለው መሆኑን አረጋግጧል፡፡

የጥናቱ ግኝት ከቫይጎቲስክ ማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ መማር ማህበራዊ ነው፤ እውቀት የሚገነባው በተማሪዎች መካከል በሚኖረው ማህበራዊ ተራክቦ ነው ከሚለው ከሆርመር (2007) እና ላም.ቢ.ኤች. (2013) ጥናትም ጋር ይስማማል፡፡ በጥናታቸው ትብብራዊ ዘዴ ትኩረቱ ማህበራዊ ተራክቦን በማሳደግ አእምሮአዊና ስሜታዊ እውቀትን መገንባት እንደሆነ አረጋግጠዋል፡፡ ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ተማሪዎች በትብብራዊ ዘዴ በክፍል ውስጥ የመጻፍ ችሎታ ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ የክፍል ውስጥ ተግባራትን በመወያየት፣ በመከራከር፣ በመተማመንና በመደጋገፍ ላይ ተመስርተው ስላከናወኑ የመማር ውጤታቸውን ለማሻሻል ምቹ አጋጣሚ መፍጠሩ ነው፡፡ በዚህም ጥናት ተማሪዎች በትብብራዊ ዘዴ የትግበራ ብልሃቶች ታግዘው በመመራቸው ውጤታማ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

ሌላው የዚህ ጥናት ውጤት በጥናታቸው ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በመጻፍ ችሎታ ትምህርት የክፍል ውስጥ ትግበራ ላይ ያላቸውን ተነሳሽነት ለማሻሻል፣ በመጻፍ ሂደት ሃሳብ የማመንጨት እና በአጻጻፍ ወቅት የሰዋስውን እውቀት ለማጎልበት ተመራጭና አዎንታዊ ፋይዳ ያለው መሆኑን ካረጋገጠው ከአስታርና (2011) እና ከሜላዊት (2015) ጥናት ውጤት እና (ዘነበች፣ 2011 ዓ.ም.) በትብብር መማር የመጻፍ ችሎታን ለማሻሻል ያለውን ሚና በፈተሸው ጥናታቸው የጥናቱ ውጤት እንዳረጋገጠው በትብብር የመማር ዘዴ በሙከራ ቡድን የተማሩ ተማሪዎች በተለመደው ዘዴ በቁጥጥር ቡድን ከተማሩ ተማሪዎች የተሻለ ውጤት ማምጣታቸው ዘዴው የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማጎልበት አዎንታዊ ሚና ያለው መሆኑን አመልክቷል ከሚለውም ጥናትም ውጤት ጋር ይስማማል፡፡

በተጨማሪ ይህ ጥናት ውጤቱ ከፓትሪቺያ (2006) ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ለማሳደግ ካለው ሚና አኳያ ባደረጉት ጥናታቸው ዘዴው ተማሪዎች ቡድናዊ ግብ እንዲያሳኩና በመካከላቸው አዎንታዊ መደጋገፍ በመፍጠር የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ አስችሏቸዋል፤ ከሚለውም ውጤት ጋር ይደጋገፋል፡፡ በዚህም ጥናት ተማሪዎች በመማር ሂደታቸው ግለሰባዊ ኃላፊነት ተቀብለው እንዲማሩ ስለተደረገ በመካከላቸው የነበረው አዎንታዊ መረካከብና መደጋገፍ የመጻፍ ችሎታቸውን ብቻ ሳይሆን የመማር ተነሳሽነታቸውም ጭምር እንዲጎለብት አድርጓቸዋል፡፡

በአጠቃላይ በድህረ ትምህርት ወቅት ከመጻፍ ችሎታ ፈተናና ከመጻፍ ተነሳሽነት መፈተሻ ጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው የንጥል ልይይት ትንተና አማካይ ውጤት በትብብራዊ ዘዴ ታግዘው የመጻፍ ችሎታ ትምህርት የክፍል ውስጥ ልምምድ ያደረጉት የፍትነት ቡድን ተሳታፊዎች በተለመደው ዘዴ ከተማሩ የቁጥጥር ቡድን ተሳታፊዎች በተሻለ መልኩ ውጤት ማስመዝገብ ችለዋል፡፡ ይህም ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት ለማጎልበት ፋይዳ ያለው መሆኑን አረጋግጧል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታ እና የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ በጥናቱ ሂደት የተሳታፊ ተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነትን ለመፈተሽ በትብብራዊና በተለመደው ዘዴ እንዲማሩ በሁለት ቡድን በመክፈል ከፊል ፍትነታዊ ንድፍ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በክፍል ውስጥ በነበረው የመጻፍ ችሎታ ትምህርት ልምምድ የፍትነት ቡድኑ በትብብራዊ ዘዴና የቁጥጥር ቡድኑ በተለመደው ዘዴ ከተማሩ በኋላ በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መጠናዊ መረጃዎችን በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታቲክስ በመተንተን ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

አላማውን ለመፈተሽ የቀረቡ የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች፡-

1. የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታን ለማጎልበት ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው?

2. የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ለማሳደግ ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው?

የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች የ2015 ዓ.ም. በቤንች ሸኮ ዞን በቢፍቱ ሚሊኒየም ከተማ አስተዳደር የቢፍቱ ሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት የፍትነት ቡድኑ በትብብራዊ ዘዴና የቁጥጥር ቡድኑ በተለመደው ዘዴ የደረጃውን መርሃ ትምህርት መሰረት ያደረገ የክፍለ ጊዜ አከፋፈል ተክትሎ የመደበኛውን ሁለት ክፍለ ጊዜና በተጨማሪ በአሰልጣኝ መምህሩና በጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች መስማማት አንድ ተጨማሪ ክፍለ ጊዜ በተቃራኒ ፈረቃ ተመቻችቶ አጠቃላይ መርሃ ግብሩ ለአራት ሳምንታትና አንድ ተጨማሪ ቀን ወይም አስራ ሶስት ክፍለ ጊዜ የሸፈነ ትምህርት ተሰጥቷቸዋል፡፡

በጥናቱም በመጻፍ ችሎታ ፈተናና በመጻፍ ተነሳሽነት መፈተሻ በጽሁፍ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ፈተናው በቅድመና በድህረ ትምህርት የተሰጠ ሲሆን የቅድመ ትምህርት ፈተናው አላማ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ያላቸው የቀደመ የመጻፍ

ችሎታቸውን ለመመዘንና የድህረ ትምህርት ፈተና አላማ ተሳታፊ ተማሪዎች ላይ በልምምድ ወቅት የታየውን ለውጥ ለመፈተሽ ነው፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ ደግሞ የተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነታቸው ምን ያህል እንደሆነ ለመፈተሽ የተተገበረ ነው፡፡ የፈተናውን ተገቢነትና አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ለተሳታፊ ተማሪዎች ከመቅረቡ በፊት በዋናው ጥናት ተተኳሪ ባልሆኑ 30 በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሙከራ (pilot test) ተደርጎ በክሮንባክ አልፋ አስተማማኝነት መገመቻ ሲፈተሽ የመጻፍ ችሎታ የፈተና ውጤት .950 በመሆኑ አስተማማኝ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪ የቅድመና ድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቁ የጥናቱ ተተኳሪ ያልሆኑ 30 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲሞሉ በማድረግ ሙከራ ተደርጎ በክሮንባንክ አስተማማኝነት መገመቻ ተረጋግጧል፡፡ ውጤቱም .823 በመሆኑ የጽሁፍ መጠይቅ አስተማማኝ እንደሆነ አመልክቷል፡፡

ከመጻፍ ችሎታ ፈተናና ከመጻፍ ተነሳሽነት መፈተሻ ከጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መጠናዊ መረጃዎች በቅድመና ድህረ ትምህርት ወቅት በቡድኖቹ መካከል ያለው ልዩነት ጉልህ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትነዋል፡፡ ከዚያም የመጀመሪያው ጥያቄ የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታን ለማጎልበት ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው? የሚለው ሲሆን ይህን ለማረጋገጥ በቅድመ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት በባዕድ ናሙና ቲ ቴስት ተፈትሾ የፒ ዋጋ= .003 ሆኗል፡፡ ውጤቱም በቅድመ ትምህርት በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት ያለ መሆኑን በማሳየቱ በድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት በንጥል ልይይት ተተንትኖ የፒ ዋጋ =.001 ሆኗል፡፡ ይህም ውጤት በፍትነትና በቁጥጥር ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት ያለ መሆኑን አረጋግጧል፡፡

በጥናቱ ሁለተኛው ጥያቄ የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው? የሚለው ሲሆን ይህን ለማረጋገጥ በቅድመ ትምህርት የመጻፍ ተነሳሽነት መፈተሻ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው ውጤት በባዕድ ናሙና ቲ ቴስት ተፈትሾ የፒ ዋጋ= .004 ሆኗል፡፡ ይህም በቅድመ ትምህርት በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት ያለ መሆኑን በማሳየቱ በድህረ ትምህርት ከመጻፍ ተነሳሽነት መፈተሻ ጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው ውጤት በንጥል ልይይት ተተንትኖ የፒ ዋጋ =.001 ሆኗል፡፡ ይህም ውጤት በፍትነትና በቁጥጥር ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት ያለ መሆኑን አሳይቷል፡፡

ከሁለቱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ከተገኙ የመጠናዊ መረጃዎች ትንተና ውጤት መረጋገጥ እንደተቻለው የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት ለማጎልበት ፋይዳ አለው፤ ወደሚል ድምዳሜ አድርሷል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

በትምርት ቤቶች ተማሪዎች ሃሳባቸው በጽሁፍ አሳክተው መግለጽ እንደሚቸገሩ በአነሳሽ ችግር ማብራሪያ ስር ተመልክተናል፡፡ በመጻፍ ችሎታ እጦች ችግርነት የሚነሱ ነጥቦች በርካታ ቢሆኑም የክፍል ውስጥ የመማር ሂደት በተለመደው አካሄድ መተግበሩ አንዱ ነው፡፡ ችግሩን ለመፍታት የማስተማር ዘዴው በተማሪዎች ፍላጎትና በእርስ በርስ በመተጋገዝ ላይ ሊመሰረት ይገባል፡፡ ትብብራዊ ዘዴም በስነ ትምህርት ውጤታማነት፣ ማህበራዊ ተራክቦን በመፍጠር፣ አእምሯአዊ እድገትን በማምጣትና በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተነሳሽነትን በመፍጠር የተሻለ ማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤትም ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በአማርኛ የመጻፍ ችሎታንና የመጻፍ ተነሳሽነታቸውን ከማጎልበት አኳያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ተረጋግጧል፡፡

በዚህም ውጤት መሰረት በሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

1. የመጻፍ ሂደት የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ አእምሯዊ ደረጃዎችን (ሂደቶችን) እንዲጠቀሙ ይጠይቃል፡፡ እነዚህም ትውስታን መጠቀም፣ ግብን መንደፍ፣ ማቀድን፣ ችግር መፍታትንና ግምገማ ናቸው፡፡ ስለሆነም በመጻፍ ችሎታ ትምህርት በክፍል ውስጥ የሚኖረው የመማር ማስተማር ሂደት የመጻፍ ችሎታ ትምህርት አቀራረቦችን አዋህዶ በመጠቀም የትብብራዊ ዘዴን መርሆችን፣ የትግበራ ብልሃቶችና የትምህርት ይዘቱን ማቅረቢያ ዘዴዎችን በተገቢው መንገድ በመጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ዘዴው (ትምህርታዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ ግብ ለማሳካት) በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከሚኖረው ቡድናዊ ተራክቦ የሚገኘውን የመጻፍን ችሎታ እውቀት ለማህበራዊ እና ትምህርታዊ ልምድ የማስገኘት ፋይዳው ከፍተኛ ነው ፡፡

2. የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት በማሳደግ በኩልም ያለው ፋይዳ አዎንታዊ ነው፡፡ ተማሪዎች የመማር ሂደታቸውን በኃላፊነትና በተጠያቂነት መንፈስ የሚመሩት ሆኖ በመካከላቸው በአቻና በቡድን ተግባራት አፈጻጸም በአዎንታዊ መደጋገፍ ላይ የተመሰረተ ውይይት፣ ክርክር፣ መተማመን፣ የተረዱትን መግለጽ፣ ወዘተ ያከናውናሉ፡፡ ይህም ሂደት በተማሪዎች ላይ ጠንካራ ተነሳሽነትንና ቡድናዊ ትብብር የሚፈጥር ስለሆነ

አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነው፡፡

በአጠቃላይ ትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት በማጎልበት፣ በመጻፍ ሂደት ጭንቀትንና ፍርሃትን በማስወገድ በነጻነት ሃሳብ በማመንጨትና በማደራጀት፣ የሰዋስውን እውቀትና የአጻጻፍ ስርዓትን ለማሻሻል ያለው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ታይቷል፡፡ ስለዚህ ትብብራዊ ዘዴን በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ተግባራዊ በማድረግ የሚፈለገውን ውጤት ለማስመዝገብ ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ እንደሆነ ሊሰተዋል ይገባል፡፡

## 5.3 አስተያየት

ትብብራዊ ዘዴ ሂደታዊ ትምህርት (መማር) ላይ በማተኮር በተማሪዎች መካከል ማህበራዊ ግንኙነትን ለማጎልበት፣ በሁሉም የክፍል ደረጃዎችና የትምህርት አይነቶች የሚተገበር ከተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች አንዱ እንደሆነ በተደጋጋሚ አንስተናል፡፡ ይህን ዘዴ በመጠቀም ክሂለ ብዙ የሆነውን፣ እንደረዥም ሂደት የሚታየውንና የማይቻል የሚመስለውን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ተማሪዎችን በትብብር ቡድኖች በማደራጀት ከርዕስ መረጣ ጀምሮ አብረው እንዲተገብሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የጥናቱ ውጤት ይህን አረጋግጧል፡፡

በጥናቱም ላይ ከተደረሰው ውጤት ማጠቃለያና ድምዳሜ በመነሳት የሚከተሉት ሙያዊ አስተያየቶች ተሰጥተዋል፡፡

ሀ. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመጻፍ ችሎታ ትምህርት በሚያሰተምሩበት ጊዜ የክፍል ውስጥ የልምምድ ተግባራትን የትብብራዊ ዘዴ መርሆችን፣ የትግበራ ብልሃቶችንና የአቀራረብ ዘዴዎችን በመጠቀም ቢተገብሩ ይመረጣል፡፡

ለ. የትምህርት ቤት ባለድርሻ አካላት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በትብብራዊ ዘዴ የትግበራ ሂደት ላይ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የስልጠና መርሃ ግብር በማዘጋጀት ስልጠና ቢሰጣቸው በጥናቱ የተገለጸውን ውጤት ማስቀጠል ይቻላል፡፡

ሐ. የዚህን ጥናት ውጤት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የስርአተ ትምህርት፣ የመርሃ ትምህርት፣ የመማሪያና ማስተማሪያ መጽሀፍት አዘጋጆች ለትብብራዊ ዘዴ የትግበራ ሂደቶች ትኩረት ሰጥተው የትምህርት ይዘቶችንና የልምምድ መልመጃዎችን ቢያዘጋጁ በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ችሎታና በሌሎችም የቋንቋ ክሂሎች ላይ ያጠላውን ችግር በመፍታት የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ይቻላል የሚል እምነት አሳድሯል፡፡

መ. የትብብራዊ ዘዴ የትግበራ ብልሃቶች፣ የመጻፍ ችሎታ ንዑሳን ችሎታዎችና የተነሳሽነት ገጽታዎች በተናጥል በጥልቀት በዚህ ጥናት አልተፈተሹም፡፡ ጥናቱ በበጀት አቅም ተደግፎና ተጨማሪ ጊዜ ተወስዶ የትግበራ ብልሃቶችን፣ የመጻፍ ችሎታ ንዑሳን ችሎታዎችንና የተነሳሽነት ገጽታዎችን በተናጥልና በጥልቀት ተመልክቶ ቢሆን በመጣው ውጤት ላይ ተጨማሪ አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

ሠ. በዚህ ጥናት ትኩረት የተደረገው በቢፍቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ውስጥ ካሉ ሁለት ምድቦች ላይ ነው፡፡ በዘርፉ ጥናት ማድረግ የሚፈልጉ ባለሙያዎች በቀሪ ምድቦችና በሌሎች የክፍል ደረጃዎች በመጻፍ ችሎታና የመጻፍ ተነሳሽነት እና በሌሎችም የቋንቋ ክሂሎች ላይ አትኩረው ጥናት ቢያደርጉ ከዚህም የተሻለ ውጤት ማምጣት ይቻላል፡፡

# ዋቢ ጽሁፎች


ማረው አለሙ (1987 ዓ.ም.)፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል በሁለተኛ አመት ተማሪዎች በግልና በቡድን በሚጻፉ በሳል ድርሰቶች ንጽጽራዊ ግምገማ (ያልታተመ ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፡፡

ሩት አበራ (2007 ዓ.ም.)፡፡ በገጸ ባህሪያት ተኮር አሀድ ማስተማር የመጻፍ ክሂልን በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና (ያልታተመ የድህረ ምረቃ ጥናት)፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ባህርዳር፡፡

ሰይድ ይመር (1993 ዓ.ም.)፡፡ በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ በቀረቡት የጽህፈት ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች፣ የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ፣ የመማር ማስተማር ሂደት (ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፡፡

ባየ ይማም (2009 ዓ.ም.)፡፡የአማርኛ ሰዋስው (ሶስተኛ እትም)፡፡አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

አማረ ተሾመ (2010 ዓ.ም.)፡፡ ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል እና ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለው ተጽዕኖ፤በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት ( ያልታተመ የፍልስፍና ዶክተሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት)፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣አዲስ አበባ፡፡

ተስፋዬ ሽዋዬ (1981 ዓ.ም.)፡፡ ስነልሳን እና ቋንቋን ማስተማር፡፡(ያልታተመ)፡፡

ተካልኝ ለማ (2009 ዓ.ም)፡፡ሂደተ ዘውጋዊ ዘዴ በተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ችሎታ እና አመለካከት ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ፣ በምዕራብ ሸዋ አካባቢ በኤጀሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት(ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፡፡

ያለው እንዳወቀ (2009 ዓ.ም.)፡፡ የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር (ሶስተኛ እትም)፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ተፈራ ስዩም ማተሚያ ቤት፡፡

ጌታቸው እንዳላማው (2011ዓ.ም.)፡፡ ቋንቋና ስነልሳን፡፡ አዲስአበባ፡፡ (ማተሚያ ቤት ያልተጠቀሰ)፡፡

Ahangari, S, and Samadian, Z. (2014). The Effect Of Cooperative Learning

`Activities On Writing Skills Of Iranian EFL Learners. Linguistics and Literature Studies 2(4): 121-130.

Albesher, K. B. (2012). Developing the writing skills of ESL students through the collaborative learning strategy (For Fullfilment of the degree of doctor of philosophy. Newcastle University.

Baltimore: P.H. Brookes Publishing Co.

Bandura, A. (1997). Self-efficacy: The exercise of control. New York, NY: Holt.

Bangert-Drowns, R. L., Hurley, M. M., & Wilkinson, B. (2004). The effects of School based writing-to-learn interventions on academic achievement: A meta- analysis. Review of Educational Research, 74(1), 29-58.

Brereton, J. C. (Ed.). (1995). The Origins of Composition Studies in the American College, 1875-1925.Pittsburgh: University of Pittsburgh Press.

Brown, H. D. (2004). Language Assessment: Principles and Classroom Practices. Pearson Education, Inc.

Brown, H. D. (2007). Principles Of Language Learning and Teaching(5th ed). San Francisco: Longman.

Clark, I. L. (2012). Process. In I. L. Clark, (Ed.). Concepts in Composition Theory and Practice in the Teaching of Writing (2, 8-28). New York; Routledge Tylore and Francies Group,

Erkan, D. Y., & Saban, A. I. (2011). Writing performance relative to writing apprehension, self-efficacy in writing, and attitudes towards writing: A correlational study in turkish tertiary-level EFL. Asian EFL Journal, 3(1),163-191.

Flower, L., and Hayes, J. R. (1981). A Cognitive Process Theory. College Composion and Communication, 32(4), 365-387.

Gillies, R. M. & Ashman, A. (2003) Co-operative learning: the social and intellectual outcomes of learning in groups, Routledge, London and New York.

Goldberg, K., Foster, K., Maki, B . , Emde, J., & O ’ Kelly, M. (2000).

Improving student motivation through cooperative learning and other Strategies (Dissertation, Saint Xavier University, 2001).

Hancock, D. (2004). cooperative learning and peer orientation effects on motivation and achievement.jornal of educational research, 97(3),159- 166.

Harmer, J. (1991).The practice of English Language Teaching. London Longman press.

Harmer, J. (2007). How to teach writing. print in Malaysia.

Hidi, S., & Boscolo, P. (2008). Motivation and Writing. In: C. A. MacArthur, S. Graham, & J. Fitzgerald (Eds.), Handbook of Writing Research (pp. 144-157). New York: Guilford Press.

Hyland, K. (2003). Second Language Writing. Cambridge: Cambridge University press.

Jacobs, G. M., Lee, C, & Ng, M. (1997). Co-Operative Learning In The Thinking Classroom. Paper Presented At The International Conference On Thinking, Singapore.

Johns, A. M. (1994). L1 Composition Theories: Implecations for Developing Theories of L2 Composion (Reprinted). In Kroll, B. (Ed.). Second Language Writing: Research insights for the classroom. Cambridge: Cambridge University press, 24-36.

Johnson, D. W. and Johnson, R. T. (2014). Cooperation and the use of technologyy. University of Minnesota Twin Cities. Minnesota.

Johnson, D. W. and Smith, K. A. (1998). Active Learning; Cooperation In The College Classroom. Interaction Campany Endim.MN.

Johnson, D. W., & Johnson, R. T. (1990). Social skills for successful group work. Leadership, 47, 29-33.

Johnson, D. W., & Johnson, R. T. (1999). Learning Together and Alone, (5th Ed.) Boston: Allyn & Bacon.

Kroll, B. (1990). Second Language Writing. Cambridge: Cambridge University press.

Kumaravadivelu, B. (2006). Understanding Language Teaching. From Method To Past Method London; San Jose University.

Lantolf, J. P. (2000) Socio cultural theory and second language learning, Language teaching.

Lepper, M. R. (1988). Motivational considerations in the study of instruction. Cognition and Instruction, 5(4), 289-309.

Li, M. P. & Lam, B. H. (2013). Cooperative Learning. The Active Class Room. The Hong Kong Institute of Education.

Mandal, R. R. (2009). Cooperative Learning Strategies to Enhance Writing Skills. Lady Willing Don Institute of Advance Study in Education, Chennai.

Manvender, M. S., Singh, K. S. (2016). Effecticeness of Cooperative Learning In Enhancing Students' Essay Writing Skills In Pakistani Colleges. A Review Of Literature. University Utara Malaysia.

Milawati, K. (2015). Using Cooperative Learning to Improve English Writing Skills Of Grade Viii Students Of Smp N 1. Jogonalan Klaten.

Moore, R. H. (1999).Effective Writing. New York: Rinchart & Company, Inc.

Niemiec, C. And Richard M. R. (2009). Autonomy, Competence, And Relatedness In The Classroom Applying Self-Determination Theory To Educational Practice. University Of Rochester, New York, USA.

Nunan, D. (1999). Second Language Teaching & Learning. Massachusetts:Heinle & Heinle Publishers. Of Georgia.

Onozawa, C. (2010) A Study Of The Process Writing Approach. Research Note, 153-161.

Pajares, F. (1996). Self-Efficacy Beliefs in Academic Settings.Review of Educational Research. Emory University.

Share On Student Participation In An Inclusive Classroom Follow. Student Research Submissions, 184. University Of Mary Washington.

Raimes, A. (1985) What unskilled ESL students do as they write: A classroom study of Composing, TESOL Quarterly, 19 (2), 229-258.

Richards, J. C. (1990). The Language Teaching Matrix. Cambridge: Cambridge University Press.

Robert, S. J. (1992). The Essential Elements of Cooperative Learning in the Classroom. Educational Resources Information Center. Used with Permission.

Sarget, D. (2004). Using Cooperative Writing Activities On Build Community Fiuency, And Accuracy. Available On; Http://Www.Schoolofesl.Com Publicayions/Cooperative Writing Project Pdf.

Shran, Y. (2010). Cooperative Learning for Academic and Social Gains: valued pedagogy, problematic practice. European Journal of Education, 45, 2.

Spratt, M., Pulverness, A., & Melanie, W. (2005).The Teaching Knowledge Test Course. Cambridge: Cambridge University Press.

Tran1 V. D. (2013). Theoretical Perspectives Underlying the Application of Cooperative Learning in Classrooms. International Journal of Higher Education. Faculty of Education, AnGiang University, Vietnam, An Giang, Vietnam.

Troyka, L. Q. (2010). Simon & Schuster Handbook for Writers, (5th Ed.).Toronto: College, 1875-1925.Pittsburgh Pearson Prentice Hall.

Usó-Juan, E. Martínez-Flor A. and Palmer-Silveira, J. C. (2006). Towards acquiring communicative competence through writing.in Esther Uso´-Juan Alicia Martı´nez-Flor Mouton de (ed.) Current Trends in the Development and Teaching of the Four Language Skills.

# አባሪዎች

## አባሪ 1. በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ

በጅማ ዩኒቨርሲቲ

የማህበራዊ ሳይንስና ሥነ-ሰብ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐግብር ውድ ተማሪዎች፦ የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና ተነሳሽነታቸውን ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ ለመፈተሽ መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡የጽሁፍ መጠይቁ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት፡፡የመጀመሪያው ክፍል የናንተን ዳራዊ መረጃ የሚጠይቅ ሲሆን፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ አማራጭ ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ለዚህ መረጃ አሰባሰብ እንዲያመች ሃያ አምስት ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል፡፡የቀረቡ ጥያቄዎችን ካነበባችሁ በኋላ ከተሰጡ አማራጮች አንዱን መርጣችሁ በስሩ የ "X " ምልክት በማስቀመጥ መልስ እንድትሰጡ ሲጠይቅ ስለመልካም ትብብራችሁ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ማሳሰቢያ፡-

- በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አስፈላጊ አይደለም።
- በክፍል አንድ ስለራሳችሁ የተጠየቃችሁን መረጃ በማንበብ እንድትሞሉና
- በክፍል ሁለት የቀረቡትን መጠይቆች በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ የመረጣችሁትን

ምላሽ በያዘው ቁጥር ስር የ "X" ምልክት በማስቀመጥ ምላሻችሁን ስጡ፡፡

ክፍል አንድ፡- የተማሪዎች ዳራ የሚመለከት መረጃ

መመሪያ ፡- ቀጥለው በቀረቡ ክፍት ቦታዎች ትክክለኛ መረጃዎች በመሙላት ምላሽ ስጡ፡፡

የክፍል ደረጃ______ዕድሜ__________ፆታ________ ክፍል ሁለት፡- የትብብራዊ ዘዴ ተነሳሽነትን ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ የተመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

መመሪያ፡- ቀጥለው የቀረቡ ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ከተሰጡ አማራጮች አንዱን መርጣችሁ በስሩ የ "X " ምልክት በማስቀመጥ መልስ ስጡ፡፡የአማራጮች ዕሳቤም በቁጥር ሲወከሉ የሚከተለውን አንደምታ ይይዛሉ፡፡

5= በጣም እስማማለሁ 4= እስማማለሁ 3=ለመወሰን እቸገራለሁ 2=አልስማማም 1=በጭራሽ አልስማማም

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | አማራጮች | | |
|---|---|---|---|---|
| 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | በትብብራዊ ዘዴ የመጻፍን ችሎታ መማር ያስደስተኛል፡፡ | | | |
| 2. | በትብብራዊ ዘዴ መማር በክፍል ውስጥ ራስን ብቸኛ ማድረግ ያሰቀራ ል፡፡ | | | |
| 3. | በክፍል ውስጥ በቡድንና በጥንድ መማር ውጤታማ ያደርገኛል፡፡ | | | |
| 4. | በትብብራዊ ዘዴ የመጻፍን ችሎታ መማር ሃሳብን በቀላሉ ማመጨንትያስችለኛል፡፡ | | | |
| 5. | በትብብራዊ ዘዴ የመጻፍን ችሎታ መማር ንቁ ተሳታፊ ያደርገኛል፡ | | | |
| 6. | በትብብራዊ ዘዴ መማር ተግባራትን በሃላፊነትና በተጠያቂነት ለማከናወንይረዳኛል፡፡ | | | |
| 7. | በትብብራዊ ዘዴ የመጻፍን ችሎታ መማር ከሌሎች ጋር ሃሳብ በመለዋወጥየተሰጠን ስራ በነጻነት መስራት ያስችለኛል፡፡ | | | |
| 8. | በትብብራዊ ዘዴ መማር በክፍል ውስጥ መደጋገፍ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ | | | |
| 9. | ትብብራዊ ዘዴ በመማር ሂደት የሚገጥሙኝን ችግሮች በቀላሉ መፍታትያስችለኛል፡፡ | | | |
| 10. | ትብብራዊ ዘዴ በመጻፍ ችሎታ ትምህርት ሂደት የሚፈጸሙ የአጻጻፍስህተቶችን በቡድን በመሆን ለማረም ይጠቅመኛል፡፡ | | | |
| 11. | በመጻፍ ችሎታ ትምህርት ሂደት በክፍል ውስጥ ከመምህር ምጋቤ ምላሽሲሰጠኝ ደስ ይለኛል፡፡ | | | |
| 12. | በትብብራዊ ዘዴ የመጻፍን ችሎታ መማር በቀላሉ የጽሁፌን አላማመወሰን ያስችለኛል፡፡ | | | |
| 13. | በትብብር ዘዴ በቡድን መማር ጊዜ ማጥፋት ነው፡፡ | | | |
| 14. | ብዙውን ጊዜዬን በክፍል ውስጥ የማሳልፈው በቡድንና በጥንድ ተግባራትነው፡፡ | | | |
| 15. | በትብብራዊ ዘዴ በቡድን መማር የመጻፍ ችሎታ እንዳዳብር ያግዘኛል፡፡ | | | |
| 16. | ትብብራዊ ዘዴ ከአቻ ተማሪዎች ጋር በመነጋገርና ምጋቤ ምላሽ እየተሰጣጡመማር ያስችለኛል፡፡ | | | |
| 17. | በትብብራዊ ዘዴ ከክፍል ጓደኞቼ ጋር የማደርገው ተራክቦ የማሰብችሎታዬን የበለጠ ያሳድግልኛል፡፡ | | | |
| 18. | ትብብራዊ ዘዴ ውስብስብ የሆነውን የመጻፍ ችሎታ ትምህርት ተግባራትንበቡድን በመተግበር በቀላሉ ውጤታማ እንዲሆን ያስችለኛል፡፡ | | | |
| 19. | እያንዳንዱን የክፍል ውስጥ የመማር ተግባራትን በግል ሳከናውን ደስይለኛል፡፡ | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 20. | ትብብራዊ ዘዴ ሌሎችን የማገዝ ባህል እንዳዳብር ያደርገኛል፡፡ | | | |
| 21. | ትብብራዊ ዘዴ ማሰብን፣በቡድን መስራትና ለሌሎች እውቀትን ማካፈል ያስችለኛል፡፡ | | | |

| Q 1 | Q 2 | Q 3 | Q 4 | Q 5 | Q 6 | Q 7 | Q 8 | Q 9 | Q 10 | Q 11 | Q 12 | Q 13 | Q 14 | Q 15 | Q 16 | Q 17 | Q 18 | Q 19 | Q 20 | Q 21 | Q 22 | Q 23 | Q 24 | Q 25 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 22. | በትብብር መማር የተለያዩ ልምዶችንና ትብብራዊ ክሂል ማዳበር ያስችለኛል፡፡ | | | |
| 23. | በክፍል ውስጥ የሚኖረው የመማር ማስተማር ሂደት በትብብራዊነት ላይየተመሰረተ ሲሆን ደስ ይለኛል፡ | | | |
| 24. | የጻፍኩትን ጽሁፍ ከክፍል ጓደኞቼ ጋር መከለስና አቻዊ ምጋቤ ምላሽመለዋወጥ በመጻፍ ችሎታን እንዳሻሽልና ውጤታማ እንዲሆን ያስችለኛል፡፡ | | | |
| 25. | በትብብራዊ ዘዴ መማር በመጻፍ ችሎታ ትምህርት አዳዲስ ቃላትንማወቅና መጠቀም ያስችለኛል፡፡ | | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 01 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 1 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 3 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 |
| 02 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 1 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 1 | 4 |
| 03 | 5 | 3 | 4 | 4 | 5 | 3 | 5 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 1 | 5 | 5 | 4 | 1 | 4 | 3 | 4 | 3 | 5 | 5 |
| 04 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 1 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 1 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 |
| 05 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 | 5 | 4 | 4 | 1 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 2 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 |
| 06 | 1 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 | 5 | 4 | 4 | 1 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 1 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| 07 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 1 | 2 | 4 | 5 | 5 | 5 | 1 | 4 | 5 | 4 | 4 | 1 | 4 |
| 08 | 4 | 3 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 5 | 4 | 1 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 |
| 09 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| 10 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 2 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 2 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 |
| 11 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 1 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 12 | 5 | 5 | 3 | 2 | 3 | 3 | 5 | 5 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 5 | 3 | 2 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 3 | 2 | 4 | 5 |
| 13 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 1 | 2 | 4 | 4 | 5 | 5 | 2 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| 14 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 2 | 5 | 5 | 3 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 |
| 15 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| 16 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 2 | 2 | 4 | 1 | 5 | 4 | 3 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 |
| 17 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| 18 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 2 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| 19 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 3 | 1 | 2 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| 20 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 3 | 3 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 |
| 21 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 3 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 |
| 22 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| 23 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 3 |
| 24 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 2 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 |
| 25 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 |
| 26 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 5 |
| 27 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 2 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 3 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 28 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 1 | 5 | 5 | 3 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 |
| 29 | 5 | 4 | 4 | 2 | 5 | 3 | 5 | 4 | 4 | 3 | 5 | 3 | 1 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 |
| 30 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 2 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 31 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 2 | 5 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 3 | 4 | 4 | 4 |
| 32 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 3 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 |
| 33 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 34 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 2 | 4 | 2 | 5 | 4 | 4 | 5 | 1 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 3 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 |
| 35 | 5 | 5 | 5 | 3 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 3 | 4 | 4 | 1 | 5 | 4 | 3 | 5 | 5 | 3 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 |
| 36 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 1 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 2 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 |
| 37 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 1 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 38 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 1 | 5 | 4 | 5 | 5 | 2 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 39 | 5 | 3 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 40 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 3 | 1 | 3 | 5 | 4 | 5 | 4 | 1 | 4 | 5 | 4 | 5 | 3 | 5 |
| 41 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 1 | 2 | 5 | 4 | 5 | 5 | 1 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 42 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 43 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 44 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 3 | 5 | 4 | 3 | 4 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |

## አባሪ 5. ለቁጥጥር ቡድን ከቅድመ ትምህርት ፈተና ጋር የተሰራጨ ጽሁፍ መጠይቅ ውጤት

| ተ. | ለጥያቄ |
|---|---|

| ቁ. | ዎቹ የተሰጠ ውጤት | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Q 1 | Q 2 | Q 3 | Q | Q 5 | Q 6 | Q 7 | Q 8 | Q 9 | Q 10 | Q 11 | Q 12 | Q 13 | Q 14 | Q 15 | Q 16 | Q 17 | Q 18 | Q 19 | Q 20 | Q 21 | Q 22 | Q 23 | Q 24 | Q 25 | |
| 01 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 1 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 3 | 4 | 4 |
| 02 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 1 | 5 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 |
| 03 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 1 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 3 |
| 04 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 1 | 2 | 5 | 5 | 4 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 05 | 5 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 1 | 4 | 5 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 |
| 06 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 1 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 |
| 07 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 2 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 3 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 08 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 5 | 1 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 3 | 5 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 |
| 09 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 3 | 2 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 |
| 10 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 3 | 5 | 4 | 4 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 2 | 5 | 4 | 4 | 5 |
| 11 | 5 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 5 | 5 | 2 | 5 | 3 | 5 | 3 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 3 | 5 | 4 | 1 | 5 | 1 | 5 |
| 12 | 5 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 3 | 4 | 4 | 3 | 1 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 1 | 4 | 1 |
| 13 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 | 5 | 5 | 4 | 1 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 |
| 14 | 5 | 3 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 3 | 5 | 5 | 5 | 1 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 |
| 15 | 5 | 1 | 5 | 4 | 4 | 1 | 5 | 5 | 4 | 5 | 3 | 2 | 3 | 3 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 |
| 16 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 17 | 4 | 4 | 5 | 3 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 1 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 |
| 18 | 5 | 2 | 4 | 2 | 4 | 5 | 4 | 5 | 3 | 1 | 5 | 4 | 1 | 3 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 3 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 |
| 19 | 5 | 3 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 1 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 20 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 1 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 2 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 |
| 21 | 5 | 3 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 1 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 1 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 |
| 22 | 5 | 1 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 3 | 1 | 1 | 5 | 4 | 1 | 4 | 2 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 |
| 23 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 24 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 3 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 |
| 25 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 1 | 1 | 4 | 5 | 4 | 4 | 1 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 |
| 26 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 3 | 4 | 5 | 5 | 4 | 2 | 2 | 4 | 5 | 5 | 1 | 4 | 1 | 4 | 5 | 5 | 1 | 5 |
| 27 | 4 | 3 | 4 | 5 | 5 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 5 | 1 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 3 | 3 | 5 | 3 | 1 |
| 28 | 4 | 3 | 5 | 2 | 1 | 4 | 5 | 4 | 3 | 4 | 3 | 2 | 5 | 4 | 4 | 2 | 3 | 4 | 2 | 3 | 1 | 2 | 4 | 3 | 5 |
| 29 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 3 | 4 | 1 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 |
| 30 | 5 | 3 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 1 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 |
| 31 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 5 | 3 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 32 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 1 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 |
| 33 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 34 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 1 | 2 | 4 | 5 | 4 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 |
| 35 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 2 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 |
| 36 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 1 | 3 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 |
| 37 | 4 | 5 | 5 | 3 | 2 | 1 | 1 | 2 | 3 | 4 | 4 | 4 | 1 | 3 | 4 | 2 | 4 | 3 | 2 | 4 | 5 | 5 | 4 | 2 | 5 |
| 38 | 5 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 1 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 |
| 39 | 5 | 3 | 4 | 5 | 1 | 2 | 4 | 5 | 3 | 1 | 2 | 5 | 3 | 4 | 2 | 3 | 5 | 3 | 4 | 1 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 |
| 40 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 2 | 1 | 4 | 4 | 5 | 1 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 |
| 41 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 2 | 1 | 2 | 5 | 4 | 1 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 |
| 42 | 5 | 3 | 4 | 5 | 4 | 5 | 1 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 3 | 5 | 3 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 43 | 5 | 2 | 4 | 1 | 5 | 2 | 1 | 2 | 4 | 4 | 4 | 2 | 1 | 4 | 5 | 4 | 2 | 2 | 4 | 5 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 |
| 44 | 5 | 4 | 1 | 4 | 5 | 2 | 4 | 2 | 5 | 2 | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 3 | 4 | 3 | 5 | 2 | 5 | 2 | 4 | 2 | 4 |

## አባሪ 5ሀ. የቅድመ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ የስርጭነት ወጥነት

## አባሪ 6. ለፍትነት ቡድን ከድህረ ትምህርት ፈተና ጋር የተሰራጨ ጽሁፍ መጠይቅ ወጤት

| ተ.ቁ. | ለጥያቄዎቹ |
|---|---|

| | የተሰጠ ውጤት | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Q 1 | Q 2 | Q 3 | Q 4 | Q 5 | Q 6 | Q 7 | Q 8 | Q 9 | Q 10 | Q 11 | Q 12 | Q 13 | Q 14 | Q 15 | Q 16 | Q 17 | Q 18 | Q 19 | Q 20 | Q 21 | Q 22 | Q 23 | Q 24 | | |
| 01 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | | |
| 02 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 1 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | | |
| 03 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 3 | 2 | 4 | 1 | 5 | 5 | 4 | 1 | 4 | 4 | 4 | 4 | | |
| 04 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 1 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 1 | 5 | 5 | 4 | 5 | | |
| 05 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 1 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 1 | 4 | 5 | 5 | 5 | | |
| 06 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 1 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 1 | 4 | 5 | 4 | 4 | | |
| 07 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 1 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 1 | 4 | 5 | 4 | 4 | | |
| 08 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 1 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | | |
| 09 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 2 | 4 | 5 | 5 | 4 | | |
| 10 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 2 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 2 | 4 | 5 | 4 | 5 | | |
| 11 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 1 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | | |
| 12 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | | |
| 13 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 1 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 2 | 5 | 5 | 4 | 5 | | |
| 14 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 1 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | | |
| 15 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 2 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 2 | 4 | 4 | 5 | 5 | | |
| 16 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | | |
| 17 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 2 | 5 | 4 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | | |
| 18 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 2 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | | |
| 19 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 2 | 5 | 5 | 5 | 5 | 3 | 1 | 4 | 5 | 4 | 5 | | |
| 20 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 2 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 3 | 5 | 4 | 4 | 5 | | |
| 21 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 1 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | | |
| 22 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 |
| 23 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 2 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 1 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 |
| 24 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 2 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 1 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 |
| 25 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 26 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 2 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 |
| 27 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 2 | 2 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 1 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 28 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 |
| 29 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 3 | 1 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 |
| 30 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 2 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 31 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 2 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 |
| 32 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 3 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 33 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 |
| 34 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 1 | 5 | 5 | 4 | 3 | 4 | 2 | 3 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 |
| 35 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 1 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 3 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 |
| 36 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 1 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 2 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 |
| 37 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 1 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 38 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 1 | 5 | 4 | 5 | 5 | 2 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 39 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 40 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 3 | 1 | 3 | 5 | 5 | 5 | 4 | 1 | 4 | 5 | 4 | 5 | 3 | 5 |
| 41 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 1 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 1 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 42 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 43 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 44 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 2 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |

አባሪ 7. ለቁጥጥር ቡድን ከድህረ ትምህርት ፈተና ጋር የተሰራጨ ጽሁፍ መጠይቅ ውጤት

| ተ.ቁ. | ለጥያቄዎቹ የተሰጠ ውጤት | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Q 1 | Q 2 | Q 3 | Q 4 | Q 5 | Q 6 | Q 7 | Q 8 | Q 9 | Q 10 | Q 11 | Q 12 | Q 13 | Q 14 | Q 15 | Q 16 | Q 17 | Q 18 | Q 19 | Q 20 | Q 21 | Q 22 | Q 23 | Q 24 | Q 25 | |
| 01 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 1 | 3 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | | 4 |
| 02 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 1 | 5 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 |
| 03 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 1 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 |
| 04 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 1 | 2 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 |
| 05 | 5 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 1 | 4 | 5 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 |
| 06 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 1 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 |
| 07 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 2 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 3 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | |
| 08 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 5 | 1 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 3 | 5 | 4 | 4 | 3 | 3 | |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 09 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 3 | 2 | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 |
| 10 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 3 | 5 | 4 | 4 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 2 | 5 | 4 | 4 |
| 11 | 5 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 5 | 5 | 2 | 5 | 3 | 5 | 3 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 3 | 5 | 4 | 1 | 5 | 1 |
| 12 | 5 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 3 | 4 | 4 | 3 | 1 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 1 | 4 |
| 13 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 | 5 | 5 | 4 | 1 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 |
| 14 | 5 | 3 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 3 | 5 | 5 | 5 | 1 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 |
| 15 | 5 | 1 | 5 | 4 | 4 | 1 | 5 | 5 | 4 | 5 | 3 | 2 | 3 | 3 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 16 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 17 | 4 | 4 | 5 | 3 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 1 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 |
| 18 | 5 | 2 | 4 | 2 | 4 | 5 | 4 | 5 | 3 | 1 | 5 | 4 | 1 | 3 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 3 | 5 | 1 | 5 | 5 | 5 |
| 19 | 5 | 3 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 1 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 20 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 1 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 2 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 |
| 21 | 5 | 3 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 1 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 1 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 |
| 22 | 5 | 1 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 3 | 1 | 1 | 5 | 4 | 1 | 4 | 2 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 |
| 23 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 24 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 3 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 |
| 25 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 1 | 1 | 4 | 5 | 4 | 4 | 1 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 |
| 26 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 3 | 4 | 5 | 5 | 4 | 2 | 2 | 4 | 5 | 5 | 1 | 4 | 1 | 4 | 5 | 5 | 1 | 5 |
| 27 | 4 | 3 | 4 | 5 | 5 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 5 | 1 | 1 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 3 | 3 | 5 | 3 | 1 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 28 | 4 | 3 | 5 | 2 | 1 | 4 | 5 | 4 | 3 | 4 | 3 | 2 | 5 | 4 | 4 | 2 | 3 | 4 | 2 | 3 | 1 | 2 | 4 | 3 | 5 |
| 29 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 3 | 4 | 1 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 |
| 30 | 5 | 3 | 5 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 1 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 |
| 31 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 5 | 3 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 |
| 32 | 5 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 1 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 5 |
| 33 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 2 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 |
| 34 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 2 | 5 | 5 | 5 | 3 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 |
| 35 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 2 | 2 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 1 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 5 |
| 36 | 4 | 4 | 5 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 5 |
| 37 | 4 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 1 | 2 | 3 | 3 | 4 | 4 | 1 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 2 | 4 | 5 | 4 | 4 | 3 | 4 |
| 38 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 2 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 |
| 39 | 3 | 3 | 4 | 5 | 1 | 3 | 4 | 5 | 3 | 1 | 4 | 5 | 3 | 4 | 3 | 3 | 5 | 3 | 4 | 1 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 |
| 40 | 4 | 3 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 2 | 1 | 4 | 4 | 5 | 1 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 |
| 41 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 3 | 5 | 2 | 1 | 3 | 5 | 4 | 1 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 4 |
| 42 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 5 | 1 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 3 | 4 | 5 | 4 | 5 |
| 43 | 5 | 3 | 4 | 1 | 5 | 2 | 1 | 2 | 4 | 5 | 4 | 2 | 1 | 3 | 5 | 4 | 4 | 2 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | 3 | 5 |
| 44 | 4 | 4 | 1 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 2 | 4 | 1 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 5 | 2 | 4 | 2 | 4 |

**አባሪ 7ሀ. የድህረ ትምህርት የጽሁፍ መጠይቅ የስርጭነት ወጥነት**

**አባሪ 8.የናሙና ሙከራ ጥናት የመጻፍ ችሎታ ፈተና**

*የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና ተነሳሽነታቸውን ለማጎልበት ያለው ፋይዳ በሚል ርዕስ ለሚሰራው ምርምር በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ የጽሁፍ ችሎታ ትምህርት ፈተና* (10%) ፡፡

*ስም* ________________ *ክፍል* ____________*ተራ ቁጥር*___________

*ለፈተናው የተፈቀደው ጊዜ፡* 2፡00 *አጠቃላይ መመሪያ፤*

*ውድ ተማሪዎች፣ ይህ የቅድመ ትምህርት ፈተና የእናንተን የመጻፍ ችሎታ የቀደመ እውቀታችሁን ለመፈተሽ የቀረበ ነው፡፡ ጥያቄዎች አራት ክፍሎች አሉት፡፡በሁሉም ክፍሎች ለቀረቡ ጥያቄዎች እንደየአጠያየቃቸው መልስ ስጡ፡፡*

*መመሪያ አንድ፡ - ቀጥሎ የቀረበው አንቀጽ ያለ ምንም ስርአተ ነጥብ የተጻፈ ነው፡፡ይህ አንቀጽ የተሟላ እንዲሆን ተገቢ ስርአተ ነጥቦችን በትክክለኛ ቦታቸው በመጠቀም አንቀጹን ጻፍ / ፊ፡፡*

*ስነ ጽሁፍ በአገላለጽ ትባቱ በህይወት ማሳያነቱ በሳቢነቱና የአንድ ደራሲ ወጥ ስራ በመሆኑ የተዋጣለትና ኪነ ጥበባዊ ብቃቱ የተመሰከረለት የፈጠራ ስራ ነው ሰዎች ለህይወት ያላቸውን ግንዛቤ ወይም የሚሰማቸውን የሚያስቡትንና የሚመኙትን በቋንቋ አማካይነት የሚያንፀባርቁበት ኪነጥበብ ነው እንዲሁም ህይወትን እውነትንና ፈጠራን ባንድ ላይ አጣምሮ በተወሰነ ቅርጽና መጠን የሚያቀርብ በመሆኑ ውበት አለው ስሜት ይነካል ይማርካል ያስደስታል ስለሆነም አንድ ምሁር በስነጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር ጠቀሜታ አለው ብለዋል*

*መመሪያ ሁለት ፡ - ቀጥሎ የቀረበውን መነሻ ሀሳብ መሰረት በማድረግና የአንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴዎችን በመጠቀም አንድ ተማሪ ከእንቅልፉ ተነስቶ ትምህርት ቤት ደርሶ የመማር ሂደቱን ጨርሶ ቤት እስኪመለስ ያለው ተከታታይ ድርጊት በጊዜ ቅደም ተከተል በማስቀመጥ አንድ አንቀጽ ጻፍ / ፊ ፡፡ በዚህ ጽሁፍ የሃሳብ አደረጃጀት፣ሰርዐተ ነጥብ ፣ሰዋስውና የአጻጻፍ ስርዓት ትኩረት ይደረግባቸዋል፡፡*

1፡00 ከእንቅልፌ ተነሳሁ

1፡30 ትምህርት ቤት ገቢ ደረስኩ 1፡45 ከባንዲራ ሰልፍ በኋላ ክፍል ገባሁ 4፡00 እረፍት ወጣሁ

6፡15 ከክፍል ወጥቼ ምሳ ተመለስኩ

መመሪያ ሶስት፡- ከዚህ በታች ቅደም ተከተላቸው የተዘበራረቀና ያለ ስርአተ ነጥብ የተጻፉ አረፍተ ነገሮች ቀርበዋል፡፡እነዚህ አረፍተ ነገሮች ቅደም ተከተላቸው ቢስተካከልና በተገቢ ስርአተ ነጥቦች ተሟልተው ቢጻፉ በምክንያትና ውጤት የተሳሰረ አንድ አንቀጽ ይወጣዋል፡፡ስለዚህ አስተካክላችሁ ጻፉና ርዕስ ስጡት፡፡

ሀ.በዚህ የተነሳ በቂ የዝናብ መጠን ላይገኝ ወይም ከሚፈለገው በላይ የዝናብ መጠን ተገኝቶ በሰዎች በእንሳስትና በሰብሎች ላይ ትልቅ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል

ለ.የኤሌክትሪክ ኃይል ባልደረሰባቸው አካባቢዎች ህዝቡ ደንን እየጨፈጨፈ ለማገዶነት ያውላል ሐ.የኃይል አጥረት ለደኖች መመናመን ዋነኛ መንስኤ እየሆነ መጥቷል መ.ስለሆነም እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ማለትም መንግስት የዘርፉ ባለሞያዎች ማህበረሰቡና ሌሎችም ትኩረት ሰጥተው ሊሰሩ ይገባል ሠ.የደኖች በጭፍጨፋ መመናመን ደግሞ የአየር ንብረት መዛባትን ያስከትላል

መመሪያ አራት፡-ቀጥሎ በተሰጠው ርእስ አንድ አንቀጽ ጻፍ/ፊ፡፡በዚህ የአንቀጽ ጽሁፍ የሃሳብ አደረጃጀት፣ ሰርዐተ ነጥብ ፣ሰዋስውና የአጻጻፍ ስርዓት ትኩረት ይደረግባቸዋል፡፡ በተጨማሪ የድርሰት ክፍሎች መግቢያ፣ሐተታና ማጠቃለያም ይተኮርባቸዋል፡፡

ርዕስ፡- የላም ጥቅም

አባሪ 9.የድርሰት እርማት መስፈርት (ለናሙና ሙከራ ጥናት) 01.ለሃሳብ አደረጃጀት የሚሰጠው ውጤት ከ1-4 (2.8%)

1. በእያንዳንዱ አንቀጽም ሆነ በዋናው ጽሁፍ ላይ ምንም አይነት የሀሳብ አደረጃጀት የማይታይበት

2. በእያንዳንዱ አንቀጽም ሆነ በዋናው ጽሁፍ ላይ በጣም ጥቂት የሆነ የሀሳብ አደረጃጀት የሚታይበት፣ርቱእነት የማይታይበትና ሀሳቦች የተምታቱበት ወይም ያልተጣጣሙበት ከሆነ

3. በወጉ ያልተደራጀና እንደነገሩ የቀረበ ሆኖ፣ ነገር ግን ዋናው ሀሳብ ተለይቶ የሚታወቅበት

4. የጽሁፉ አጠቃላይ ቅርጽም ሆነ የአንቀጾች ውስጣዊ አደረጃጀት ግልጽ የሆነና በደንብ የተደራጀ፣ ርቱእ የሆነ አገላለጽ የሚታይበት፣ ሀሳቦች በግልጽ የቀረቡበት

02. ለሰዋስው የሚሰጠው ውጤት ከ1-4(2.7%)

1. በእያንዳንዱ አረፍተነገር ላይ ሰዋስዋዊ ኢ-ርቱእነት ካለበት

2. በጣም ተደጋጋሚ የሆነ ሰዋስዋዊ ኢርቱእነት ካለበት፣ ለምሳሌ ከአስር በላይ የሆኑ ሰዋስዋዊ

ስህተቶች ካሉበት

3. በጣም አነስተኛ የሆነ ሰዋስዋዊ ኢ.ርቱእነት ካለበት፣ ለምሳሌ በጽሁፉ ውስጥ ከአስር በታች የሆኑ

ሰዋስዋዊ ስህተቶች ካሉበት

4. በተዋጣለት የአረፍተነገር ርቱእነት ከቀረበ

03. የአጻጻፍ ስርዓት (2.5%)

3.1. ለስርአተ ነጥብ የሚሰጠው ውጤት ከ1-3

1. በጣም ደካማ የሆነ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም የሚታይበት ከሆነ

2. ጉልህ የሆነ የስርአተነጥብ አጠቃቀም ችግር የማይታይበት ከሆነ

3. የስርአተነጥብ አጠቃቀም ብቃቱ ከፍተኛ ከሆነ

3.2. ለፊደላት አቀራረጽ የተሰጠው ውጤት ከ1-3 1.የፊደላት አጠቃቀም የጎላ ችግር የሚታይበት ከሆነ 2.የፊደላት አጠቃቀም የጎላ ችግር የማይታይት ከሆነ 3.ለጽሁፉ ብቁ የቃላት አጠቃቀም ያለው ከሆነ

04. ለቃላት ምርጫ የተሰጠው ውጤት ከ1-3 (2%)

1.የጽሁፍ መልዕክት የማስተላለፍ አቅም ደካማ ከሆነ 2.የጽሁፉን መልዕክት በተወሰነ መልኩ መግለጽ ከቻለ 3. የጽሁፉን መልዕከት በሚገባ ማስተላለፍ ከቻለ

(ሩት አበራ፣ 2007 ዓ.ም.፤ሃይላይ ተስፋዬ፣2011 ዓ.ም. ለደረጃው በሚመጥን መልኩ ተሻሽሎ የተወሰደ)

አባሪ 10.የናሙና ሙከራ ጥናት የመጻፍ ችሎታ ትምህርት ፈተና ውጤት (10 %)

| የተማሪው ኮድ | አራሚ መምህር 01 | አራሚ መምህር 02 | አራሚ መምህር 03 | አማካይ ውጤት |
|---|---|---|---|---|
| 01 | 1 | 2.5 | 2 | 1.83 |
| 02 | 3 | 4 | 3 | 3.33 |
| 03 | 4 | 4 | 4 | 4 |
| 04 | 4 | 5 | 3 | 4 |
| 05 | 4.5 | 4 | 5 | 4.5 |
| 06 | 6 | 7 | 6 | 6.33 |
| 07 | 5 | 5 | 4 | 4.67 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 08 | 7.5 | 7 | 6 | 6.83 |
| 09 | 7 | 7 | 8 | 7.33 |
| 10 | 6 | 5 | 5 | 5.33 |
| 11 | 7 | 6 | 6 | 6.33 |
| 12 | 5 | 5 | 4 | 4.67 |
| 13 | 7 | 5 | 5.5 | 5.83 |
| 14 | 4 | 6 | 4 | 5.33 |
| 15 | 8 | 7 | 7 | 7.33 |
| 16 | 4 | 5 | 5 | 4.66 |
| 17 | 5 | 3 | 5 | 4.33 |
| 18 | 7 | 6 | 7 | 6.67 |
| 19 | 9 | 7.5 | 8 | 8.16 |
| 20 | 6 | 7 | 5 | 6 |
| 21 | 5 | 6 | 6 | 5.67 |
| 22 | 7 | 5 | 5 | 5.67 |
| 23 | 6 | 5 | 5 | 5.33 |
| 24 | 5 | 5 | 5 | 5 |
| 25 | 8 | 8 | 7 | 7.67 |
| 26 | 7 | 5 | 6 | 6 |
| 27 | 9 | 9 | 9 | 9 |
| 28 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 29 | 3 | 5 | 3 | 3.67 |
| 30 | 9 | 9 | 8 | 8.67 |

አባሪ 11.ቅድመ ትምህርት ፈተና

የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና ተነሳሽነታቸውን ለማጎልበት ያለው ፋይዳ በሚል ርዕስ ለሚሰራው ምርምር በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ የጽሁፍ ችሎታ ትምህርት ፈተና (100%) ፡፡

ስም _______________ ክፍል ___________ተራ ቁጥር__________ ለፈተናው የተፈቀደው ጊዜ፡ 3፡00

አጠቃላይ መመሪያ፤

ውድ ተማሪዎች፣ ይህ የቅድመ ትምህርት ፈተና የእናንተን የመጻፍ ችሎታ የቀደመ እውቀታችሁን ለመፈተሽ የቀረበ ነው፡፡ ጥያቄዎች አራት ክፍሎች አሉት፡፡በሁሉም ክፍሎች ለቀረቡ ጥያቄዎች እንደየአጠያየቃቸው መልስ ስጡ፡፡

መመሪያ አንድ፡ - ቀጥሎ የቀረበው አንቀጽ ያለ ምንም ስርአተ ነጥብ የተጻፈ ነው፡፡ይህ አንቀጽ የተሟላ እንዲሆን ተገቢ ስርአተ ነጥቦችን በትክክለኛ ቦታቸው በመጠቀም አንቀጹን ጻፍ / ፊ፡፡

ስነ ጽሁፍ በአገላለጽ ትባቱ በህይወት ማሳያነቱ በሳቢነቱና የአንድ ደራሲ ወጥ ስራ በመሆኑ የተዋጣለትና ኪነ ጥበባዊ ብቃቱ የተመሰከረለት የፈጠራ ስራ ነው ሰዎች ለህይወት ያላቸውን ግንዛቤ ወይም የሚሰማቸውን የሚያስቡትንና የሚመኙትን በቋንቋ አማካይነት የሚያንፀባርቁበት ኪነጥበብ ነው እንዲሁም ህይወትን እውነትንና ፈጠራን ባንድ ላይ አጣምሮ በተወሰነ ቅርጽና መጠን የሚያቀርብ በመሆኑ ውበት አለው ስሜት ይነካል ይማርካል ያስደስታል ስለሆነም አንድ ምሁር በስነጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር ጠቀሜታ አለው ብለዋል

መመሪያ ሁለት ፡ - ቀጥሎ የቀረበውን መነሻ ሀሳብ መሰረት በማድረግና የአንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴዎችን በመጠቀም አንድ ተማሪ ከእንቅልፉ ተነስቶ ትምህርት ቤት ደርሶ የመማር ሂደቱን ጨርሶ ቤት እስኪመለስ ያለው ተከታታይ ድርጊት በጊዜ ቅደም ተከተል በማስቀመጥ አንድ አንቀጽ ጻፍ / ፊ ፡፡ በዚህ ጽሁፍ የሃሳብ አደረጃጀት፣ሰርዐተ ነጥብ ፣ሰዋስውና የአጻጻፍ ስርዓት ትኩረት ይደረግባቸዋል፡፡

1፡00 ከእንቅልፌ ተነሳሁ

1፡30 ትምህርት ቤት ግቢ ደረስኩ 1፡45 ከባንዲራ ሰልፍ በኋላ ክፍል ገባሁ 4፡00 እረፍት ወጣሁ

6፡15 ከክፍል ወጥቼ ምሳ ተመለስኩ

መመሪያ ሶስት፡- ከዚህ በታች ቅደም ተከተላቸው የተዘበራረቀና ያለ ስርአተ ነጥብ የተጻፉ አረፍተ ነገሮች ቀርበዋል፡፡እነዚህ አረፍተ ነገሮች ቅደም ተከተላቸው ቢስተካከልና በተገቢ

ስርአተ ነጥቦች ተሟልተው ቢጻፉ በምክንያትና ውጤት የተሳሰረ አንድ አንቀጽ ይወጣዋል፡፡ስለዚህ አስተካክላችሁ ጻፉና ርዕስ ስጡት፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

ሀ.በዚህ የተነሳ በቂ የዝናብ መጠን ላይገኝ ወይም ከሚፈለገው በላይ የዝናብ መጠን ተገኝቶ በሰዎች በእንሳስትና በሰብሎች ላይ ትልቅ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል ለ.የኤሌክትሪክ ኃይል ባልደረሰባቸው አካባቢዎች ህዝቡ ደንን እየጨፈጨፈ ለማገዶነት ያውላል ሐ.የኃይል አጥረት ለደኖች መመናመን ዋነኛ መንስኤ እየሆነ መጥቷል መ.ስለሆነም እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ማለትም መንግስት የዘርፉ ባለሞያዎች
ማህበረሰቡና ሌሎችም ትኩረት ሰጥተው ሊሰሩ ይገባል ሠ.የደኖች በጭፍጨፋ መመናመን ደግሞ የአየር ንብረት መዛባትን ያስከትላል

መመሪያ አራት፡-ቀጥሎ በተሰጠው ርእስ አንድ አንቀጽ ጻፍ/ፊ፡፡በዚህ የአንቀጽ ጽሁፍ የሃሳብ አደረጃጀት፣ ሰርዐተ ነጥብ ፣ሰዋስውና የአጻጻፍ ስርዓት ትኩረት ይደረግባቸዋል፡፡ በተጨማሪ የድርሰት ክፍሎች መግቢያ፣ሐተታና ማጠቃለያም ይተኮርባቸዋል፡፡

ርዕስ፡- የላም ጥቅም

አባሪ 12.የድርሰት እርማት መስፈርት (ለዋናው ጥናት) 01.ለሃሳብ አደረጃጀት የሚሰጠው ውጤት ከ1-4 (28%)

1. በእያንዳንዱ አንቀጽም ሆነ በዋናው ጽሁፍ ላይ ምንም አይነት የሀሳብ አደረጃጀት የማይታይበት

2. በእያንዳንዱ አንቀጽም ሆነ በዋናው ጽሁፍ ላይ በጣም ጥቂት የሆነ የሀሳብ አደረጃጀት የሚታይበት፣ርቱእነት የማይታይበትና ሀሳቦች የተምታቱበት ወይም ያልተጣጣሙበት ከሆነ

3. በወጉ ያልተደራጀና እንደነገሩ የቀረበ ሆኖ፣ ነገር ግን ዋናው ሀሳብ ተለይቶ የሚታወቅበት

4. የጽሁፉ አጠቃላይ ቅርጽም ሆነ የአንቀጾች ውስጣዊ አደረጃጀት ግልጽ የሆነና በደንብ የተደራጀ፣ ርቱእ የሆነ አገላለጽ የሚታይበት፣ ሀሳቦች በግልጽ የቀረቡበት

02. ለሰዋስው የሚሰጠው ውጤት ከ1-4(27%)

1. በእያንዳንዱ አረፍተነገር ላይ ሰዋስዋዊ ኢ-ርቱእነት ካለበት

2. በጣም ተደጋጋሚ የሆነ ሰዋስዋዊ ኢርቱእነት ካለበት፣ ለምሳሌ ከአስር በላይ የሆኑ ሰዋስዋዊ

ስህተቶች ካሉበት

3. በጣም አነስተኛ የሆነ ሰዋስዋዊ ኢርቱእነት ካለበት፣ ለምሳሌ በጽሁፉ ውስጥ ከአስር በታች የሆኑ

ሰዋስዋዊ ስህተቶች ካሉበት

4. በተዋጣለት የአረፍተነገር ርቱእነት ከቀረበ

03. የአጻጻፍ ስርዓት (25%)

3.1. ለስርአተ ነጥብ የሚሰጠው ውጤት ከ1-3

1. በጣም ደካማ የሆነ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም የሚታይበት ከሆነ

2. ጉልህ የሆነ የስርአተነጥብ አጠቃቀም ችግር የማይታይበት ከሆነ

3. የስርአተነጥብ አጠቃቀም ብቃቱ ከፍተኛ ከሆነ

3.2. ለፊደላት አቀራረጽ የተሰጠው ውጤት ከ1-3 1.የፊደላት አጠቃቀም የጎላ ችግር የሚታይበት ከሆነ 2.የፊደላት አጠቃቀም የጎላ ችግር የማይታይት ከሆነ 3.ለጽሁፉ ብቁ የቃላት አጠቃቀም ያለው ከሆነ

04. ለቃላት ምርጫ የተሰጠው ውጤት ከ1-3 (20%)

1.የጽሁፍ መልዕክት የማስተላለፍ አቅም ደካማ ከሆነ

2.የጽሁፉን መልዕክት በተወሰነ መልኩ መግለጽ ከቻለ 3. የጽሁፉን መልዕክት በሚገባ ማስተላለፍ ከቻለ

(ሩት አበራ፣ 2007 ዓ.ም.፤ሃይላይ ተስፋዬ፣2011 ዓ.ም. ለደረጃው በሚመጥን መልኩ ተሻሽሎ የተወሰደ)

አባሪ 13. የፍትነትና የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት (100 %)

| የፍትነት ቡድን | የቁጥጥር ቡድኑ |
| --- | --- |

| ቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት | ቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የተማሪው ኮድ | አራሚ መምህር01 | አራሚ መምህር02 | አራሚ መምህር03 | አማካይ ውጤት | የተማሪው ኮድ | አራሚ መምህር01 | አራሚ መምህር02 | አራሚ መምህር03 | አማካይ ውጤት |
| 01 | 50 | 52 | 46 | 01 | 70 | 68 | 71 | | |
| 02 | 70 | 69 | 73 | 02 | 55 | 52 | 58 | | |
| 03 | 49 | 52 | 50 | 03 | 59 | 55 | 57 | | |
| 04 | 52 | 49 | 53 | 04 | 45 | 41 | 41 | | |
| 05 | 66 | 69 | 63 | 05 | 57 | 59 | 55 | | |
| 06 | 70 | 69 | 70 | 06 | 53 | 54 | 53 | | |
| 07 | 48 | 52 | 43 | 07 | 70 | 70 | 73 | | |
| 08 | 50 | 52 | 49 | 08 | 51 | 51 | 51 | | |
| 09 | 47 | 56 | 50 | 09 | 60 | 58 | 61 | | |
| 10 | 76 | 74 | 73 | 10 | 41 | 44 | 43 | | |
| 11 | 67 | 66 | 64 | 11 | 57 | 60 | 55 | | |
| 12 | 61 | 69 | 66 | 12 | 50 | 51 | 51 | | |
| 13 | 50 | 48 | 55 | 13 | 40 | 43 | 39 | | |
| 14 | 66 | 69 | 64 | 14 | 30 | 32 | 30 | | |
| 15 | 51 | 52 | 51 | 15 | 47 | 50 | 49 | | |
| 16 | 52 | 55 | 50 | 16 | 50 | 50 | 48 | | |
| 17 | 70 | 73 | 69 | 17 | 41 | 43 | 40 | | |
| 18 | 70 | 69 | 62 | 18 | 30 | 29 | 30 | | |
| 19 | 76 | 77 | 77 | 19 | 35 | 31 | 33 | | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 20 | 50 | 56 | 53 | 20 | 30 | 27 | 30 | | |
| 21 | 80 | 79 | 73 | 21 | 60 | 63 | 59 | | |
| 22 | 60 | 64 | 63 | 22 | 78 | 73 | 77 | | |
| 23 | 56 | 55 | 50 | 23 | 45 | 41 | 41 | | |
| 24 | 56 | 57 | 53 | 24 | 60 | 60 | 63 | | |
| 25 | 68 | 70 | 71 | 25 | 62 | 64 | 61 | | |
| 26 | 76 | 69 | 78 | 26 | 39 | 40 | 36 | | |
| 27 | 50 | 51 | 54 | 27 | 80 | 83 | 84 | | |
| 28 | 59 | 50 | 56 | 28 | 45 | 45 | 42 | | |
| 29 | 70 | 68 | 72 | 29 | 60 | 61 | 63 | | |
| 30 | 62 | 57 | 69 | 30 | 72 | 69 | 70 | | |
| 31 | 56 | 57 | 54 | 31 | 68 | 67 | 67 | | |
| 32 | 67 | 72 | 70 | 32 | 65 | 63 | 66 | | |
| 33 | 67 | 68 | 56 | 33 | 55 | 54 | 49 | | |
| 34 | 76 | 70 | 74 | 34 | 80 | 85 | 83 | | |
| 35 | 75 | 76 | 74 | 35 | 76 | 73 | 77 | | |
| 36 | 66 | 61 | 63 | 36 | 60 | 62 | 62 | | |
| 37 | 72 | 68 | 74 | 37 | 73 | 71 | 73 | | |
| 38 | 68 | 62 | 64 | 38 | 67 | 63 | 69 | | |
| 39 | 37 | 33 | 38.5 | 39 | 30 | 28 | 29 | | |
| 40 | 66 | 68 | 69 | 40 | 48 | 43 | 44 | | |
| 41 | 42 | 38 | 44 | 41 | 50 | 48 | 49.5 | | |
| 42 | 60 | 66 | 69 | 42 | 40 | 41 | 41 | | |
| 43 | 60 | 60 | 63 | 43 | 20 | 17 | 18 | | |
| 44 | 66 | 67 | 65 | 44 | 40 | 38 | 43 | | |

**አባሪ 13 ሀ. የቅድመ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና የስርጭነት ወጥነት**

**አባሪ 14.የድህረ ትምህርት ፈተና**

የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ችሎታና ተነሳሽነታቸውን ለማጎልበት ያለው ፋይዳ በሚል ርዕስ ለሚሰራው ምርምር በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ የጽሁፍ ችሎታ ትምህርት ፈተና (100%) ፡፡

ስም ________________ ክፍል ____________ተራ ቁጥር___________

ለፈተናው የተፈቀደው ጊዜ፡ 2፡30

አጠቃላይ መመሪያ፤

ውድ ተማሪዎች፣ ይህ ቅድመ ትምህርት ፈተና የእናንተን የመጻፍ ችሎታ የቀደመ እውቀታችሁን ለመፈተሽ የቀረበ ነው፡፡ ጥያቄዎች አራት ክፍሎች አሉት፡፡በሁሉም ክፍሎች ለቀረቡ ጥያቄዎች እንደአጠያየቃቸው መልስ ስጡ፡፡

መመሪያ አንድ፡ - ቀጥሎ የቀረበው አንቀጽ ያለ ምንም ስርአተ ነጥብ የተጻፈ ነው፡፡ይህ አንቀጽ የተሟላ እንዲሆን ተገቢ ስርአተ ነጥቦችን በትክክለኛ ቦታቸው በመጠቀም አንቀጹን ጻፍ / ፊ፡፡

ስነ ቃል የሚለው ስያሜ ሁለት እሳቤዎችን ይወክላል አንደኛው የልዩ ልዩ ኪነቃላዊ ቅርጾች ጥቅል መጠሪያነቱ ሲሆን ሁለተኛው ራሱን የቻለ የጥናትና የእውቀት ዘርፍ መሆኑ ነው ስነቃል ራሱን እንደቻለ የጥናት መስክ መጠሪያነቱ ሲታይ በጽሁፍ ያልሰፈሩ ነገር ግን በቃል የሚከወኑ የቋንቋ ጥበቦችን የሚያጠና የስነጽሁፍ ዘርፍ ነው እንደኪነቃላዊ ቅርጾች ጥቅል መጠሪያነቱ ደግሞ በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ ተረቶችን ሐተታ ተፈጥሮዎችን አፈ ታሪኮችን ምሳሌያዊ ንግግሮችን እንቆቅልሾችን ቃላዊ ግጥሞችንና ዝማሬዎችን ሁሉ ያጠቃልላል

መመሪያ ሁለት ፡ - ቀጥሎ የቀረበውን መነሻ ሀሳብ መሰረት በማድረግና የአንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴዎችን በመጠቀም የህይወት ታሪካችሁን የጊዜ ቅደም ተከተል ጠብቃችሁ አጭር ድርሰት ጻፍ / ፊ ፡፡ በዚህ ጽሁፍ የሃሳብ አደረጃጀት፣ሰርአተ ነጥብ ፣ሰዋስውና የአጻጻፍ ስርዓት ትኩረት ይደረግባቸዋል፡፡

ስም-------------

የትውልድ ዘመን----- የትውልድ ስፍራ ክልል----ዞን------ወረዳ--- ከአባቴ-------እና ከእናቴ---
----- ተወለድኩ፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቆይታና ትምህርት ቤቱ

በአንደኛ ደረጃ ቆይታዬ ለመጻፍ ትምህርት ያለ መሻት

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቆይታና ትምህርት ቤቱ

አሁን የ------ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡

በዚህ የክፍል ደረጃ ያለኝ ለመጻፍ ትምህርት ያለ መሻት

መመሪያ ሶስት፡-ቀጥሎ የቀረበው መነሻ መሰረት በማድረግና የአንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴዎችን በመጠቀም አንቀጽ ጻፍ/ፊ፡፡በዚህ ጽሁፍ የሃሳብ አደረጃጀት፣ሰርዐተ ነጥብ ፣ሰዋስውና የአጻጻፍ ስርዓት ትኩረት ይደረግባቸዋል፡፡

ምክንያት ውጤት

-የኃይል እጥረት -የደኖች መመናመን

-የደኖች መጨፍጨፍ -የአየር ንብረት በዛባት

-በቂ ዝናብ አለመኖር ወይም ከሚጠበቀው በላይ መጣል -የሰዎች የእንስሳትና የሰብሎች ጉዳት

መመሪያ አራት ፡ - ቀጥሎ በተሰጠው ርእስ አንቀጽ ጻፍ / ፊ ፡፡ በዚህ ጽሁፍ የሃሳብ አደረጃጀት፣ሰርዐተ ነጥብ ፣ሰዋስውና የአጻጻፍ ስርዓት ትኩረት ይደረግባቸዋል፡፡በተጨማሪ የድርሰት ክፍሎች መግቢያ፣ሐተታና ማጠቃለያም ይተኮርባቸዋል፡፡

ርዕስ፡- የበሬ ጥቅም

አባሪ 15.የፍትነትና የቁጥጥር ቡድኑ የድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት (100 %)

| የፍትነት ቡድን ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት | የቁጥጥር ቡድን ድህረ ትምህርት ፈተናውጤት | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የተማሪው ኮድ | አራሚ መምህር 01 | አራሚ መምህር02 | አራሚ መምህር03 | አማካይ ውጤት | የተማሪው ኮድ | አራሚ መምህር01 | አራሚ መምህር02 | አራሚ መምህር03 | አማካይ ውጤት |
| 01 | 60 | 62 | 56 | 01 | 77 | 70 | 81 | | |
| 02 | 80 | 79 | 83 | 02 | 50 | 57 | 63 | | |
| 03 | 51 | 55 | 50 | 03 | 54 | 60 | 59 | | |
| 04 | 57 | 51 | 53.5 | 04 | 47 | 53 | 51 | | |
| 05 | 86 | 79 | 83 | 05 | 58 | 59 | 53 | | |
| 06 | 88 | 77 | 84 | 06 | 63 | 59 | 66 | | |
| 07 | 49 | 54 | 51 | 07 | 79 | 70 | 77 | | |
| 08 | 59 | 54 | 57 | 08 | 58 | 50.5 | 60 | | |
| 09 | 53 | 56 | 59.5 | 09 | 60 | 67 | 63 | | |
| 10 | 91 | 94 | 87 | 10 | 47 | 39 | 43 | | |
| 11 | 79 | 74 | 83 | 11 | 70 | 66 | 59 | | |
| 12 | 70 | 76 | 73 | 12 | 61 | 53 | 51 | | |
| 13 | 55 | 50 | 58 | 13 | 59 | 63 | 53.5 | | |
| 14 | 86 | 89 | 84.5 | 14 | 41 | 34 | 37 | | |
| 15 | 53.5 | 57 | 51 | 15 | 46 | 48 | 51 | | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 16 | 50 | 58 | 51.5 | 16 | 52 | 50 | 48 | | |
| 17 | 90 | 93 | 89 | 17 | 51 | 41 | 47 | | |
| 18 | 90 | 89 | 92 | 18 | 40 | 32 | 37 | | |
| 19 | 91 | 90 | 93 | 19 | 25 | 39 | 32 | | |
| 20 | 50 | 56 | 53 | 20 | 36 | 32 | 41 | | |
| 21 | 90 | 89 | 93 | 21 | 69 | 62 | 60 | | |
| 22 | 71 | 73.5 | 76 | 22 | 80 | 74 | 79 | | |
| 23 | 58 | 55 | 53 | 23 | 52 | 40 | 43 | | |
| 24 | 61 | 68 | 63 | 24 | 61 | 60 | 64 | | |
| 25 | 69 | 72 | 74 | 25 | 60 | 61 | 64 | | |
| 26 | 86 | 90 | 88 | 26 | 32 | 41 | 37 | | |
| 27 | 59 | 57 | 64 | 27 | 90 | 82 | 86 | | |
| 28 | 59 | 54 | 61 | 28 | 51 | 57 | 46 | | |
| 29 | 89 | 80 | 88 | 29 | 68 | 60 | 64 | | |
| 30 | 61 | 64 | 70 | 30 | 75 | 69 | 71 | | |
| 31 | 59 | 63 | 54 | 31 | 66 | 69 | 63 | | |
| 32 | 69 | 76 | 71 | 32 | 70 | 73 | 69 | | |
| 33 | 63 | 69 | 66 | 33 | 54 | 60 | 51 | | |
| 34 | 86 | 80 | 91 | 34 | 86 | 81 | 86 | | |
| 35 | 85 | 86 | 84 | 35 | 73 | 79 | 81 | | |
| 36 | 76 | 71 | 73 | 36 | 69 | 63 | 72 | | |
| 37 | 82 | 89 | 84 | 37 | 70 | 76 | 73 | | |
| 38 | 81 | 74 | 74 | 38 | 70 | 60 | 68 | | |
| 39 | 41 | 43 | 48 | 39 | 38 | 33 | 39 | | |
| 40 | 76 | 78 | 70 | 40 | 45 | 48 | 51 | | |
| 41 | 51 | 49 | 53 | 41 | 55 | 51 | 54.5 | | |
| 42 | 80 | 76 | 79 | 42 | 43 | 47 | 51 | | |
| 43 | 90 | 89 | 86 | 43 | 34 | 37 | 45.5 | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 44 | 81 | 87 | 90 | 44 | 32 | 34 | 39 |

**አባሪ 15 ሀ. የድህረ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና የስርጭነት ወጥነት**

**አባሪ 16.የስልጠና ማኑዋልና የማስተማሪያ ወህዳህድ**

**መግቢያ**

ይህ ጥናት የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችንበአማርኛ የመጻፍ ችሎታና ተነሳሽነት የማጎልበት ፋይዳ የሚፈትሽ ነው፡፡የጥናቱም ንድፍ ከፊል ፍትነታዊ ስለሚሆን በትብብራዊ ዘዴ ለሚማረው ቡድን በክፍል ውስጥ የሚኖረው የአተገባበር ሂደት ለማመልከት የተዘጋጀ ነው፡፡

በዚህም ስልጠና በመጀመሪያው ክፍል ትኩረት የሚደረግባቸው የትብብራዊ ዘዴ ምንነት፣ ከተለመደው ዘዴ ጋር ያለውን ልዩነት፣መርሆች፣የአተገባበር ብልሃቶች፣ ጠቀሜታው፣ የመምህራንና የተማሪዎች ሚና እና የትግበራ ዘዴዎቹ ላይ ነው፡፡በሁለተኛው ክፍል የማስተማሪያ ውህዳህድና እቅድ ቀርቧል፡፡ከመምህሩ ስልጠና መውሰድ በኋላ ፍትነታዊ ቡድኑ በዚህ ማኑዋል ይመራል፡፡

የስልጠናው አላማ ሰልጣኙ መምህር ከዚህ ስልጠና በኋላ፡-

ϖ የትብብራዊ ዘዴን ምንነት፣ከተለመደው ዘዴ ጋር ያለውን ልዩነት፣የትብብራዊ ዘዴ መርሆች፣የአተገባበርብልሃቶች፣

ጠቀሜታው፣የመምህራንናየተማሪዎች ሚናና ጠቀሜታውን ይገልጻሉ፡፡ የስልጠናው ይዘቶች፡-

ϖ የትብብራዊ ዘዴን ምንነት መግለጽ

ϖ ከተለመደው ዘዴ ጋር ያለውን ልዩነት መግለጽ፣

ϖ የትብብራዊ ዘዴ መርሆች መግለጽ፣

ϖ የአተገባበር ብልሃቶች መግለጽ፣

ϖ የዘዴውን ጠቀሜታ መግለጽ፣

ϖ የመምህራንና የተማሪዎች ሚና መግለጽ፣

ϖ የመተግበሪያ ዘዴዎቹን መግለጽ፤ ናቸው፡፡

ክፍል አንድ የትብብራዊ ዘዴ ምንነት

ትብብራዊ ዘዴ በመምህሩ አመቻችነት አንድን የጋራ የመማር ግብና አላማ ለማሳካት ተማሪዎች በንኡሳን ቡድኖች በመሆን፣መማራቸውን በሃላፊነትና በተሳታፊነት የሚመሩበት እና ማህበራዊ ትስስር የሚንጸባረቅበት ከተግባቦታዊ ዘዴዎች አንዱ ነው ፡፡

ትብብራዊ ዘዴ አደረጃጀቱ ስብጥራዊነት ላይ የሚመሰረት በመሆኑ በተማሪዎች መካከል ባህሪያዊ፣ግንዛቤያዊ እና ማህበራዊ ትስስርን ይፈጥራል፡፡ ባህሪያዊ ትስስሩ በአንድ ቡድን አባላት መካከል መነጋገርን፣መተራረምን፣ድጋፍ መሰጣጣት፣የሃሳብ ልውውጥና የተሻለ የመረጃ ፍሰት በመካከላቸው ስለሚኖር ጠንካራ ግንኙነትንና ጤናማ አንድነትን መፍጠር ያስችላል፡፡

የልማዳዊ እና ትብብራዊ ማስተማር ዘዴ ልዩነት

| ተለምዷዊ ዘዴ | ትብብራዊ ዘዴ | |
|---|---|---|
| ነጻነት ከመስጠት አኳያ | አዎንታዊ ነጻነት ይሰጣል፡፡ | |
| አቀራረቡ | -መምህር ተኮር ነው -ተማሪዎች አስቀድመው የሚያውቁት ክሂል አለ ተብሎ ስሚታሰብ -ትብብራዊክሂሎት ላይ አያተኩርም፡፡ -እውቀትን ያስተላልፋል፡፡ -ግላዊ እና ውድድራዊ ነው፡፡ | -ተማሪ ተኮር ነው፡፡ -ትብብራዊ ክሂሎት እንዲያድግ ይጠበቃል፡፡ -አውቀትን ያሸጋግራል፡፡ -ትብብራዊነት ላይ ያተኩራል፡፡ |
| ከመደጋገፍ አኳያ | አዎንታዊ ተደጋጋፊነት አይታይበትም | አዎንተዊ ተደጋጋፊነት ይታይበታል |
| የሚከተለው የመማር ማስተማር ስልት | አንድ ወጥነት ያለውን ወይም ተመሳሳይ(homogeneity) ማስተማር ስልትን ይከተላል | የተማሪዎችን የተለያዩ ተላውጦችን መሰረት ያደረገ ውህድ(ስብጥራዊነት) ይታይበታል |
| የተማሪው ሚና | -የቡድን ስራን የሚያከነውኑ ቢኖሩም ጥቂት ናቸው፣ተማሪዎችም ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት ይማራሉ፡፡ -አድማጭና የታዘዙትን ፈጻሚ ናቸው፡፡ | -የቡድን አባል ተማሪዎች ሚናቸውን ለይተውየአመራር ሚናን ይቀያየራሉ፤ ይወጣሉ፤ -ንቁ ተሳታፊና መማራቸውን በበላይነት ይመራሉ፡፡ |

ለተማሪዎች ነጻነት አይሰጥም፤ ቢሰጥም አሉታዊነት ይታይበታል፡፡

| | |
|---|---|
| ግለሰባዊ ተጠያቂነት አይታይበትም | በየቡድናቸውበሚኖረው የተግባር አፈጻጸም |

| | | |
|---|---|---|
| | ግለሰባዊተጠያቂነት ይኖረዋል፡፡ | |
| ቡድን አባላት መካከል አንዳቸው ስለ አንዳቸው ሃላፊነት አይኖራቸውም | ተሳትፏቸውን በሚያሳድግ ሁኔታ ተግባራትንተከፋፍለው ይሰራሉ፤ የአባላቱም ሃላፊነት አለባቸው | |
| ከተማሪዎች የሚጠበቀው | -ከተማሪዎችየሚጠበቀው የተጠናቀቀ ስራ ነው፡፡ -የራስ ግለ መማር መገምገም ላይ ያተኮረ ነው፡፡-ግላዊ ስኬት ላይ የሚያተኩር ስለሆነ ውጤቱ ሊሳካ ላይሳካም ይችላል፡፡ | -በቡድን ስራው ግብና አላማ ‧ ስለሆነ ተማሪዎች ውጤታማ ‧ታል፡፡-ለቡድኑ ውጤታማነት ፊነትያከናውናሉ፡፡-እያደገና ፡፡ |
| ተራክቦ | በትብብራዊነት ላይ የተመሰረተ መልካም ግንኙነት የሌለው ነው፡፡ | ምቹ የሆነ የክፍል ውስጥ መማርና መልካምየስራ ግንኙነት ይፈጥራል፡፡ |
| የመምህር ሚና | በተማሪዎች የመማር ሂደት ላይ የሚደረገው ክትትል አናሳ ነው፡፡ የክፍሉ ማእከል፣ተቆጣጣሪ፣ውሳኔ ሰጪ፣ ብቸኛው አጋዥ ወዘተ፡፡ | -የቡድን ስራው አደራጅና አማካሪ ነው፡፡የመማር ማስተማሩ ሂደት አመቻች፣ተማሪዎችን ያነቃቃቸዋል፤ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣል፤ተገቢ የሆነ ክትትልያደርጋል፡፡ |

የትብብራዊ ዘዴ የመማር ማስተማር ሂደት የአተገባበር ብልሃቶች 1.የቡድን አመሰራረት ብልሃቶች

የቡድን ምስረታ በተማሪዎች መካከል አዎንታዊ ተደጋጋፊነት እንዲኖር የሚያደርግ ስለሆነ በቡድን ምስረታ ወቅት የሚከተሉትን ነገሮች ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

1.የመጀመሪያው የቡድን ስፋት መወሰን፡- የተማሪዎችን ዕድሜ፣ ለትምህርቱ የተሰጠው ሰዓትና የሚከናወኑ ተግባራትን ከግምት ውስጥ በማስገባት አንድ ቡድን ውስጥ ምን ያህል

ተማሪ መካተት እንዳለበት መወሰን ነው፡፡ የቡድን አደረጃጀቱን ከ 2-4 የሚደርሱ ተማሪዎችን በአንድ ቡድን መመደብ ተመራጭነት አለው፡፡

2.ተማሪዎችን በየቡድኑ መመደብ፡- ይህ ደግሞ በመምህሩ ወይም በተማሪዎች ምርጫ አለበለዚያ ደግሞ በእጣ ሊከናወን ይችላል፡፡ በመምህሩ ምርጫ የሚከናወነው ምደባ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ምክንያቱም የተማሪዎችን ያለፈ ጊዜ ስኬት፣ ፆታ፣ የመጡበትን አካባቢ ባህላዊና ማህበራዊ ዳራ እና የመሳሰሉትን ጉዳዩች በሚገባ ሊያውቅ ስለሚችል ነው፡፡

3.ለሁሉም የቡድን አባል ተማሪዎች የየራሳቸው የሆነ ድርሻን መስጠት፤ ለምሳሌ፡-

አስተዋዋቂ፡-ራሱ የቡድኑ ተሳታፊ በመሆን የቡድኑን ስራ በሃላፊነት ይመራል፡፡ለቡድን አባላት ተግባራትን

እንዲከፋፈሉ ያደርጋሉ፡፡

ጸሀፊ፡-በትብብራዊ ዘዴ የሚማሩ ቡድኖች በውይይት ሂደት የሚነሱ ሃሳቦችን በመመዝገብ የተጠቃለለውን የመጨረሻውን ሪፖርት ለአቅራቢው ያቀርባል፡፡

የሰዓት ተቆጣጣሪ፡-የቡድን አባላት መጠቀም ያለባቸውን ጊዜ ያሳውቃል፤ይቆጣጠራል፤ለቡድኑ የተሰጠው ጊዜና ተግባራት መጣጣማቸውን ያረጋግጣል፡፡ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ከመምህሩ ጋር በመነጋገር እንዲጨመር ያደርጋል፡፡

አቅራቢ፡- የቡድን አባላትን የውይይት ማጠቃለያ ለክፍሉ ያቀርባል ወይም ያንጸባርቃል፡፡

አረጋጋጭ፡-እያንዳንዱ የቡድን አባል የተጣለበትን ሃላፊነት መወጣት አለመወጣቱን በመከታተል ያረጋግጣል፡፡

አበረታች፡- እያንዳንዱ የቡድን አባል የተሰጠውን ተግባር በሚያከናውንበት ወቅት የበለጠ እንደተጋ የሚያበረታቱ ቃላትን በመጠቀም እንዲበረታቱ ያደርጋል፡፡

4.እያንዳንዱ ተማሪ ለስራው ተጠያቂ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስ ፡- ይህም በቡድን ስራው ወቅት እያንዳንዱ ተማሪ ካበረከተው አስተዋፆ በመነሳት ውጤት በመስጠት ወይም ደግሞ ከቡድን አባላት ውስጥ ዕድል ሰጭ በሆነ መንገድ በዘፈቀደ ሁኔታ አንዱን በማስነሳት ስራቸውን ለክፍሉ ተማሪ እንዲያንጸባርቁ በማድረግ እና በመሳሰሉት ዘዴዎች ሊከናወን ይችላል፡፡

5.የተማሪዎችን የቡድን ስራ መዋቅር ማስያዝ፡ -ይህም ተማሪዎች በቡድን ሆነው አንድን ተግባር በሚያከናወኑበት ወቅት የተለያዩ ዘዴዎችን እንዲጠቀሙበማድረግ ይከናወናል፡፡

6.ስብጥራዊነት ማቧደን (Hetrogeneous grouping):- ስብጥራዊ መርህ በአንድ ትብብራዊ የመማር ቡድን ውስጥ የሚዋቀሩ ተማሪዎች ቅይጥ ወይም ውህድነት የሚታይበት ነው፡፡ይህም የተማሪዎች የተለያዩ ተላውጦችን(ጾታን፣ብሄርን፣ ማህበራዊ መደብን፣ሃይማኖትን ስብእናን፣እድሜ፣ ቋንቋ፣ ችሎታና ትጋትን) የሚያትት ነው፡፡እንዲሁም የቡድን አባላትን የሃሳብ ተሳትፎ ጥምረትም ይጠይቃል፡፡አላማውም በተማሪዎች መከካል መተጋገዝን፣ ልምድ መለዋወጥን፣ እውቀት መጋራትን፣ ልዩነትን መቀበልንና ማድነቅን ያጎለብታል፡፡

2. የትግበራ ሂደቱ መርሆች

1.አዎንታዊ ተደጋጋፊነት፡ አዎንታዊ ተደጋጋፊነት በትብብራዊ የመማር ማስተማር ዘዴ ውስጥ እንደ ልብ (ማእከል) የሚቆጠር መርህ ነው፡፡ተማሪዎች አንድን የመማር ግብ ለማሳካት ሚናቸውን የለየና የአለክሳንደር ዱማስን "ሁሉ ለአንዱ፣አንዱ ለሁሉ" የሚለውን መርህ በመከተል በመደጋገፍ አንዱ ሌላውንና ራሱን ለማብቃት ድርሻውን መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ ምክንያቱም የእንዱ ተጠቃሚነት የቡድን አጋሩ ተጠቃሚነት እንዲሁም የአንዱ መጎዳት የቡድኑ መጎዳት ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ መርህ ተማሪዎች የሚያስቡትና የሚያቅዱት ከመማር የሚጠበቀውን ውጤት የጋራ ስኬት ማድረግ ነው፡፡በሂደቱም በሚኖረው ተራክቦ የተማሪዎች የመማር ተነሳሽነት ይጨምራል፤በጋራ ውጤት ላይም ትኩረት ይደረጋል፤የባህሪይና አመለካከት ለውጥ ይመዘገባል፡፡

2.ግለሰባዊ ተጠያቂነት :-ትብብራዊ ቡድንን ስንጠቀም የተቀናጀ ቡድንና ግለሰባዊ ተጠያቂነት ይሻል፡፡የትብብራዊ ቡድን አላማው እያንዳንዱ የትብብራዊ ቡድን አባል በራሱ ፈቃድ ጠንካራ ስብእና የሚገነባበት ነው፡፡ግለሰባዊ ተጠያቂነት እያንዳንዱ የቡድን አባል ጥንካሬ የሚፈተሽበትና የሚረጋገጥበት ቁልፍ ነው፡፡የመማሪያ ክፍሉም ገጽታ አንደኛ ተማሪዎች እውቀትን፣ክሂልን፣ብልሃትንና የትግበራ ቡድንኑን የትግበራ ቅደም ተከተል የሚማሩበት ሲሆን ሁለተኛው በትብብራዊ የመማር ሂደት ያገኙትን እውቀት ውይም ብቃታቸውን፣የመማር ብልሃታቸውንና ያገኙትን ግላዊ ችሎታ በተግባር የሚያሳዩበት ነው፡፡ በግለሰባዊ ተጠያቂነት መርህ ሁሉም የትብብራዊ ቡድኑ አባላት ሚናቸውን ለይተው ለጋራ ውጤትና የጋራ አላማ ለማሳካት አንዱ አድማጭ ሌላው ተናጋሪ ሊሆኑ አይገባም፡፡ ምክንያቱም የቡድን ስራው ተጠያቂም ተሸላሚም ሊያደርግ ይችላል፡፡

3.ትብብራዊነትን ማሳደግ :-በተማሪዎች መካከል ተራክቦ እያደገ ሲመጣ መተማመን በመገንባት፣ምክንያታዊነትን፣ የማስተባበር፣ውሳኔ የመስጠት እና ችግሮችን የመፍታት ክሂል

ያዳብራሉ፡፡ትብብራዊነት ሲያድግ የቡድን አባላት ስነ ትምህርታዊ እና ስብእናዊ አቅም በማሳደግ ችሎታቸውን በተግባር ማሳየት ይጀምራሉ፡፡ይህ መርህ በባህሪይው በቡድን አባላት መካከል በሚኖረው ተራክቦ ብቃትንና ውጤታማነትን ያሳድጋሉ፡፡ ከሚሰጡ ምጋቤ ምላሾች በመነሳት መከራከርን፣ በምክንያታዊነት መተማመንን፣ ማጠቃለያና ውሳኔ መስጠትን ማሻሻል ያስችላቸዋል፡፡

4. ቡድናዊ ሂደት ፡-ይህ መርህ ከተቀመጠው ቡድናዊ ግብ አኳያ እያንዳንዱ የቡድን አባል ሚናውን በመለየት፣ ሃላፊነቱን በማወቅ፣የሚጠበቅበትን ተግባር በማከናወን ውጤታማነቱ የሚፈተሸበት ነው፡፡ ከተገኘው ውጤት በመነሳት ከተሳካ ውጤቱ ቀጣይነቱን ለማስጠበቅ፣ካልተሳካ የማረም ስራ የሚሰራበት ነው፡፡አላማውም የጋራ ግብ በማሳወቅ፣ የተግባር ሂደቱን በግልጽ ለማብብራት፣ ውጤታማነቱን ለማሳደግና ግብ ማሳካት ነው፡፡

5.የፊትለፊት ተራክቦን ማሳደግ፡- የዚህ መርህ ቁልፍ ጉዳይ ግለሰቦች ለጋራ ስኬት መረዳዳትን፣መደጋገፍን፣መበረታታትንና መመሰጋገንን ለያሳድጉ ይገባል፡፡ምንም እንኳን አንዳንድ ቡድኖች ተናጠላዊነትንና የሌላው የመገልበጥ ችግር ቢታይባቸውም ሌሎች የጋራ አላማን ለማሳካት በትብብራዊ ተራክቦ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡በእነዚህ አእምሯዊ ሂደቶችና በውስጤ ቡድናዊ ተግባራት አፈጻጸም ከሌሎች ጋር የሚኖረውን ተራክረቦ በማሳደግ ችግሮችን እንዴት መፍታት እንደሚቻል፣በጽንሰ ሃሳቦች ላይ መወያየትንና መግለጽን፣እውቀትን መማማርንና ከቀደመ እውቀት ጋር በማስተሳሰር ክሂልን ማጎልበት ይቻላል፡፡ የፊት ለፊት ተራክቦ መርህ በቡድን አባላት መካከል የቡድን ተጠያቂነትን፣ምክንያታዊ ክርክርንና ማጠቃለያ መስጠትን፣ማህበራዊ አርአያነትንና የመደጋገፍ ችሎታን እንዲያሳድጉ በማድረግ በከል አዎንታዊ ተጽእኖ ያደርጋል ፡፡

6.የአንድ ጊዜ ተራክቦ ፡-በመማሪያ ክፍል ብዙ የማይመከረው ልማዳዊ የመማር ሂደት አንድ ጊዜ እንደ ተማሪ መናገርን ይፈቅዳል፤ክትትሎሻ ሂደቱም መምህር ተናጋሪ ተማሪ አድማጭ ወይም አንዱ መላሽ ሌላው አድማጭ የሚሆንበት ነው፡፡ ትብብራዊ ዘዴ ግን በአንድ ክፍል ሃያ ቡድን ቢኖረው የየቡድኑን ተናጋሪ ቁጥር ከፍ በማደረግ በአንድ ጊዜ የተናጋሪው ቁጥር እንዲጨምር ያደርጋል፡፡

7.እኩል ተሳትፎ ፡- በክፍል ውስጥ በቡድን ትግበራ ወቅጥ ከሚፈጠሩ ችግሮች በቡድን ውስጥ የአንድና ሁለት ተማሪ የበላይ ተጽእኖ ፈጣሪነት ወይም የሌሎች ተሳትፎ ማነስ ነው፡፡በትብብራዊ መማር ተማሪዎች ሚናቸውን ለይተው ስለሚጀምሩ እንዲሁም አስፈላጊ ሲሆን ሚናን በመቀያየር እንዲመሩ ስለሚያደርግ ተሳትፎአቸውን ከፍ ያደርጋል፡፡

በትብብራዊ ዘዴ የሚዋቀሩ ቡድን አይነቶች

ትብብራዊ ዘዴ ሁለገብ የሆነ የማሰተማሪያ ቅደም ተከተላዊ ሂደቶች ያሉት ሲሆን ለተለያየ አላማ ማለትም ለዝርዝር የትምህርት ይዘት ማስተማሪያ(መደበኛ የሆነ ትብብራዊ መማር ቡድን) ፣በእይታና በገለጻ መልክ ለሚቀርቡ የማስተማሪያ መሳሪያ መረጃዎችን ለማረጋገጥ( ኢ-መደበኛ የሆነ ትብብራዊ መማር ቡድን) እና ረጅም ጊዜ የሚወስድ ድጋፍና እገዛ የሚሹ አካዳሚያዊ ትምህርቶችን(ትብብራዊ መሰረት ያላቸው ቡድኖችን) እንጠቀማቸዋለን፡፡ቡድኖቹ የሚከተሉ ናቸው፡፡

1.መደበኛ ትብብራዊ የመማር ቡድን ፡-ይህ የቡድን አይነት ከአንድ ክፍለ ጊዜ ጀምሮ የተወሰኑ ሳምንታትን የሚዘልቅ እድሚያለው ዘዴ ነው፡፡ የሚደራጀውም ተማሪዎች አንድን ውስን አላማ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ በጋራ ማሳካት እንዲችሉ የሚፈጠር ቡድን ነው፡፡ በዚህ ቡድን የሚከናወኑ ተግባራት ችግሮችን መፍታት፣ ሪፖርት ወይም ዘገባ ማዘጋጀት፣ ቃላትን ማስተማር እና በየምእራፉ መጨረሻ ጥያቄዎችን ማሰራት ናቸው፡፡

የትኛውም መማር በትብብራዊነት እንዲቀናጅ ይጠበቃል፡፡ስለሆነም በመደበኛ ትብብራዊ የመማር ቡድን መምህሩ የሚከተሉ ተግባራትን ያከናውናል፡-

1.ከመማሪያ ክፍል አስቀድሞ የትምህርት ውሳኔዎችን ይወስናል፡፡ በትብብር ቡድኑ ለትምህርትነት የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች ሊኖራቸው የሚችለውን ዝርዝር አላማዎች (አካዳሚያ እና ማህበራዊ ክሂሎት ያካተተ)፣በክፍል ውስጥ የቡድን ብዛት፣ የተማሪዎች በቡድን የአመዳደብ ዘዴ፣ የተማሪዎችን ሚና፣ከትምህርት ይዘት ጋር ተያያዝ የሆኑ ማስተማሪያ መሳሪያዎች እና ክፍሉን እንዴት ማደራጀት እንዳለበት አስቀድሞ መወሰን አለበት፡፡ የመማር ሂደቱ ትብብራዊነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የትብብር መማር ክሂሎችን መወሰን ያስፈልጋል፡፡

2.ተግባራትን ማብራራት እና የአዎንታዊ ተደጋጋፊነት መርህን መግለጽ፡- መምህሩ በክፍል ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትንና የተግበራው ሂደት የሚጠይቀውን ጽንሰ ሃሳብንና ብልሃትን በግልጽ ማብራራት፣የአዎንታዊ ተደጋጋፊነትና ግለሰባዊ ተጠያቂነትን መርህ ማሳወቅ፣ የመመዘኛ መስፈርት መስጠት፣ትብብራዊ ክህል እንዲጠቀሙ ማስገንዘብ እና ከመማር በኋላ የሚጠበቀውን መግለጽ ፡፡

3. የተማሪዎችን የመማር ሂደት መቆጣጠርና ጣልቃ መግባት መርዳት፡- በተማሪዎች መካከል ጠንካራ ተራክቧዊ ግንኙነት እንዲኖር እና የቡድን ክሂል እንዲያድግ አስፈላጊ

ሲሆን በየቡድኑ ስራ ጣልቃ በመግባት ማገዝ፣ መርዳት፣ ማበረታታት እና ምጋቤ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

4.ተማሪዎችን መማር መመዘን እና የቡድኑን የተግባር ሂደቱ ምን ያህል ስከታማ እንደሆነ መገምገም፡- የተማሪዎች መማር በጥንቃቄ መመዘን እና ብቃታቸው መገምገም አለበት፡፡ከዚያም የትብብራዊ መማር ቡድን አባላት የተግባር አፈጻጸማችው ውጤታማነት ላይ እና ወደ ፊትም እንዴት ማሻሻል እንዳለባቸው ይወያያሉ፡፡

2. ኢ.መደበኛ ትብብራዊ የመማር ቡድን ፡-የዚህ ቡድን አደረጃጀት ከተወሰኑ ደቂቃዎች እስከ አንድ ክፍለ ጊዜ የሚቆይ

እድሜ ያለው ሲሆን ተማሪዎች አንድን የመማር ተግባር (አላማ) አሳክተው ሲጨርሱ የሚፈርስ ጊዜያዊ ቡድን ነው፡፡

የቡድን አላማም የትምህርት የማስተማሪያ መሳሪያዎችን (በገለጻ፣ለእይታ በፊልም) በሚቀርቡበት ጊዜ ለማስተዋወቅ፣ምቹ

የመማር አውድ ለመፍጠር፣የሚሸፈነውን የትምህርት ይዘት እንዲጠብቁ፣ ስሜታቸውን ለመማር ዝግጁ ለማድረግ እና

የትምህርት ይዘቱን ማጠቃለያ ለመስጠት ነው፡፡ስለዚህ መምህራን ትምህርቱ በሚቀርብበት ጊዜ ከገለጻው በፊትና በኋላ

ለተማሪዎች ለማሰቢያና ለመወያያ የሚሆን ከ3-5 ደቂቃዎችን ሊሰጡ ይገባል፡፡

3. ትብብራዊ መሰረት ያላቸው ቡድኖች፡- ትብብራዊ መሰረት ያላቸው ቡድኖች ስብጥራዊነት ላይ የተመሰረተ ቋሚ

የቡድን አባላት ያሉት ነው፡፡አደረጃጀቱም ከወራት ጀምሮ ለአንድ አመትና ከዚያ በላይ ጊዜ ሊቆይ የሚችል ሆኖ ከ3-4

አባላትን ያካትታል፡፡የዚህ ቡድን አላማ የቡድን አባል ተማሪዎች የመማር ግባቸው እንዲሳካ መደጋገፍ፣መረዳዳት፣መበረታታት የሚታይባቸው እና የመማር ሂደቱ (የክፍል ቁጥጥር፣ ተግባራትን መጨረስ፣መማር) ማህበራዊ እና ግንዛቤያዊ ክሂላቸውን እንዲያሳድጉ ነው፡፡

የትግበራ ብልሃቶች

በትብብራዊ መማር ማስተማር ሂደት በክፍል ውስጥ የሚተገበሩ ብልሃቶች ጽንሰ ሃሳባቸው ተማሪዎች በቡድን እንዲሰሩ የሚያበረታቱ፣ለራሳቸውና ለቡድን የመማር ሂደት ሃላፊነት እንዲሰማቸው የሚያደርግ ብልሃት ነው፡፡እንደሚከተለውም እንመለከታለን፡፡

ሀ.ማሰብ መጎዳኘት እና ማጋራት፡- ይህ ዘዴ ከትብብራዊ ቡድን የማሰተማሪያ ብልሃቶች አንዱ ነው፡፡አተገባበሩ ለተማሪዎች በመመህሩ በኩል ጥያቄዎች ይቀርቡና በዝምታ እንዲያስቡ ወይም እንዲያሰላስሉ ይደረጋል፤ያሰቡትን በአእምሮአቸው ውስጥ ለመጠበቅ ይጽፋሉ፤ያን ሃሳብ የበለጠ ለማብላላት በጥንድ ሆነው ከጓደኞቻቸው ጋርይወያያሉ፤በመጨረሻም የውይይቱን ማጠቃለያ ለጠቅላላ ክፍል ያቀርባሉ፡፡የዚህ ማስተማሪያ ዘዴ ጠቀሜታዎች የሚከተሉ ናቸው፡፡

ለተማሪዎች በቂ የማሰቢያጊዜ ስለሚኖራቸው የጠራ ምላሽ እንዲኖራቸው ያደርጋል፤ ከማሰቢያ ጊዜ በኋላ በጥንድ ስለሚወያዩ አመለካከታቸውን ሌሎች የማጋራት እድል ይሰጣቸዋል፤

በተማሪዎቹ መካከል( ራሳቸውን ማግለል ለሚፈልጉ) ተራክቧዊ ተግባቦት ከፍ እንዲል ያደርጋል፡፡

ለምሳሌ፡-

የትብብር ቡድኑ ይደራጃል፡፡አንድ ርዕስ ይሰጣል፡፡ ስለዚያ ርዕስ የቡድን አባላት አስቀድመው ብቻቸውን በዝምታ እንዲያስቡ ይደረጋል፡፡ በግል ያሰቡትን በወረቀት ላይ እንዲጽፉ ይደረጋሉ፡፡

በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የጻፉትን የግላቸውን ሃሳብ ለቡድን አባላት በማቅረብ እንዲወያዩ ይደረጋል፤የበለጠ

ያሰፉታል፡፡ከቡድን ውይይቱ በኋላ ቢጋር ያዘጋጃሉ፤ለክፍል ያቀርባሉ፤አስተያየት ይቀበላሉ፤የመጨረሻውን ጽሁፍ በግላቸው ይጽፋሉ፡፡የእርማቱ መስፈርት በአጻጻፍ ስርአት፣ ይዘት፣በሃሳብ አደረጃጀት፣በቃላት አጠቃቀምና ሰዋስው ላይ ያተኩራል፡፡

ለ. የተለያዩ ተግባራትን ለተለያዩ የቡድን አባላት መስጠት ፡-የተለያዩ ተግባራ ለተለያዩ ለተለያዩ ቡድን አባላት የመስጠት ብልሃት ነው፡፡ ብልሃቱ በትምህርት ይዘታዊ አውድ ላይ በማተኮር ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን በግል እና በቡድን የሚያከናውኑበት ነው፡፡የመማር ሂደቱም በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ቡድን በመመስረት ለእያንዳንዱ የቡድን አባል ተግባራት ተከፋፍለው ይሰጣሉ፡፡ በቀረበው የትምህርት ይዘት አውድ ላይ አስቀድሞ በግል በመቀጠል ከራሱ የቡድን አባላት ጋር ውይይቶችን በማድረግና

መረጃዎችን በመለዋወጥ በመጨረሻም የተደረሰበትን የጋራ መረዳት ለሌሎች የክፍል ተማሪዎች በማጋራት የሚተገበርና በጣም አስፈላጊ የትብብር መማር ዘዴ ነው፡፡ የቡድን ትግባራው በተማሪዎች መካከል የነቃ ተሳትፎ፣ እኩል የተግባር ክፍፍልና ሃላፊነት የሚጠይቅ በመሆኑ ጠንካራ ማህበራዊ ትስስር ያለውን ትብብራዊነትን ይፈጥራል፡፡በዚህ ዘዴ መምህሩ መረጃ ሰጪ አይደለም፡፡በመማር ማስተማሩ ሂደት አዎንታዊ ተጽእኖ ፈጣሪ፤ተማሪዎች በቡድን ስራዉ የራሳቸውና የቡድን አባላት የመማር ሃላፊነት እንዳላቸው ማሳወቅ አለበት፡፡ለምሳሌ፡-

የትብብር ቡድኑ ይመረታል፣በአንድ ቡድን ውስጥ ላሉ በቡድን አባላት ቁጥር የተለያየ የመጻፊያ ርዕስ ይሰጣቸዋል፡፡

የመጻፊያ ርዕስ ከተሰጣቸው በኋላ ተመሳሳይ ርዕስ የያዙ ተማሪዎችን በመለየት ሌላ ኢ. መደበኛ ወይም ጊዜያዊ ቡድን በመመስረት አንድ ላይ ይመደባሉ፡፡

በዚያ ኢ. መደበኛ ቡድን ላይ ሆነው በያዙት ርዕስ ላይ እንዲወያዩ ይደረጋል፡፡ ውይይቱ እንዳበቃ ወደ መደበኛ(ቋሚ) ቡድናቸው እንዲመለሱ ይደረጋል፡፡

በኢ. መደበኛ ቡድን ውይይት ያገኙት መረጃ ለመደበኛ ቡድና አባላት ያጋራሉ፡፡ ከዚያ ውይይት ባገኙት ሃሳብ በመነሳት በጋራ አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡ ቀጥለው የሚመጣውን አንቀጽ በግላቸው እንዲጽፉ ይደረጋል፡፡

በግል የጻፉትን አንቀጽ በመለዋወጥ መመህሩ ከሰጣቸው መስፈርት(ከአጻጻፍ ስርአት፣ ይዘት፣ የሃሳብ አደረጃጀት፣ከቃላት አጠቃቀምና ሰዋስ አኳያ በሌሎች የቡድን አባላት እርማት ይደረጋል፡፡

ከተሰጣቸው ምጋቤ ምላሽ በመነሳት የራሳቸውን የግል ስራቸውን የመጨረሻውን ጽሁፍ ጽፈው ለክፍል ያቀርባሉ፡፡

ይህን ሂደት መምህሩ ይከታተላሉ፤ይቆጣጠራሉ፤አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጣልቃ በመግባት የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና በትብብር የመማር ክሂላቸውን ይገነባሉ፡፡

ሐ. ባለ ሶስት ደረጀ ቃለ መጠይቅ ፡-ባለ ሶስት ደረጀ ቃለ መባለ ሶስት መጠይቅ አንዱ የትብብራዊ መማር የማስተማር ብልሃት ነው፡፡አላማውም ተማሪዎች በቡድን መማር ውስጥ የሚገጥማቸውን ችግር የመፍታት ፣ተግባራትን የመጨረስና ውጤታማ መሆን የሚያስችል ክሂል የሚያዳብሩበት ነው፡፡መማር በባህሪው ማህበራዊ ስለሆነ ብልሃቱ ተማሪዎች አንዳቸው ካንዳቸው ጋር በሚያደርጉት መጠያየቅ፣ ማሰብ ወይም ማሰላሰል፣ መልስ በመስጠት፣ ማስታወሻ መያዝ፣መወያየትና ሌሎች በማጋራት ይከናወናል ፡፡የዚህ

ብልሃት የመማር ሂደታዊ ደረጃዎች መምህሩ የመጀመሪያ ርእስ ጉዳይ ያነሳና ተማሪዎችን የተለያዩ ጥያቄዎችን ይጠይቃቸዋል፤በራሳቸው ርእሰ ጉዳይ ተማሪዎች ጠያቂና መላሽ በመሆን ቃለ መጠይቅ ያካሂዳሉ፤በሶስተኛ ደረጃ ሚና በመቀያየር ይጠያየቃሉ፡፡

በዚህ ዘዴ ተማሪው የመምህሩ ልምድና እውቀት ቀሳሚ ብቻ ሳይሆን ከቡድን አባላቱ ጋር በሚኖረው ተራክቦም ጭምር ስለሚማር ንቁ አድማጭ፣እውቀት አመንጭ፣ጸሀፊ ወይም መዝጋቢ እና ሌሎች አጋሪ ነው ፡፡ ለምሳሌ፡-

ለቡድን አባላት አንድ ርዕስ ይሰጣል፡፡

ከቡድን አባላት አንዱ ጠያቂ ሌላኛው አንዱ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡ ጠያቂው በተነሳው ርዕስ የሚሰጠውን ምላሽ ይመዝገባል፡፡ በመቀጠል ሚና በመለዋወጥ ተጠያቂው ጠያቂ በመሆን ርዕሱ ላይ ጥያቄ ይጠይቃል፤ የሚሰጠውን ምላሽ ይመዝግባል፡፡ ሌሎችን የቡድን አባላት ምልልሱን ይከታላሉ፤ማስታወሻ ይይዛሉ፡፡ በተነሱ ሃሳቦች ላይ ሃሳብ ይለዋወጣሉ፤የጋራ መረዳት ላይ ይደርሳሉ፤

የመጨረሻውን ጽሁፍ ይጽፋሉ፡፡የእርማቱ መስፈርት በአጻጻፍ ስርአት፣ ይዘት፣በሃሳብ አደረጃጀት፣በቃላት አጠቃቀምና ሰዋስው ላይ ያተኩራል፡፡

መ. በጋራ መማር ፡-በጋራ መማር ትብብራዊ የማስተማር ዘዴን የነደፉት ዴቪዲ ጆንሰን እና ሮጀር ጆንሰን ሲሆኑ በትብብራዊ የመማር ክፍሎች ማትለም በአዎንታዊ ተደጋጋፊነት፣ግለሰባዊ እና ቡድናዊ ተጠያቂነት፣ የፊት ለፊት ተራክቦ በማሳደግ፣ ትብብራዊ ክሂል እና በቡድን ሂደት ላይ የተመሰረተ ነው ፡፡ዘዴው ስብጥራዊ በሆነ መንገድ በአንድ ቡድን ከአራት እስከ አምስት አባላት በማደራጀት ተግባር እንዲያከናውኑ ይደረጋል፡፡ አንድ የትምህርት ይዘት ለቡድን ስራ ይሰጣቸውና የጋራ ውጤት የሚመዘገብበት ነው፡፡ይህ ብልሃት ትኩረቱ በትትብራዊ መማር ክፍል ውስጥ ተማሪዎች ወደ ትግበራዉ ከመግባታቸው በፊት ቡድን ይደራጅና የትግበራ ሂደቱ እንዴት እንደሚፈጽም ይወያያሉ፡፡ ይህም አዎንታዊ ውጤት እንዲመዘገብ ያደርጋል፡፡

ሠ. ቡድን ማሰስ ፡- የቡድን ማሰስ ዘዴ በሻሎሞ ሻርና እና ያይኤል ሻርና በ1992 የዳበረ ዘዴ ሲሆን በአጠቃላይ የክፍል ውስጥ የቡድን አደረጃጀት በተማሪዎች ፍላጎት እና ስብጥራዊነት ላይ ተመስርቶ ተግባራቸውን በቡድን ውይይት እና በፕሮጀክት ስራ ይከናወናል፡፡ይህ ዘዴ አንዱና ዋናው ተማር ተኮር ዘዴ ነው፡፡ሂደቱ ለተማሪዎች የቡድን አሰሳ ከሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች ንኡሳን ርእሶችን በመምረጥ እንዲያቅዱና እንዲሰሩ፣ በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡና ውጤት እንዲገመግሙ ነጻነትን ይሰጣል፡፡እንደ ቡድን አሰሳ

ዘዴ ባብዛኛው ተማሪዎች ከተለያዩ ምንጮች መረጃ ስለሚያስሱ ለሚገጥሙ ችግሮች መፍትሄ ለማፈላለግ በሚደረገው ጥረት ከፍተኛ ወደሆነና በጥልቀት ወደ ማሰብ ደረጃ እንዲሸጋገሩ የሚረዳቸው ነው፡፡ለምሳሌ፡-

ትብብራዊ ቡድኑ አንድ ርዕስ ይመርጣል፡፡ የቡደን አባላቱ በተመረጠው ርዕስ ንዑሳን ርዕሶችን ከነደፉ በኋላ ይከፈላሉ፡፡ በንዑሳን ርዕሶች ላይ በግላቸው ሃሳብ ያመነጫሉ፤ መረጃ ያደራጃሉ፡ በግላቸው ያደራጁትን ሃሳብ ለቡድን አባላቱ ያቀርባሉ፤ይወያያሉ፤ቢጋር ያዘጋጃሉ፡፡

የመጨረሻውን ጽሁፍ ይጽፋሉ፤ለክፍልያቀርባሉ፡፡የእርማቱ መስፈርት በአጻጻፍ ስርአት፣ ይዘት፣ የሃሳብ

አደረጃጀት፣ከቃላት አጠቃቀምና ሰዋስው ያተኩራል፡

ረ. ውጤት ተኮር የቡድን አከፋፈል ፡-ይህ ዘዴ በተለያዩ የትምህርት አይነቶች (ቋንቋ፣ሂሳብ፣ማህበራዊ ሳይንስ ወዘተ) ጥቅም ላይ የዋለ ነው፡፡ውጤት ተኮር የቡድን አከፋፈል አምስት የትግበራ ደረጃዎች አሉት፡፡

ለምሳሌ፡- ለተማሪዎች የተዘጋጀው ርዕስ በጥያቄ መልክ ይገለጽላቸዋል፡፡

ከቀረበው ገለጻ በመነሳት በተሰጠው ርዕስ ላይ የቡድን ውይይት ይደረጋል፡፡እዚህ ጥንቃቄ ሊደረግ የሚገባው የመማር ሂደቱ ውድድር ሊንጸባረቅበት ሰለሚችል የቡድን አደረጃጀቱ ስብጥራዊ እንዲሆን ይመከራል፡፡

በተሰጠው ርዕስ ላይ የቡድን ውይይት ከተደረገ በኋላ አቅም መፈተሻ የጽሁፍ ምዘና በግል እንዲፈተኑ ይደረጋል፡፡ የእርማት ሂደቱ ትኩረት በአጻጻፍ ስርአት፣ ይዘት፣የሃሳብ አደረጃጀት፣ከቃላት አጠቃቀምና ሰዋስው ላይ ይሆናል፡፡ነገር ግን የቡድንውጤቱ ለእውቅና አሰጣጥ ስለሚጠቅም ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

እውቅና ይሰጣል፡፡ ውጤታማነታቸው የሚረጋገጠውና እውቅናው የሚሰጠው በተማሪዎች በቡድን ስራ በመጡት ውጤት አማካይ ላይ ተመስርቶ ቀድሞ ካለ ውጤት ጋር በማመዛዘን ይከናወናል፡፡የትብብራዊ ዘዴ ጠንካራና ደካማ ጎን የትብብራዊ ዘዴ ጠንካራና ደካማ ጎኑን እንደሚከተለው ያስቀምጣል፡፡ጠንካራ ጎን በተማሪዎች መካከል አብሮ የመስራት ክሂል በማሳደግ የራስ መተማመን ይጨምራል፡፡

በተማሪዎች ውጤት ላይ አዎንታዊ ግብ አለው፡፡ራስን ማወቅን፣በጥልቀት የማሰብ ችሎታን፣የእርስ በርስ ግንኙነትን፣ጤናማ ጓደኝነትንና ውጤታማነትን ያሳድጋል፡፡

መምህሩ ከተማሪዎች ጋር አዎንታዊ ግንኙነት እንዲኖረው ያስችላል፡፡ ከውድድር ይልቅ መተባበር ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ያደርጋል፡፡ትብብራዊ ክሂልን በማሳደግ ምክንያታዊ ሃሳብ በማቅረብ መከራከርንና ማሳመንን፣ሀሳብ ማመንጨትንና በፍጥነት ማሸጋገርን፣መፍትሄ አምጪ እንዲሆኑ ያበረታታል፡፡

በትብብራዊ ቡድን በሚማሩበት ጊዜ አእምሯ፣ባህሪያዊና ማህበራዊ ትስስር በመፍጠር አዎንታዊ መደጋገፍን፣ግለሰባዊ ሃላፊነትን፣ትብብራዊነትን ማጎልበትን፣ ማህበራዊ ክሂልን ማሳደግንና ቡድናዊ ሂደትን እንዲያበለጽጉ ያደርጋል፡፡

ደካማ ጎን በማህበራዊ ክህሎታቸው ወይም ተግባቦት ላይ ንቁ ያልሆኑ ተማሪዎች ተጠቃሚ ላይሆን ይችላሉ፡፡ ጀማሪና አዲስ ለሆኑ መምህራን አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በአተገባበር ሂደቱ ተማሪዎች ሚናቸውን በአግባቡ ካተወጡ የሚጠበቀው ውጤት ላይመዘገብ ይችላል፡፡

በትብብራዊ ዘዴ የመምህራን እና የተማሪዎች ሚና የተማሪዎች ሚና

- ከተማሪዎች የሚጠበቀው የመጀመሪያው ነገር እንደ ቡድን አባልነቱ ከሌሎች የቡድኑ አባላት ጋር በጋራ የመስራት ፍላጎት መኖር ነው፡፡
- ተማሪዎች የመማር ሂደት መሪዎች ይሆናሉ፡፡ የመማር ሂደቱን ያቅዳሉ ይቆጣጠራሉ፤ ይተገብራሉ፤ ይገመግማሉ፡፡
- በቡድን ይደራጃሉ በተለይም የጥንድ ቡድን መመሰረት ተመራጭም ነው፡፡
- መማር በዚህ ዘዴ የተማሪዎችን ቀጥተኛና ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ የመምህሩ ሚና
- መምህሩ በክፍል ውስጥ በሚገባ የተደራጀና የተዋቀረ የመማር ሁኔታን ይፈጥራል
- የማስተማር አላማዎችን ያስቀምጣል፡፡ ተግባራትን ያቅዳል፣ የወንበር አቀማመጥ ሁኔታውን ቅርጽ ያስይዛል

ተማሪዎችን በየቡድኑ በመመደብ ተግባራትን ያከፋፍላል መርጃ መሳሪያዎችን ይመርጣል፡፡ ሰዓት ይቆጣጠራል ፡፡

- በዚህ ዘዴ የመምህሩ ዋነኛ ሚና የሚሆነው አመቻቺነት ሲሆን በዚህ ሚናው በክፍል ውስጥ በመዘዋወር

ተማሪዎችን መርዳትና ማገዝ ምጋቤ መምላሽ መሰጠት ጥያቄዎችን መጠየቅ ተማሪዎችን የማሰብ ችሎታ ይመዝናሉ ማለት ነው፡፡

ክፍል ሁለት የማስተማሪያ ውሁዳሀድ

መግቢያ

ይህ የማስተማር ውሁዳሀድ የተዘጋጀው የትብብራዊ ዘዴ የተማሪዎችን በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ችሎታና ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለውን ፋይዳ ለመመርመር ነው፡፡የውሁዳሁዱ ዝግጅት በዘጠነኛ ክፍለ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሀፍና መርሃ ትምህርት ላይ የተመሰረተ ሲሆን በውስጡ የተካተቱ የትምህርት ይዘቶችና ተግባራት ከትብብራዊ ዘዴ የትግበራ ብልሃቶች ጋር ተጣጥመው የቀረቡ ናቸው፡፡

በትብብራዊ ዘዴ በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ትኩረት የሚደረግባቸው የትግበራ ብልሃቶች የተለያዩ ተግባራትን ለተለያዩ የቡድን አባላት መስጠት(ጂግሶው)፣ባለ ሶስት ደረጃ ቃለ መጠይቅ፣ቡድን ማሰስ፣ቢጋራ መማር እና ውጤት ተኮር የቡድን አከፋፈል ናቸው፡፡

ውሁዳሀዱ በስድስት የትምህርት ጊዜያት የተከፈለ ነው፡፡ የትምህርቶቹ የይዘት ትኩረት ከድርሰት የመጻፊያ ስልቶችና ክፍሎችን፣ከመጻፍ ችሎታ ንዑሳን ችሎታዎች የሃሳብ አደረጃጀት፣የአጻጻፍ ስርአት፣ሰዋስውና ይዘት ናቸው፡፡የትግበራ ሂደቱ የትብብራዊ ዘዴን የትግበራ ብልሃቶችን ይጠቀማል፡፡

ትምህርት አንድ የትግበራው ቀን፡- 10፣11 እና 13/06/2015 ዓ.ም.

የትምህርቱ ትኩረት………………………………. የሃሳብ አደረጃጀት

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ………………………..ሁለት ሰዓት

የማስተማሪያ ብልሃት፡- የተለያየ ስራ ለተለያዩ የቡድን አባላት መስጠት(ጂግሶው ብልሃት) (እያንዳንዱ ቡድን አንድ ርዕስ ይመርጣል) የትምህርቱ አላማ፡-ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ተገቢውን የሃሳብ አደረጃጀት የያዘ አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡

ተማሪዎች ወደ ተግባር አፈጻጸም ከመግባታቸው በፊት ስለ አንቀጽና አስተዋጽኦ አነዳደፍ ግንዛቤ እንዲኖራቸው መንደርደሪያ ሃሳብ ይሰጣቸዋል፡፡

ማስታወሻ

አንቀጽ ማለት ገባ ብሎ የሚጀምር፣ አንድ ነጠላ ሐሳብን ለመግለጽ ሲባል፣በቁጥር አንድ ወይም ከአንድ የበለጡና የሐሳብ ተዛምዷቸውን የጠበቁ አረፍተ ነገሮች የሰፈሩበት የድርሰት ቅርጽ ነው፡፡አንቀጽ ብዙውን ጊዜ አንድ ኃይለ ቃል(መንደርደሪያ አረፍተ ነገር) እና ከአንድ በላይ መዘርዝር አረፍተ ነገሮችን ሊይዝ ይችላል፡፡

እነዚህ መሪውና መዘርዝር አረፍተ ነገሮች በአንድ አንቀጽ ወይም ድርሰት የአጻጻፍ ሂደት አንቀጾች ተገቢ የሆነ የሃሳብ አደረጃጀት እንዲኖራቸው የማድረግ ድርሻ አላቸው፡፡

አንድን ድርሰት መጻፍ ከመጀመራችን በፊት ሶስት ዋና ዋና ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ እነዚህም ተግባራት

ርዕስ መምረጥ፣የተመረጠውን ርዕስ መወሰን ወይም ማጥበብና አስተዋጽኦ ማዘጋጀት ናቸው፡፡ አስስዋጽኦ ዋናውን ጽሁፍ ለመጻፍ፣መንገድ ቀያሽ ወይም ትልም ነው፡፡ጥቅሞቹም፡-

- አላማን ግልጽ ለማድረግና ሐሳብ ከአላማ ጋር ለማዛመድ ያግዛል፡፡
- ድርሰት ከመጻፉ በፊት የሐሳብ ቅንጅት ለማየትና ለማስተካከል ይጠቅማል፡፡
- መልዕክት ለማስተላለፍ ራሱን የቻለ መሳሪያ በመሆን ያገለግላል፡፡
- ተግባር ጽሁፍ በሚጻፍበት ጊዜ ከዋናው ሃሳብ እንዳንወጣ

አንድ ያደርጋል፡፡

የተለያዩ ቡድኖች የተለያየ የመጻፊያ ርእስ ይመርጣሉ፡፡መምረጣቸው ሲረጋገጥ ሌላ ኢ መደበኛ ቡድን ይዋቀራል፡፡በጊዜያው ቡድን ይዘውት በሄዱት ርዕስ ላይ ይወያያሉ፡፡ የውይይት ሃሳባቸውን ይጽፋሉ፡፡ውይይቱ ሲያበቃ ወደ መደበኛው ቡድናቸው ይመለሳሉ፡፡ በጊዜያዊ ቡድን የተወያዩትን ሃሳብ ለቡድን አባላት ያጋራሉ፡፡

ተግባር ሁለት

የውይይት ሃሳባቸውን መነሻ አድርገው አስተዋጽኦ ይነድፋሉ፡፡በተነደፈው አስተዋጽኦ ላይ ይወያያሉ፤ስህተት ካለ ያርማሉ፡፡

ተግባር ሶስት

ያዘጋጁትን አስተዋጽኦ ንድፍ መሰረት በማድረግ የመጀመሪያ ረቂቅ ጽሁፍ በግል ይጽፋሉ፡፡ረቂቅ ጽሁፋቸውን ሲጨርሱ ከቡድን አባላት ጋር ደግመው እንዲከለሱና ስህተት

አርመው የመጨረሻውን ጽሁፍ እንዲጽፉ ይደረጋል፡፡በዚህ ሂደት የመምህሩ ክትትልና እገዛ ትኩረት ይሻል፡፡

ተግባር አራት

ቡድኑ የጻፈው የመጨረሻው አንቀጽ በቡድን አቅራቢው በኩል ለክፍሉ ይቀርባል፡፡ ክፍሉም አስተያየት ይሰጣል፡፡እርማት ካለ ይወሰዳል፤ ይታረማል፤ የታረመው ጽሁፍ ለመምህሩ ይሰጣል፡፡

ትምህርት ሁለት ቀን፡- 16 እና 17/06/2015 ዓ.ም.

የትምህርቱ ትኩረት…………ስርአት ነጥቦችን በጽሁፍ ውስጥ መጠቀም

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ… 80 ደቂቃ የማስተማሪያ ብልሃት፡- ማሰብ መጎዳኘትና ማጋራት የትምህርቱ አላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ያለ ስርአተ ነጥብ የተጻፈውን ጽሁፍ

በተገቢው ስርአተ ነጥብ አጠቃቀም አስተካክለው ይጽፋሉ፡፡

ማስታወሻ

በጽሁፍ ውስጥ የስርዓት ነጥቦች ዋነኛ ተግባር የጽሁፉን መልዕክት ሳይድብሰበስ አንባቢ ወዲያውኑ እንዲረዳ ማገዝ ነው፡፡ስለሆነም ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው መጠቀም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

የተዘጋጀው ጽሁፍ

የኃይል አጥረት ለደኖች መመናመን ዋነኛ መንስኤ እየሆነ መጥቷል የኤሌክትሪክ ኃይል ባልደረሰባቸው አካባቢዎች ህዝቡ ደንን እየጨፈጨፈ ለማገዶነት ያውላል የደኖች በጭፍጨፋ መመናመን ደግሞ የአየር ንብረት መዛባትን ያስከትላል በዚህ የተነሳ በቂ የዝናብ መጠን ላይገኝ ወይም ከሚፈለገው በላይ የዝናብ መጠን ተገኝቶ በሰዎች በእንሳስትና በሰብሎች ላይ ትልቅ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል ስለሆነም እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ማለትም መንግስት የዘርፉ ባለሞያዎች ማህበረሰቡና ሌሎችም ትኩረት ሰጥተው ሊሰሩ ይገባል

ተግባር አንድ

የተዘጋጀው ጽሁፍ ለሁሉም የቡድን አባላት ይሰጣቸዋል፡፡በተሰጣቸው ጽሁፍ ላይ ያለውን የስርአተ ነጥብ ክፍተት በግል ይመለከታሉ፤ ያሰተዋሉትን በማስታወሻቸው ይጽፋሉ፡፡

ተግባር ሁለት

በግል ሊሆን ይገባል ብለው ያሰቡትን የስርአተ ነጥብ አቀማመጥ እያንዳንዳቸው ለቡድን አባላት ያቀርባሉ፡፡በቀረበው ሃሳብ ላይ ይወያያሉ፡፡ምጋቤ ምላሽ ይሰጣጣሉ፡፡ ከተሰጠው አስተያየት በመነሳት እንደገና እያስተካከሉ ይጽፋሉ ፡፡

ተግባር ሶስት

በሚሰጣቸው የመገምገሚያ መስፈርት አማካኝነት የራሳቸውን ጽሁፍ እንዲገመግሙና ውጤት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

ትምህርት ሶስት ቀን፡- 20፣24 እና 25/06/2015 ዓ.ም.

የትምህርቱ ትኩረት……………………………….. ሰዋስው

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ………………………...2፡00 ሰዓት

የማስተማሪያ ብልሃት፡-ባለ ሶስት ደረጃ ቃለ መጠይቅ

የትምህርቱ አላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ትክክለኛ የሰዋሰው አገባብ የተከተለ በገላጭ ስልት አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡

ማስታወሻ

ገላጭ ድርሰት

ከድርሰት መጻፊያ ስልቶች አንዱ ገላጭ ስልት ሲሆን የአንድ ነገር ምንነት፣አገኛኘት፣ ባህሪያት፣ ዓይነት፣መጠን፣ቅርጽ፣አሰራር፣ጠቀሜታ፣ጉዳት ወዘተ፣የሚያብራራ ነው፡፡አንድን ተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሰራሽ ነገር አስመልክቶ ምንድ ነው? ምን ማለት ነው ? የተሰራው ከምንድን ነው? እንዴት ተሰራ ?እንዴት እንዲህ ሊሆን ቻለ? ምን ጉዳት ምን ጥቅም አለው? ወዘተ. በሚል ለሚቀርቡ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ለመስጠት የሚሞክር ድርሰት ነው፡፡

ተግባር አንድ

ተማሪዎች በቡድን በመሆን የ"ቤተሰብ ፍቅር" በሚል በቀረበው ርዕስ ላይ ጥያቄ እንዲጠያየቁና ሃሳብ እዲመያነጩ ይደረጋል፡፡በመጠያየቅ ሂደት ጠያቂው የሚሰጠውን ምላሽ ይመዘግባል፡፡ በመቀጠል ሚና በመለዋወጥ ተጠያቂው ጠያቂ በመሆን ይጠይቃል፤ የሚሰጠውን ምላሽ በማስታወሻው ይመዘግባል፡፡ሌሎች በትኩረት ያዳምጣሉ፤ማስታወሻ ይይዛሉ፡፡

ተግባር ሁለት በመጠያየቅ ሂደት በርዕሱ ዙሪያ የተነሱ ሃሳቦችን መነሻ በማድረግ አስተዋጽኦ ይነድፋሉ፡፡ ተግባር ሶስት የተነደፈውን አስተዋጽኦ መሰረት በማድረግ የመጀመሪያ ረቂቅ በግል ይጽፋሉ፡፡በግል

የተጻፈው ረቂቅ ጽሁፋቸው ለቡድን አባላት ይቀርብና አስተያየት ወይም ምጋቤ ምላሽ ይሰጣል፤ከተሰጠው ምጋቤ ምላሽ በመነሳት ታርሞ እንደገና እንዲጽፉ ይደረጋል፡፡

ተግባር አራት

በቡድኑ ተጽፎ የተጠቃለለው ጽሁፍ ለክፍሉ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡በክፍሉ ተማሪዎች አስተያየት ይሰጥበታል፡፡ከተሰጠው አስተያየት ወይም ምጋቤ ምላሽ በኋላ እርማት የሚያስፈልገው ከሆነ ታርሞ እንደገና ይጻፋል፡፡ በመጨረሻ ጽሁፉ ለመምህሩ ይሰጣል፡፡

ትምህርት አራት ቀን፡- 24/06/2015 እና 27/06/2015

የትምህርቱ ትኩረት……………………………….. ጅምር ሃሳብ መጨረስ

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ………………………..80ደቂቃ

የማስተማሪያ ብልሃት፡- ባለ ሶስት ደረጃ ቃለ መጠይቅ

የትምህርቱ አላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ተገቢነት ያለውን ሃሳብ ተጠቅመው ጅምር ሃሳብ ወይም መሪ አረፍተ ነገር በመጨረስ አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡

የተዘጋጀው ጅምር ሃሳብ

ሰላም ለአንድ ሀገር የህልውናው መሰረት ነው፡፡ ______________________________________

__________________________________________________________________________________

_______________

__________________________________________________________________________________

_____________፡፡

ተግባር አንድ

ተማሪዎች በቡድናቸው ሆነው ጅምር ላይ የቀረ ሃሳብ ተሰጥቷቸው እንዲወያዩበት ይደረጋል፡፡ በውይይት ሂደታቸው ማስታወሻ በጽሁፉ ይይዛሉ፡፡በዚህ ብልሃት ጥልቅ የሆኑ ሃሳቦች ይነሳሉ፡፡

ተግባር ሁለት በተሰጠው ጅምር ሃሳብ የነበራቸውን የውይይት ሃሳብ መነሻ አድርገው አስተዋጽኦ ይነድፋሉ፡፡ ተግባር ሶስት በቡድን የተነደፈውን አስተዋጽኦ መነሻ በማድረግ የግል ጽሁፋቸውን ይጽፋሉ፡፡ ተግባር አራት

በግል የጻፉት ጽሁፍ ለቡድን አባላት ቀርቦ አስተያየት ይሰጥበታል፡፡ ይታረማል፤ ይከለሳል፤ እንደገና ይጻፋል፡፡

ተግባር አምስት በዚህ የተግባር ደረጃ የመጨረሻው ጽሁፍ ለክፍል ቀርቦ አስተያት ከተሰጠ በኋላ ታርሞ ይጠቃለላል፡፡ ትምህርት አምስት

ቀን፡- 30/06/2015 እና 1/07/2015

የትምህርቱ ትኩረት……………………………….. አረፍተ ነገር

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ……………………….. 80 ደቂቃ

የማስተማሪያ ብልሃት:-ማሰብ መጎዳኘትና ማጋራት

የትምህርቱ አላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ተዘበራርቆ የተቀመጠ አረፍተ ነገር ቅደም ተከተሉን አስተካክለው ርዕስ በመስጠት ተራኪ ድርሰት ይጽፋሉ፡፡

ማስታወሻ ተራኪ ድርሰት

ተራኪ ድርሰት በጣም ከተለመዱ የድርሰት መጻፊያ ስልቶች አንዱ ነው፡፡ይህ ስልት ድርጊቶችንና ሰንሰለታዊ እውነቶችን የድርጊት ጊዜ ቅድም ተከተላቸውን ጠብቆ እንዲህ እንዲህ ሆነ፤ እንዲህ እንዲህ ተደረገ እያለ የሚተርክልን ጽሁፍ ነው፡፡ታሪኩን የሚያቀርብልን ራሱ የድርጊቱ ተሳታፊ ለሆን ይችላል፡፡የድርጊቱ ተሳታፊ ካልሆነ ድርጊቱን የተመለከተ፣የደረሰበትን፣በልምድ ያገኘውንና ከሌላ ሰምቶ የሚያቀርበው ሊሆን ይችላል፡፡

የተዘጋጀው አረፍተ ነገር

1.በክረምት ለእረፍት ትምህርት ሲዘጋ እንደምጠይቃት አስቀድሜ ለአክስቴ ቃል ገብቸላት ነበር፡፡

2.በዚያው ሰሞን እናቴ አክስቴን ጠይቃ ስትመለስ አክስቴ ብቻዋን እንደሚትኖር የነገረችኝ ትዝ አለኝና ምናልባት የሚሰማኝ ያጣሁት ደህና ባትሆን ይሆናል ብሎ ሃሳብ ገባኝ፡፡ምን ማድረግ እንዳለብኝ ማሰላሰል ጀመርኩ፡፡

3.በልጅነት የምወዳትን አክስቴን ለመጠየቅ ወደ ፍቼ ከተማ በሄድኩ ጊዜ ያጋጠመኝ ነገር መቼም አይረሳኝም፡፡

4.ለግማሽ ሰዓት ያህል ከቆየሁ በኋላ፣ባረጀው ቁመቱ በጣም ከፍ ባለው የፍልጥ አጥር ላይ ተንጠልጥዬ አክስቴን ለመጥራት ወሰንኩ፡፡

5.የአክስቴን አይን ለማየት ብቸኩልም ወደ ቤቷ አጥር ግቢ ከመድረሴ በፊት ጥቅጥቅ ባለው የባህር ዛፍ ጫካ ውስጥ ጥቂት መጓዝ ነበረብኝ፡፡

6.እኔም ከታች አግጥጦ ከሚጠብቀኝ ጉቶ ላይ አረፍኩኝ፤ከዚያ በኋላማ ሁለት የጎድን አጥንቶቼ ተሰብረው አክስቴ አልጋ ላይ እንደተኛሁ ከመንቃቴ በስተቀር በመካከል የሆነውን ነገር አላስታውስም፡፡

7.ድካሜን ሁሉ ረስቼ ጫካውን በሩጫ በማለፍ እውጭ በር እንደደረስኩ በሩን ቶሎ ቶሎ አንኳኳሁ፡፡ነገር ግን፣ “ማነህ” የሚለኝ አጣሁ፡፡

8.እንደምንም ብዬ በመውጣት አጥሩ ጫፍ እንደደረስኩ የጨበጥኩት የበሰበሰ ፍልጥ ተሰበረ፡፡

9.የሐምሌን ጭጋግና ዝናብ ችዬ በልጅ እግሬ እየገሰገስኩ ከምኖርበት የገጠር መንደር ከአዲስጌ ግማሽ ቀን ተጉዤ ስድስት ሰዓት ገደማ ፍቼ ከተማ ደረስኩ፡፡

10.እንደገናም በሩን ደጋግሜ ደበደብኩት፤ምንም መልስ የለም፡፡

ተግባር አንድ

ተዘበራርቀው የተቀመጡ አረፍተ ነገሮች የቡድን አባላት በግል እንዲያስተካክሉ፣ቅደም ተከተል

እንዲያስይዙና ርዕስ እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

ተግባር ሁለት

የግል ስራቸውን ይዘው ወደ ቡድን አባላት ይመለሱና መያዝ በሚገባው ቅደም ተከተል ተወያይተው የተሰጠው ርዕስ የቀረበውን ሃሳብ አጠቃሎ የያዘ መሆን አለመሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡አስተያየት ይሰጥበታል፡፡የተሻለ የሚባለው ርዕስ ይሰጠዋል፡፡

ተግባር ሶስት

የመጨረሻው የቡድኑ ስራ ለክፍል ይቀርባል፤አስተያየት ይሰጣል፤እርማት ካለው ታርሞ የመጨረሻው ጽሁፍ ይጻፋል፡፡

ትምህርት ስድስት ቀን፡- 04 እና07/2015 ዓ.ም.

የትምህርቱ ትኩረት፡- የሃሳብ አደረጃጀት፣ስርአተ ነጥብ፣ይዘት፣የአጻጻፍ ስርአትና የቃላት ምርጫ ናቸው፡፡

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ………………………...2፡00

የትምህርቱ አላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፣ “አከባቢያችን” በሚል ርዕስ ድርሰት ይጽፋሉ፡፡

ተግባር አንድ

ተማሪዎች በቡድን በመሆን ”አከባቢያችን” በሚል በቀረበው ርዕስ ላይ ጥያቄ እንዲጠያየቁና ሃሳብ እዲመያነጩ ይደረጋል፡፡በመጠያየቅ ሂደት ጠያቂው የሚሰጠውን ምላሽ ይመዘግባል፡፡ በመቀጠል ሚና በመለዋወጥ ተጠያቂው ጠያቂ በመሆን ይጠይቃል

የሚሰጠውን ምላሽ በማስታወሻው ይመዘግባል፡፡ሌሎች በትኩረት ያዳምጣሉ፤ማስታወሻ ይይዛሉ፡፡

ተግባር ሁለት

በመጠያየቅ ሂደት በርዕሱ ዙሪያ የተነሱ ሃሳቦችን መነሻ በማድረግ አስተዋጽኦ ይነድፋሉ፡፡

ተግባር ሶስት

ያዘጋጁትን አስተዋጽኦ መሰረት በማድረግ የመጀመሪያ ረቂቅ በግል ይጽፋሉ፡፡ በግል የተጻፈው ረቂቅ ጽሁፋቸው ለቡድን አባላት ይቀርብና አስተያየት ተቀብለው እንደገና እንዲጽፉ ይደረጋል፡፡

ተግባር አራት

በተማሪዎች ተጽፎ የተጠቃለለው ጽሁፍ ለክፍል እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ አስተያየት ይሰጥበታል፡፡እርማት የሚያስፈልገው ከሆነ ታርሞ እንደገና ይጻፋል፡፡

ክፍል ሶስት የግልና የቡድን የትግበራ ሂደት መገምገሚያ ቅጽ

ሀ.የትብብር ቡድን አባላት በክፍል ውስጥ የነበራቸውን የመማር ልምምድ ግላዊ ተሳትፎ ለመገምገም የተዘጋጀ ቅጽ

ውድ ተማሪዎች፡- በትብብራዊ ዘዴ በክፍል ውስጥ የነበራችሁን ግላዊ የመማር ተሳትፏችሁን ለመገምገም የሚያስችላችሁ ጥያቄዎች በሰንጠረዥ ቀርበውላችኋል፡፡የቀረቡ ጥያቄዎችን በማንበብ ከቀረቡ አማራጮች ተሳትፏችሁን የሚገልጸውን በመምረጥ በ “x” አመልክቱ፡፡

| ተ.ቁ. | መጠይቆች | ሁልጊዜ | አልፎ አልፎ | በፍጹም |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ትብብራዊ ዘዴ ጠንካራ የሆነ አዎንታዊ መደጋገፍ ፈጥሮልኛል፡፡ | | | |
| 2 | ትብብራዊ ዘዴ የቀረበውን የትምህርት ይዘት በማሰብና በመረዳትከሌሎች ጋር በመነጻኘት ማጋራት አስችሎኛል፡፡ | | | |
| 3 | ትብብራዊ ዘዴ በክፍል ውስጥ የነበረውን የመማር ሂደትናትምህርቱን በሚገባ እንዲረዳ አስችሎኛል፡፡ | | | |
| 4 | ትብብራዊ ዘዴ የቡድን አጋሮቹ የተሰጣቸውን ተግባር በተገቢውማከናወናቸውን እንዳረጋገጥ አድርጎኛል፡፡ | | | |
| 5 | በትብብራዊ ዘዴ የትምህርቱን ሂደት ማጠቃለያ መስጠትችያለሁ፡፡ | | | |
| 6 | ትብብራዊ ዘዴ በመማር ሂደት ማስታወሻዎችን በመያዝ ሌሎችየቡድን አባላት ማብራራት ችያለሁ፡፡ | | | |

ለ.የትብብር ቡድን አባላት በክፍል ውስጥ የነበራቸውን የመማር ልምምድ ቡድናዊ ተሳትፎ ለመገምገም የተዘጋጀ ቅጽ

ውድ ተማሪዎች፡- በትብብራዊ ዘዴ በክፍል ውስጥ የነበራችሁን ቡድናዊ የመማር ተሳትፏችሁን ለመገምገም የሚያስችላችሁ ጥያቄዎች በሰንጠረዥ ቀርበውላችኋል፡፡የቀረቡ ጥያቄዎችን በማንበብ ከቀረቡ አማራጮች ተሳትፏችሁን የሚገልጸውን በመምረጥ በ “x” አመልክቱ፡፡

| ተ.ቁ. | መጠይቆች | ሁልጊዜ | አልፎ አልፎ | በጭራሽ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በትብብር መማር በቡድን አባላት መካከል ጠንካራ ማህበራዊትስስር ፈጥሯል፡፡ | | | |
| 2 | ትብብራዊ ዘዴ የክፍል ውስጥ ተግባራትን በተጠያቂነት መንፈስመተግበር አስችሎናል፡፡ | | | |
| 3 | ትብብራዊ ዘዴ ግላዊ ውድድርን በማስቀረት ጠንካራ የመተጋገዝልምድ ፈጥሮናል፡፡ | | | |
| 4 | ሁሉም የቡድን አባላት የተሰጣቸውን ተግባርና ሚናቸውንበተገቢው መወጣታቸውን ማረጋገጥ አስችሎናል፡፡ | | | |
| 5 | እያንዳንዱ ቡድን የየራሱን ማጠቃለያ ለሌሎች ቡድኖች ማቅረብአስችሎናል፡፡ | | | |